ከዚያም ከአንሷሮች ሌላ ተናጋሪ ተነሳ፡፡ ጉዳዩን የነሱ ተናጋሪ ባስቀመጠው ክበብ ውስጥ ለመመለስ ሽቶ አለም፡- «እናንተ ቁረይሾች ሆይ! ከናንተም መሪ ይኑር፤ ከኛም እንደዚሁ፡፡» ዑመር አለ፡- «ጫጫታው በዛ፡፡ ድምጾች ከፍ አሉ፡፡ መለያየትን እስከፈራሁ ድረስ» አልኩም «አንተ አቡበክር እጅህን ዘርጋ፡፡ እጁን ዘረጋ፡፡ ቃል ተጋባሁት፡፡ ከዚያም ሙሃጂሮች ቃል ገቡለት፡፡ ከዚያም አንሷሮቹ ቃል ገቡለት፡፡» ሰዕድ ኢብኑ ዑባዳ የአንሷሮች ተመራጭ በግፍ ሊገደል ተቃርቦ ነበር፡፡ ሰዎች አቡበክር ጋር ቃል ለመጋባት ተገፋፉ፡፡ ሰዕድን ሊገድሏቸው እስከቀረቡ ድረስ ይህ ሳያውቁ ነው»

እንደዚሁ ሰሓባዎች ሪድዋኑሏሂ ዐለይሂም ልዩነቱን በልቦች ውስጥ የጥላቻ ዝቃጮች ሳይቀሩ መቁረጥ ችለዋል፡፡ የሙስሊሞች ቃል አንድ ሆነች፡፡ የሕቅን መልዕክት ለማሳለፍ አላህ እንድትሠራጭ ወደሻበት፡፡

4/ ዘካን በከለከሉ ሰዎች ዙሪያ መለያየታቸው፡- ይህ ጉዳይ አደገኛ ከሆኑት ሰሓባዎች ከተለያዩበት አራተኛ ጉዳይ ነበር፡፡ በተሸለሙበት እውነተኛ ሐሳብ ከመለያየት ሥርዓት ጋር ሊያሸንፉትን ችለዋል፡፡ አቡበክር ረዲየሏሁ ዐንሁ በኸሊፋነት ቃል ከተገባላቸው በኋላ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ አዲስ ሰለምቴዎች የሆኑ ከፊል ጎሳዎች ከእስልምና ተመለሱ፡፡ ከፊል ነብይነትን የሞገቱ ሰዎችም ቀጠሉ፡፡ እንደ ሙሰይለመተል ከዛብና ሌሎችንም ይመስል ከፊል ጎሳዎችም ሶላትን ከመስገድና ዘካን ከመስጠት እንደተከለከሉ ሁሉ ከፊል ጎሳዎች ደግሞ ዘካ ከመስጠት ብቻ ተከለከሉ፡፡ የከፊሎቹ ዘካን መስጠት መከልከል ምክንያት ለአቡበክር ረዲየሏሁ ዐንሁ ለመስጠት ደራና ኩራት ይዟቸው ነው፡፡ ሰይጣን ለከፊላቸው በተበላሸ ትችት ሸልሞላቸው ነው፡፡ እነሱም አሉ፡- «እሷ በሸሪዓው ውስጥ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ውጭ ላለ አካል አትሰጥም፡፡ ውሰድ የተባሉት እሳቸው ናቸውና፡፡ በሷ ምንዳቸውን ማጽዳትና ማስተዳደግ እንዲሁም ዱዓ ማድረግ በቀጣዩ አንቀጽ ውስጥ ለረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ ነውና፡-»

«ከገንዘቦቻቸው ስትሆን በርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የሆነችን ምጽዋት ያዝ፤ ለነሱም ጸልይላቸው፤ ጸሎትህ ለነርሱ እርካታ ነውና፤ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡» (አት-ተውባ 9፡103)

ዘካን ከልካይ ሰዎች ረስተዋል ወይም እንደረሳ ሰው ሆነዋል፡፡ ይህ ንግግር በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የማያጥር መሆኑን፡፡ ይልቁንስ ከርሳቸው በኋላ በጉዳዩ ላይ የሚሾመውንም ያካትታል፡፡ እሱም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደ አስተዳደርና እንደ ሙስሊሞች መሪ ሆነው ነውና የተነገራቸው፡፡ ዘካን ከባለቤቶቿ መውሰድና ለምትገባቸው መስጠት ማህበረሰቡን ሥርዓት በማስያዝ ጉዳዮች ውስጥ

ይካተታል፡፡ ሑዱዶቹንና ሌሎችንም እንደማቋቋም ይቆጠራል፡፡ ተጠያቂነቷ በሙስሊሞች ጉዳይ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ሕዝብን ተከተው ቋሚ በሆኑት ላይ ትሸጋገራለች፡፡

ማንኛውም ሙስሊም ሁሉ ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ቃል እንደሚጋባ ሁሉ ቃል ከሚጋባቸው ነገሮች ውስጥ ሶላትን በማቆም ዘካን በመስጠት በመካከላቸው መለያየትን ከማያስችል ነገር የመጀመሪያው ኸሊፋ የእስልምናው ሂደት እንዲቀጥል ካላቸው ጉጉት አቡበክር ረዲየሏሁ ዐንሁ እነሱን ለመዋጋት ይወስናሉ፡፡ እንዲፀፀቱና ዘካን እንዲሰጡ ወደ እስልምና ክልልም እንዲመለሱ ለረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ቃል የገቡትን እንድይዙ ለማስገደድ፡፡

በዚህ የመጀመሪያው ኸሊፋ የያዙት አቋም ላይ በሳቸውና በዑመር መካከል ልዩነት ይፈጠራል፡፡ ያ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘካን የከለከሉ ሰዎችን መጋደል አይፈቀድም ማለት የታያቸው አቡ ሁረይራ አላህ ይውደድላቸውና እንዲህ ይላሉ፡-

«ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሲሞቱ ጊዜ አቡበክርም ረዲየሏሁ ዐንሁ ነበሩና ከዐረቦች የካደ ሰው ካደ፡፡ ዑመርም አሉ፡- ‹ሰዎችን እንዴት ትዋጋቸዋለህ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ብለው ሳለ፡- ‹ሰዎችን ላ ኢላሀ ኢለላህ እስከሚሉ ድረስ ልጋደላቸው ታዝዣለሁ፡፡ ያላትም ሰው ከኔ ገንዘቡንም ነፍሱንም ጠብቋል፡፡»

(ዘካን ባለመስጠት) በሷ ሙብት እንጅ ሒሳቡም በአላህ ላይ ነው›»

አቡበክርም «በአላህ ይሁንብኝ! ለረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ይሰጧት የነበረችን ግለገል ቢከለክሉኝ በመከልከላቸው እዋጋቸዋለሁ፡፡» ዑመርም አሉ፡- «በአላህ ይሁንብኝ! አላህ የአቡበክርን ልብ ጦርነት ለመዋጋት ያሰፋ ጊዜ እሱ ሐቅ መሆኑን አወኩኝ፡፡» ኢብኑ ዘይድ ደግሞ አለ «ሶላትና ዘካ አንድ ላይ ነው፡፡ ግዴታ የሆኑት በመካከላቸው አልተለየም፡፡ አነበበም

«ቢፀፀቱም ሶላትንም ቢሰግዱ ዘካንም ቢሰጡ የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ናቸው፡፡» (አት-ተውባ 9፡11)

ሶላትን ከዘካ ጋር እንጅ መቀበልን እምቢ አለ፡፡ አለም፡- «አላህ አቡበክርም ይማራቸው፤ ምን እንዲህ ዐዋቂ አደረገው!» በሶላትና በዘካ መካከል የለየን በመዋጋት ላይ የሙጥኝ ማለታቸውን ሸቶ ነው›»

በአቡ በክርና በዑመር መካከል የልዩነቱ ምክንያት ሰይዲና ዑመርና አብረዋቸው ያሉት የሐዲሡ ቅርፅ የሚያመለክተውን ግልጽ መልዕክት ያዙ፡፡ አንድ

ሰው ሁለቱን ሸሃዳ በማለት ወደ እስልምና በመግባቱ ብቻ ይሆናል ብለው አሰቡ፡፡ ደሙን የሚጠብቅ ገንዘቡንም መዋጋቱመረ እርም የሚሆን መሰላቸው፡፡

ሲድ-ዲቅ ረዲየሏሁ ዐንሁ የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) አባባል «ኢላ ቢ ሐቂሃ» የሚለውን ያዘ፡፡ ዘካን የገንዘብ ሐቅ/መብት እሱን ከመስጠት መከልከል የነፍስንና የገንዘብን ጥብቅነት ያሳጣል ብሎ አሰበ/አመነ፡፡ አብዛኞቹ በቁርኣን አንቀጾችና በበርካታ ሐዲሦች ዘካና ሶላት ተቆራኝተው ከመምጣታቸውም እነሱ ተመሳሳዮች ናቸው፡፡ በመካከላቸው ልዩነት የለም ማለትን እንደተረዳ ሁሉ፡፡

ሶላትን መተው ከእስልምና መመለስና ነብይነትን ለሚሞግት ለመከተል ማስረጃ በመሆኑ ላይ የተስማሙ ከሆኑ ዘካን አለመስጠትም ሠሪው እሚወጋበት የሙርተድነት ማስረጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በዚህም ሲድ-ዲቅ ቀሪ ሰሓባዎችን በትክክለኛ ምርምሩ ዘካ ከልካዮችን መዋጋት ግዴታ መሆኑን ማሳመን ችለዋል፡፡ እስካልተፀፀቱ ድረስ ከእስልምና የተመለሱ አድርጎ ማየት ሶላት እስከሚቆሙና ዘካን እስከሚሰጡ ድረስ በዚህም አቋም በዚች አስቸጋሪ በሆነች ጥያቄ ውስጥ የነበረው ልዩነት ተነሳ፡፡ ዘካ ከልካዮችን በመውጋት ቃል አንድ ሆነች፡፡ ሙሉ የሆነን መመለስ ከእስልምና የተመለሱትን ሰዎች መዋጋት ላይ አንድ እንደሆችው እስልምናም ከጫወታና እያንዳንዱን ማዕዘን በየተራው ከማፍረስ ሙከራ ተጠበቀ፡፡ ሙሉውን ለማፍረስ በሞከሩት ላይ ሙከራ ከተሸነፉ በኋላ ይህ አቋም ከሲድ-ዲቅ ከዚያም ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓቦች ባልነበር ለእስልምና ቋሚ አትቆምለትም ነበር፡፡ በመዲናና በመካም ያጥር ነበር፡፡ ወደነሱም ይሰብሰብ ነበር፡፡ በደሴቷም አጠቃላይ አካባቢ ላይ ከእስልምና መውጣትና ፈተና ይሰፍን ነበር፡፡

o/ በከፊል ፊቅህ መስአላዎች መለያየታቸው፡- በቁጥጥር ሥር የዋሉትን አደገኛ ጉዳዮች ብንተውና ከሷ ውጭ ብንፈልግ በልዩነት ሥርዓትና ምሁራኖች ከፊላቸው ከፊላቸውን ስለማክበር ገር እማያበቃ ነገርን እናገኛለን፡፡ ሁለቱ ሸይኾች - አቡበክር እና ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁማ ከተለያዩባቸው ጉዳዮች ካወሳነው ውጭ የሪዳ ሰዎች ሙርከኛ ነበር፡፡ አቡበክር የሙርተዶችን ሴቶች መርከኛ መሆናቸውን ያምኑ ነበር፡፡ በዑመር ተቃራኒ እሳቸው በኸሊፋነታቸው ጊዜ የአበቡክርን ብይን ሽረዋል፡፡ በዚህ መስኣላ ላይ ወደቤተሰቦቻቸው ነፃዎች ሆነው መልሰዋቸዋል፡፡ ለነሱ ለአሳዳሪዋ የወለደች ስትቀር ከነሱ ውስጥ ኸውለት የጀዕፈር ልጅ ሐነፊያ በመባል የምትታወቀዋ የሙሐመድ ቢን ዐሊይ - ረዲየሏሁ ዐንሁም እናት የሆነችው የተከፈቱ ሀገሮች መሬቶች አከፋፈልም እንደተለያዩ አቡበክር መከፈል አበለባት ማለትን ያምኑ ነበር፡፡ ዑመር ደግሞ ወቅፍ መሆኗን አለመከፈሏን ያምኑ ነበር፡፡ እንደዚሁም በስጦታ መበላለጥም ላይ ተለያይተዋል፡፡ አቡበክር በስጦታ

መስተካከል አለባቸው ይሉ ነበር፡፡ ዑመር ደግሞ መበላለጥ አለባቸው ይሉ ነበር፡፡ በሙስሊሞች መካከል በስጦታቸው አበላልጠዋል፡፡

ዑመር ከሳቸው የሚተካ ሰው አላደረጉም፡፡ አቡበክር ደግሞ ዑመርን ምትክ አድርገዋል፡፡ ከፊቅህ መስአላዎች በብዙ በመካከላቸው ልዩነት እንደበረም ሁሉ፡፡ ነገር ግን ልዩነቱ ሁለታቸውንም ፍቅርን እንጅ አልጨመረላቸውም፡፡ አቡበክር ዑመርን የተኩ ጊዜ ከፊል ሙስሊሞእ አሏቸው፡- «ለጌታህ ምን ትለው ይሆን ዑመርን በኛ ላይ ስለመተካትህ ሲጠይቅህ» እለዋለሁ አለ፡- «»ጌታዬ ሆይ እኔ በነሱ ላይ ከአሕሎችህ የተሻለውን ተክቼላቸዋለሁ» አንዳቸው ለዑመር ባለ ጊዜ፡- «አንተኮ ከአቡበክር የተሻልክ ነህ» ሊያለቅስ ደረሰ፡፡ አለም፡- «በአላህ ይሁንብኝ! የአቡበክር አንድ ሌሊት ከዑመር እና ከዑመር ቤተሰቦች የተሻለች ነች፡ ፡»

እነኝህ በሁለቱ ሸይኾች መካከል ከነበሩት ልዩነቶች ናሙናዎች ናቸው፡፡ ሐሳቦች ተለያዩ፡፡ ልቦች አልተለያዩም፡፡ መንልጠያዋ በሰማይ ገመዶች ታስረዋልና ለምድር አፈር በሷ ላይ ሥልጣን አልኖራትም፡፡

በዑመር እና በዐሊይ መካከል

በዑመር እና በዐሊይ መካከልም ከፊል ልዩነቶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከፍ ባለ ሥርዓት ከበብ ነበር፡፡ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁ አንድ ጊዜ ባለቤቷ የሌለ ወደሆነች ሴት ወደቤቷ ሰዎች የሚገቡ ያንንም ጠሉ ወደሷ ላኩባት፡፡ ወደ ዑመር ነይ ተባለች፡፡ ዋ ጥፋቴ ለኔና ለዑመር ደግሞ ምን አለ አለች፡፡

እሷ በመንገድ ላይ እያለች ደነገጠችና ምጥ ያዛት፡፡ የሆነ ቤት ገባችና ልጇን ጣለች፡፡ ሕፃኑ ሁለት ጊዜ ጮኸና ከዚያ ሞተ፡፡ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓቦች አማከረ፡፡ ከፊላቸው ምንም የለብህም አሉት፡፡ አንተ ሥርዓት አስያዝ አስተዳዳሪ ነህ አሉት፡፡ ዐሊይ ደግሞ ዝም አሉ፡፡ ዑመር ወደሳቸው ዞሩና አንተስ ምን ትላለህ አሉ፡፡ ዐሊይ አሉ፡- «ይህን ነገር በግምት ተናግረውት ከሆነ ግምታቸው ተሳስቷል፡፡ አንተ በምትወደውም ነገር ብለውልህ ከሆነ አልመከሩህም ማለት ነው፡፡ ጉማው ባንተ ላይ ነው፡፡ ብዩ አስባለሁ፤ ምክንያቱም አንተ ነህ ያስደነገጥካት፡፡ ያስወረዳትም ባንተው ምክንያት ነው፡፡» ዑመርም የሕፃኑ ጉማ በዑመር ቤተሰቦች ላይ እንዲከፋፈል አዘዙ፡፡ እንደዚሁ ዑመር በዐሊይ አስተያየት ላይ ወረዱ - ረዲየሏሁ ዐንሁማ እሳቸው የአማኞች አዛዥ ሆነው በዐልይ የምርምር ውጤት ለመሥራት ምንም ነውር አላገኙም፡፡ በሌሎች አስተያየት ውስጥ ነፃነት ኖሮላቸው ሳለ፡፡

በዑመር እና በዐብዱሏህ ኢብን መስዑድ መካከል

ዐብዱሏህ ኢብን መስዑድ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባባዎች ሁሉ ይበልጥ ቁርኣን አንባቢ ነው፡፡ በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንናም ይበልጥ አዋቂያቸው ነው፡፡ ብዙ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባዎች ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ስለማይለይ ከሳቸው ቤተሰቦች እስከሚቆጥሩት ድረስ አቡ ሙሳ አል-አሽዐሪይ እንዲህ ይላሉ፡-

«ለብዙ ጊዜ ኢብን መስዑድንና እናታቸውን ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች እንጅ አይመስሉንም ነበር ከሳቸውም ላለመለየታቸው»

አቡ መስዑድ አል-በድሪይ አለ፡- «ወደ ዐብደላህ ኢብን መስዑድ የጠቆመ ሲሆን ሲመጣ አይቶት «ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ከሚመጣው ሰውዬ ይበልጥ አላህ ያወረደውን የሚያውቅ ከሳቸው በኋላ አንድም መተዋቸውን አላውቅም፡፡»

አቡ ሙሳም አሉ፡- «እኛ የራቅን ጊዜ ይኖር ነበር፡፡ የተጋረደብን ጊዜ ይፈቀድለት ነበር»

ዑመር ደግሞ በዕውቀታቸውና በደረጃቸው ታላቅነት ማን እንደሆኑ ይታወቃሉ፡፡ ኢብን መስዑድ ደግሞ በከፊል ሥራዎች አንዱ ሠራተኛ ነበሩ፡፡ ዐብዱላህ ዑመርን በብዙ ኢጅቲሃዶቻቸው ተስማምተዋል፡፡ የእስልምና ድንጋጌ ታሪክ ጸሐፊዎች ከሰሓባዎች ይበልጥ የዑመር ዕውቀት ተጽዕኖ የደረሰበት እስከቆጠሩት ድረስ በብዛት በምርምር (ኢጅቲሃድ) ይሰማው ነበር፡፡ በማስረጃ አወሳሰድ መንገዳቸውም እንደውም ዐብዱላህ ወደ ዑመር መዝሀብ ይመለስ ነበር፡፡ በከፊል የፊቅህ መስአላዎች በውርስ አያት ከወንድሞች ጋር የመካፈልን ጥያቄ ይመስል አንድ ጊዜ ወደ አንድ ሦስተኛ አንድ ጊዜ ደግሞ ወደ አንድ ስድስተኛ፡፡

ነገር ግን እነሱ በብዙ መስአላዎች ላይ ተለያይተዋል፡፡ በመካከላቸው ከተለያዩበት መስአላዎች መካከል፡-

ኢብን መስዑድ በሶላት ውስጥ እጃቸውን በታፋቸው መሃል ያደርጉ ነበር፡፡ በጉልበቶች ላይ ማስቀመጥን ይከለክሉ ነበር፡፡ ዑመር ደግሞ ይህን ያደርጉ ነበር፡፡ በታፋ ውስጥ ከማስገተባት ይከለክሉ ነበር፡፡

ኢብን መስዑድ ሰውየው ለባለቤቱ «አንቺ በኔ ላይ እርም ነሽ» ካለ መሓላ ነው የማለው ይሉ ነበር፡፡ ዑመር ደግሞ አንድ ፍቺ ፈታቷል ይላሉ፡፡

ኢብን መስዑድ ይሉ ነበር፡- በሆነች ሴት ላይ ዝሙት ፈጽሞ ከዚያ ያገባት ስለሆነ ሰውዬ፡- ባድ እስካሉ ድረስ ዝሙተኛ ከመሆን አይዘሉም፡፡ ዑመር ደግሞ ይህን አይቀበሉም፡፡ መጀመሪያው ዝሙት መጨረሻው ኒካሕ ነው ይሉ ነበር፡፡

ኢብኑል ቀይም «ኢዕላመል ሙወቂዒን» በተባለው መጽሐፉቸው ውስጥ አውስተዋል፡፡ ኢብን መስዑድ ከዑመር የተለያዩባቸው የፊቅህ መስአላዎች መቶ መስአላ ደርሰዋል፡፡ ከነሱም አራቶቹን ጠቅሰዋል፡፡ ከመሆኑም ጋር ይህ መለየያታቸው አንዱ ጓደኛውን ከመውደድ አላጎደለም፡፡ የትኛውቸውም ለሌላው ያለውን ክብርና ፍቅር አላደከመም፡፡ ይሀው ኢብን መስዑድ ሁለት ሰዎች ይመጡባቸዋል፡፡ አንዱ በዑመር ላይ የቀራ/ዑመር ያስተማረው ሌላው ደግሞ በሌላው ሰሓብይ ላይ የቀራ፡፡ ያ በዑመር ላይ የቀራው አለ፡- «ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ነው ያቀራኝ፡፡ ኢብኑ መስዑድ ሳቅ ሳቅ ብለው አለቀሱ፡፡ በእንባቸው ጠጠሩን እስከሚርሱ ድረስ፡፡ አሉም፡- ‹ዑመር እንዳቀራህ አንብብ፤ እሱ ለእስልምና ጠባቂ የሆነ ምሽግ ነበረና፡፡ ሰዎች ወደሱ የሚገቡና ከሱ የማይወጡ ዑመር በተመቱ ጊዜ ምሽጉ ተጣሰ»

አንድ ቀን ዑመር ተቀምጠቀው ሳለ ኢብኑ መስዑድ ይመጣሉ፡፡ እየመጡ ሲያጡዋቸው ዑመር አሉ፡- «ፊቅህ ወይም ዕውቀት የተሞላ ዕቃ» በሌላ ዘገባ ደግሞ «ዕውቀት የተሞላ ዕቃ ከቃድሲያ ሰዎች እመርጠዋለሁ» የዑመር ዕይታ ለኢብን መስዑድ እንዲህ ነበር - ረዲየሏሁ ዐንሁማ፡፡ በነዚያ መስአላዎች በመካከላቸው ልዩነቱ መገኘቱ ፍቅርንና ማክበርን እንጅ አልጨመረውም፡፡ ከነኝህ ክስተቶች የልዩነት ጉዳዮችን በማከም ማብረያት የሚሆኑን ሥርዓቶችን ማውጣጣት እንችላለን፡፡

በኢብን ዐብ-ባስ እና በዘይድ ኢብን ሣቢት መካከል

በሰሓባዎቹ መካከል ሪድዋኑሏሂ ዐለይሂም የነበረውን የልዩነት ሥርዓት ተጨማሪ እንድዳስስ/መለከት የልዩነት ጉዳዮችን እናቀርባለን፡፡ እንላለንም፡- ኢብን ዐብ-ባስ ረዲየሏሁ ዐንሁማ እንደ ሲድ-ዲቅ እና ብዙ ሰሓባዎችም ያምኑ ነበር፡፡ አያት በውርስ ላይ እንደ አባት ሁሉንም ወንድሞችና እህቶች ይጥላል ማለትን፡፡

ዘይድ ኢብን ሣቢት ደግሞ እንደ ዐሊይ እና ኢብን መስዑድ ከሰሓባዎች እንደ ሌሎችም ቡድኖች ሪዋድኑሏሂም ዐለይሂም አጅመዒን ከአያት ጋር ወንድሞችን ማውረስን ይመርጥ ነበር፡፡ አይጋርዳቸውም፡፡ አንድ ቀን ኢብኑ ዐብ-ባስ አለ፡- «ዘይድ አላህን አይፈራም፤ የልጅ ልጅን ልጅ አድርጎ የአባትን አባት አባት አያደርግም!» አለም እኔና እነዚህ ከኔ ጋር በግዴታ የሚለዩት ተሰብስበን እጆቻችንን በሩክን ላይ አድርገን ከዚያም ጸሎት አደርገን የአላህን እርግማን በውሸታሞች ላይ ባደረግን እመኛለሁ፡፡

እነዚህ የሰሓባዎች የፊቅህ ልዩነቶች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ የምናመጣቸውም ክፍተቱን ለማስፋትና ለልዩነት መሠረት ለመጣል አይደለም፡፡

ይልቁንስ የጠፉችንን ዕቃ ሥርዓቶችን መከታተል የሆነችውን ለማሳጠር የፊቅህ ልዩነቶቻችንን ለመፍታት ለኛ ሕይወት ዘይቤ እንዲሆንልን ከሰዎች ጋር ሰንዋዋል፡፡

በራሱ የምርምር ውጤት ትክክለኛነት መተማመኑ የዘይድ የምርምር ውጤት ስህተት መሆኑ እዚህ ያየነው ደረጃ ላይ ያደረሰው ኢብን ዐብ-ባስ ረዲየሏሁ ዐንሁማ አንድ ቀን ዘይድ ኢብን ሣቢትን እንስሳውን ሲጋልብ አየና እርካቡን ያዘለት፡፡ ዘይድም አለ፡- «አንተ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አጎት ልጅ ፈቅ በል፡፡» ኢብኑ ዐብ-ባስም አለ፡- «በምሁራኖቻችንና በታላላቆቻችን እንዲህ እንድናደርግ ታዘናል» ዘይድም አለ፡- «እጅህን አሳየኝ» ኢብን ዐብ-ባስም እጃቸውን አወጡ፡፡ ዘይድም ሳም አደረጋት፡፡ አለም፡- «በነብያችን ቤተሰቦች እንዲህ እንድናደርግ ታዘናል» ዘይድ ሲሞቱ ጊዜ ኢብን ዐብ-ባስ አሉ፡- «ዕውቀት እንደዚህ ነው የሚሄደው»

በበይሀቂ ዘገባ በሱነነል ኩብራ ውስጥ «የዕውቀት መሄድ እንደዚህ ነው፤ ዛሬ ብዙ ዕውቀት ተቀበረ፡፡» ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁ ለአስቸጋሪ መስአላዎች ከሙሃጂሮችና ከአንሷሮች ሊቃውንቶች ጋር የበድር ሰዎችና ሌሎችም ኢብን ዐብ-ባስን ይጠሩ ነበር፡፡

በእውነቱ በሰሓባዎች መካከል የልዩነት ጉዳዮችን ለመከታተል ብንሞክር በፊቅህ መስአላዎችና መዝሀባቸውን ሲያቀርቡ አካሄዳቸውንም ብዙ መጽሐፎችን በዚህ ጉዳይ እንጽፍ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ እዚህ ጋ ፍላጎታችን አይደለም፡፡ ናሙና ብቻ ነው የምናመጣው፡፡ የሰሓባ ትውልድ ያደገበትን ሥርዓት አሻግረን ለማየት በሁሉም ሁኔታ የልዩነትን ሥርዓት የቱን ያህል እንደሚይዙ ለማመላከት ያህል፡፡

በአላህ ዕውቀት ውስጥ ያለፈው ውሳኔ በተፈጸመ ጊዜ ታላላቅ ፈተናዎች ሲከሰቱ ጊዜ በሰሓባዎች መካከል የተከሰተው በተከሰተ ጊዜ ምክንያቶቹን ሁሉ አላህ (ሱ.ወ) ብቻ ለሚያውቃቸው አካባቢም የሆነ ከዋኞቿን ሁለ ያ ጉዳይ ሲከሰት ጊዜ በመካከላቸው ሰይፍ ሲወድቅ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ከነሱ የደረጃን ባለቤቶች ደረጃ አልረሱም፡፡ ታላላቅ ክስተቶችም ታላላቅ ፈተነማዎችም አላስረሷኋቸውም፡፡ ከነሱ የጥሩን ደረጃዎች ወይም መናቅብ ባለቤቶች

ይህ ዐሊይ ኢብን አቢ ጣሊብ መርዋን ኢብኑል ሐከም ስለነሱ እንዲህ ይላል፡- «አንድንም ከዐሊይ ይበልጥ የተከበረ ማሸነፍን የሚያሸንፍ አላየሁም፡፡ እሱኮ በጀመል ዕለት ወዳጃችን እንጅ አልነበረም፡፡ ተጣሪው ተጣራና .... ቁስለኛም አይገደልም»

ዒምራን ኢብን ጠልሓ በዐሊይ ላይ ይገባና ከጀመል ጦርነት ካበቁ በኋላ ይጋብዘውና ያቀርበዋል፡፡ ይላልም፡- «እኔ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ አላህ እኔንና አንተን ከነዚያ አላህ ስለነሱ ቀጣዩን አንቀጽ ያለው፡-

وَنَزَعْنَا مَا فِي صُدُورِهِم مِّنْ غِلٍّ إِخْوَانًا عَلَىٰ سُرُرٍ مُّتَقَابِلِينَ [١٥:٤٧]

«ባልጋዎችም ላይ ፊት ለፊት የሚቅጣጩ ወንድማማቾች ኾነው በደረቶቻቸው ውስጥ ከቂም ያለውን ሁሉ እናስወግዳለን፡፡» (አል-ሒጅር 15፡17)

ከዚያም የጠልሓን ቤተሰቦች እያንዳንዳቸው ከባሮቻቸውና ከልጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው መጠየቅ ጀመሩ፡፡ አንተ የወንድሜ ልጅ! እገሊት እንዴት ናት እገሊትስ እንዴት ነች የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረባነት ያላገኙ ከፊል በቦታው ላይ ያሉ ሰዎች ይገረማሉ፡፡ አንድ ሰው ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባዎች የመሆን ትርጉም አልገባቸውም፡፡ ሁለት ሰዎች በሰማኔ ዳርቻ ላይ ተቀምጠው እንዲህ ይላሉ፡- «አላህ ከዚህ ነገር ፍትሐዊ ነው፡፡ ትላንትና ገድለኋቸው ነገ በጀነት ውስጥ ወንድማማቾች ትሆናላችሁ?» ዐሊይ ይቆጡና ለተናጋሪዎቹ እንዲህ ይላሉ፡-

«ማነው ታዲያ እኔና ጦልሓ ካልሆንን ማነው ታዲያ?» ከፊል ሰዎች የሙእሚኖቹን አዛዥ ዐሊይን ረዲየሏሁ ዐንሁ ይጠይቃሉ ስለጀመል ሰዎች እነርሱ አጋሪዎች ናቸውን? አላህ ይውደድላቸውና ይላሉ፡- «ከሺርክ ወይም በአምላክ ከማጋራት ሸሽተው ነው ሙናፊቆች ናቸውን? አለ» ዐሊይ አላህ ይውደድላቸውና አሉ፡- «ሙናፊቆች አላህን በጥቂቱ እንጅ አያወሱትም» እነማን ናቸው ታዲያ እነሱ? ዐሊይም እንዲህ አሉ፡- «በኛ ላይ ድንበር ያላፉብን ወንድሞቻችን ናቸው፡፡ »

አንዳቸው የሙእሚኖችን እናት ዓኢሻን ረዲየሏሁ ዐንሃ በዐማር ኢብን ያሲር ዘንድ በመጥፎ ያነሳል፡፡ እንደሚታወቀው ዐማር ደግሞ የጀመል ዕለት ከሷ አቋም የተለየ አቋም ነበር የያዘው፡፡ አላህ ይውደድለትና ይላል፡- «ዝም በል አስቀያሚ ማስጠሌ ስትሆን የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ወዳጅ ታስቸግራለህ? እሷ በጀነት ውስጥ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት ነች ብዬ እመሰክራለሁ፡፡» እናታችን ዓኢሻ ረዲየሏሁ ዐንሃ ጉዞዋን በርግጥ ተጉዛለች፡፡ እኛ እሷ በዱንያም ሆነ በኣኼራ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት መሆኗን እያወቅን አላህ በሷ ፈተናን እሱን እንታዘዝ እሷ ለማወቅ»

ምን ዓይነት ሥርዓት ነው እንዲገኝ የሚጠበቀው ከዚህ በኋላ ጥሩዎቻቸው እንዲገናኙ አላህ ከሻባቸው ወንዶች? ነገር ግን ያ ከነብይነት መስኮት የጠጡት ብርሃን ጥላቻዎች ሊገቡባቸው ያቃቷቸው ልቦች ሲበራ ቆይቷል፡፡ በልዩነት እንዲህ ዓይነት ሥርዓት አመነጩልን፡፡ ለአላህ ምስጋና ይገባውና፡፡ አላህ

ጀልለ ሸዕኑሁ በበጎ ጊዜያቶች ሰዎች ውስጥ መለያየትና ሥርዓት ማጣተን አይሰበስብም፡፡

ዲራር ስለዐሊይ ያደረጉት ገለፃና የሙዓዊያ ማልቀስ

አቡ ኑዐይም ከአቡ ሷሊሕ ዘግበዋል፡፡ እሳቸውም አሉ፡- «ዲራር የደምራ ልጅ ኪናናዊ የሆነው ሙዓዊያ ባሉበት ገባ፡፡ ሙዓዊያም አለው፡- ዐሊይን ግለጽልኝ እስኪ» እሱም አሉ፡- አንተ የሙእሚኖች አዛዥ ይቅር አትለኝም? ይቅር አልልህም አለው፡፡ ካልቀረማ አለ «እሱ በአላህ ይሁንብኝ መጨረሻው ሩቅ ነው፡፡ ሀይሉ ጠንካራ ነው፡፡ ቁርጥ ይናገራል፡፡ በፍትሕ ይፈርዳል፡፡ ዕውቀት ከጎኖቹ ይፈልቃል፡፡ ከአቅጣጫው ጥበብ ይነገራል፡፡ ዱንያና አበባዋ አታሳስተውም፡፡ በሌሊትና በጨለማው ይደሰታል፡፡ በአላህ ይሁንብኝ! እንበ ብዙ ነው፡፡ ረጅም አስተዋይ ነበር፡፡ ሁለት መዳፎችን ይገለባብጥና ራሱን ያናግራል፡፡ ከልብስ የጠራውን ይወዳል፡፡ ከምግብ ደግሞ ወፈር ደረቅ ያለውን፡፡ በአላህ ይሁብንኝ! እንደ አንዳችን አጠገቡ የሄድን ጊዜ ያቀርበን ነበር፡፡ የጠየቅነውም ጊዜ ይመልስልን ነበር፡፡ ወደኛ ከመቅረቡ ጋር እናከብረውና እናናግረውም ነበር፡፡ ፈገግ ያለ ጊዜ እንደ ተሰካኩ ሉል ባለ ነበር፡፡ የሃይማኖት ሰዎችን ያከብራል፡፡ ድሆችን ይወዳል፡፡ ጠንካራ ሰው ከንቱን ተስፋ አያደርግም፡፡ ደካማ ደግሞ ከፊቱ ተስፋ አይቆርጥም፡፡ በአላህ እመሰክራለሁ! በከፊል አቋሞቹ በርግ አይቸዋለሁ፡፡ ሌሊቱ መጋረጃዎቹን ለቆ ከዋክብቶቹ ገብተው በክፍሉ ውስጥ ጺሙን ዐብጠ ሲገባ እባብ እንደተናደፈው ሰው ሲገለባበጥ ያዘነን ሰው ለቅሶ ሲያለቅስ ልክ እኔ አሁን ስል የሚሰማው ይመስለኛል፡- ጌታችን ሆይ! ጌታችን ሆይ! ወደሱ ተናንሶ በጸሎት እየታገለ ለዱንያም እያለ ለኔ ራስሽን አቀረብሽ፤ እኔን ተመለከትሽኝ፤ እጅግ በጣም የራቀ ነገር ነው፡፡ ከኔ ሌላ የሆነን ሰው አታልይ፤ ሦስቱንም ፈትቼሻለሁ፤ ዕድሜሽ አጭር ነው፤ መቀመጫሽ ወራዳ ነው፤ አልጋሽ ጥቂት ነው፤ አኽ አኽ የስንቁ ማነስ! የጉዞው መራቅ፣ የመንገዱ ጭርታ .... »

የሙዓዊያ እንባ በደረቱ ላይ ፈሰሰ፡፡ የማይቆጣጠረውም ሆነ፡፡ ሰዎቹም እንባ ተናነቃቸው፡፡ ሙዓዊያም አለ፡- «የሐሰን አባት እንደዚሁ ነበረ፤ አላህ ይማረውና በሱ ላይ ያለው ሐዘኔ እንዴት ነው አንተ ዲራር? አንድ ልጇ በጉያዋ እንደታረደባት ሴት ሐዘን እንባ የማይቆረጥ ሐዘኗ የማይሰክን ከዚያ ተነስቶ ወጣ»

በቅን የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምትኮች ጊዜ የነበረው የልዩነት ሥርዓት ባህሪዎች

የልዩነትን ጉዳዮች በምናቀርብበት ጊዜ ዝንባሌ የአንዱም ሰሓብይ ሪድዋኑላሂ ዐለይሂም አጅመዒን ፈረስ አለመሆኑን እንመከታለን፡፡ እነዚያ እነኝህን ሥርዓቶች የወለዱት ልዩነቶች ወደነሱ የገፋፋ ነገር ሐቅን ከመፈለግ ውጭ

አልነበረም፡፡ ይህ ቀጣዩ በሰሓባዎች መካከል ከነብይነትና ወሕይ ከተቋረጠበት በኋላ የነበረ የልዩነት ሥርዓት ምልክቶች ከብዙ በጥቂቱ እነሆ፡-

1/ እነሱ ማምለጫ ካገኙ ልዩነትን ይርቁ ነበር፡፡ እነሱ ልዩነት እንዳይኖር ሙሉ የሆነን ጉጉት ይጓጉ ነበር፡፡

2/ ስለልዩነቱ የሚያስፈቅዱት ምክንያቶች ባሉ ጊዜ በጉዳዩ ለሌላው ያልደረሰ ሱንና ለአንዳቸው መድረስን ይመስል ወይም ማስረጃውን በማስረዳት መለያየትን ይመስል ወይም በቃል በድንበሮች ላይ ቋሚዎች ነበሩ፡፡ እውነታውን ለመቀበል ይፋጠኑ ነበር፡፡ ስህተትንም በማመን ምንም ዓይነት ሀፍረት ሳይሰማቸው ከነሱ ለዕውቀትና ለደረጃ ለፊቅህ ባለቤቶች የበረታ ክብርም እንደነበራቸው ሁሉ ከነሱ አንዳቸው የራሱን ልክ አያልፍም፡፡ የሌላውን መብትም አይጋፋም፡፡ ከነሱ ሁላቸውም አስተያየት የጋራ መሆኑን ያምናሉ፡፡ እውነታው እሱ የሄደበት ሊሆን ይችላል፤ ይህ ነው እነሱ ጋ አመዛኙ፡፡ እውነታው ወንድሙ የሄደበት ሊሆን ይችላል፡፡ ያ ደግሞ እሱ ነው ተሸናፊው፡፡ እሱ በላጭ ነው፡፡ ብሎ ያሰበው ተበላጭ ከመሆን የሚከለክል ከልካይ የለም፡፡ እሱ ተበላጭ ነው ብሎ ያሰበው ደግሞ በላጭ ከመሆን የሚከለክል ነገር የለም፡፡

3/ በመካከላቸው የእስልምና ወንድማማችነት አሳሳቢ ከሆኑት ከኢስላም መሠረታዊ ነገሮች አንዱ መሠረት ነበረ፡፡ ያለሱ ለኢስላም መቆም የለውም፡፡ እሷም ከመለያየትና ወይንም ኢጅቲሃዳዊ ከሆኑ መሳኢሎች ላይ አንድ ከመሆን በላይ ነች፡፡

4/ እምነታዊ መሳኢሎች ልዩነት ከሚቀበሉት ነገሮች አልነበሩም፡፡ ልዩነቶች ቅርንጫፋዊ መሳኢሎችን አያልፉም ነበር፡፡

5/ ሰሓባዎች ሪድዋኑሏሂ ዐለይሂም ከዑሥማን ረዲየሏሁ ዐንሁ ኺላፋነት በፊት በመዲና ላይ ያጠሩ ነበሩ፡፡ ከነሱ ጥቂቶቹ መካ ነበሩ፡፡ ለጂሃድ እና መሰል ጉዳዮች በስተቀር አይለቁም ነበር፡፡ ከዚያም ይመለሳሉ፡፡ መሰብሰባቸው ይቀላል፡፡ ከብዙ ጉዳዮች ላይ አንድነታቸው ይረጋገጣል፡፡

6/ ቁራዎችና ፉቀአሆች እንደ ፖለቲካ መሪዎች ግልፆችና ታዋቂዎች ነበሩ፡፡ ሁሉም ተከራካሪ የማይከራከርበት የራሱ የሆነ ደረጃ ነበረው፡፡ ለሁሉም በደንብ ከሚችለው ፊቅህ አኳያም ዕውቅናው እንዳለ ሁሉ የማውጣጣት መንገዶቻቸውንና ስልቶቻቸው ግልጽ ከመሆኑ ጋር፡፡ በዚህ ላይ ውስዊ አንድነት የሚመሰል በመካከላቸው አለ፡፡

7/ ከፊላቸው በከፊላቸው ላይ በሚያደርጉት ነቀፋ የነበራቸው ዕይታ ነቀፋው ለወንድሙ የሚሰጠው ዕርዳታ ነው የሚል ነበር፡፡ ማነወር ወይም መተቸት አልነበረም፡፡

በታቢዒዮች ዘመን የነበረው ልዩነትና ሥርዓቱ

ከሙእሚኖች አዛዥ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁ ፖለቲካዊ ዕይታ ነበረ ለሰሓባዎች ሙሃጂሮቹም ሆኑ አንሷሮች ከመዲና ውጭ መኖር አለመፍቀድ፡፡ እነሱ ሁልጊዜ ከመዲና ውጭ ለዘመቻ የሚሄዱ መንገደኞች ወይም ለማስተማር ወይም ዳኝነት ለመሾም ወይም ከዚህ ሌላ ላሉ ጉዳዮች ከዛ በኋላ መዲና መረጋጊያቸውና መኖሪያቸው ሆና ትቀጥላለች፡፡ እሷ የሀገሪቱ ዋና ከተማ ነች፡፡ የኺላፋውም መሠረት ነች፡፡ እነሱ የእስልምናን መልዕክት ተሸካሚዎች ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ቡድኑ ናቸው፡፡ ወደኸሊፋው ቅርብ ቦታ ላይ መኖራቸው የግድ ይላል፡፡

በግዴታዎቹ ላይ አጋዦች ሆነው በሁሉም የኡምማው ጉዳዮች ተጋሪዎቹ ሆነው፡፡ ዑሥማን በተሾሙ ጊዜ ከሰሓባ መዲናን መልቀቀቅ ለሚሻ ሁሉ በመፍቀዱ ችግር አልታያቸውም፡፡ ወይም ከኢስላም ሀገሮች የሻበት ቦታ ለመኖር የሰሓባ ፉቀሀአዎችና ቁረአዎች ወደተከፈቱት ከተሞች ተበታተኑ፡፡ ሁለቱን ከተሞች (በስራና ኩፋን) ከሦስት መቶ በላይ የሚሆኑ ሰሓባዎች ኖሩባቸው፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሑነይን ዘመቻ ከተመለሱ በኋላ በመዲና ውስጥ አስራ ሁለት ሺ ሰሓባዎችን ትተዋል ማለት በርግጥ ተዘግቧል፡፡ ከነሱ በመዲና ውስጥ እሳቸው እስከሚያልፉ ድረስ አስር ሺ ቀርተዋል፡፡ ከነሱ ሁለቱ ሺ በከተሞች ተሰራጭተዋል፡፡

የፉቀሀአችና የቁራአዎች ዕውቀትና ፊቅሀ ከሰሓቦች ከነሱ በኋላ በርግጥ ተሸከመዋል፡፡ ከታቢዒዮቹ ከነሱ የተማሩት በመዲና የዑመር ዘጋቢ የፊቅሁ ተሸካሚ ተብሎ የሚታሰበው ሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብን ይመስል፡፡

በመካ ዐጣእ ኢብኑ አቢ ረባሕን ይመስል፡፡ በየመን ጣውስን፣ በየማማ የሕያ ኢብኑ አቢ ኩሢር፣ በበስራ ሐሰንን፣ በሻም መክሑልን፣ በኹራሳን ዐጣእን፣ በኩፋ ዐልቀማን እና ሌሎችንም ይመስል፡፡

እነኝህ በብዛት ፈትዋንና ኢጅቲሃድን በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባዎች ዘንድ የሚያደርጉ ነበሩ፡፡ እነዚያ ዕውቀትንና ፊቅሀን ከነሱ የወሰዱት በጆቻቸው ያደረጉት በሥርዓቶቻቸው የሠለጠኑት በማውጣጣት ስልቶቻቸው ለውጥ የፈጠሩባቸው ናቸው፡፡ የተለያዩ ጊዜ ሰሓባዎች የልዩነት ሥርዓቶች አልወጡም፡፡ ያቺን ታሪክም

አላለፉም፡፡ እነዚያ እነሱ የኡምማው ብዙኃኖች በነሱ ለውጥ ያገኙባቸው የብዙኃኑ ፈቀሀአዎች ናቸው፡፡ ፊቅህንም ከነሱ ነው የተማሩት፡፡

ያንን ሥርዓት ከሚገልጽ ነገር እነዚያ (በዲያ) በጉማ ጉዳይ ላይ የተደረጉ ሁለት ውይይቶች ናቸው፡፡ ዐብዱር-ረዛቅ ዘግበዋል፡፡ በሻዕቢ መንገድ እሳቸው አሉ፡- «አንድ ሰው ወደ ሹረይህ መጣና ስለጣቶች ጉማ ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም አሉ፡- በእያንዳንዱ ጣት አስር ግመል አለበት፡፡ ሰውየው ለአላህ ጥራት ይገባውና ይቺና ይቺ እኩል ናቸው አለ፡፡ (ወደ አውራ ጣትና ትንሽዋ ጣት እየጠቀሰ ሲሆን)» ሹረይህም አለ፡- «ወዮልህ! ሱንና ግምትን ከልክላለችና ተከተል አትፍጠር፡፡»

ማሊክ በሙወጣእ ውስጥ ከራቢዓ ዘግበዋል፡፡ ሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብን በሴት ጣት ጉማው ስንት ነው ብዬ ጠየኩት አለ፡፡ አስር ነው አለኝ፡፡ በሁለት ጣትስ አለኝ፡፡ ሀያ ግመል ነው አለ፡፡ በሦስት ጣትስ አለ፡፡ ሠለሣ ነው አለ፡፡ በአራትስ አልኩት፡፡ ሀያ ነው አለኝ፡፡ ቁስልዋ ሲያድግ. መከራዋ ሲጠና ጉማዋ ጎደለ አልኩኝ፡፡ ሰዒድ ደግሞ አለ፡- «አንተ ኢራቃዊ ነህ? ረቢዓ አለ» ይልቁንስ የሚያጣራ ምሁር ወይም ተማሪ መይም ነኝ ሰዒድ አለ፡፡ አንተ የወንድሜ ልጅ ሆይ! ሱንናው እንዲህ ነው፡፡ ጉዳዩ እዚህ ድረስ ያበቃል፡፡ አንዱ ወገን ሳይሞቅና ሌላውን ወገን በመሀይምነት ሳይወነጅል ወይም ለራሱ እውነታውን ማግኘቱን ሳያስብ ከሱ ሌላ ያሉት ከንቱ ነው ሳይል፡፡

የሰዒድ እና የሒጃዝዮች ምርጫ የሴት ጉማ እንደ ወንድ ጉማ ነው፡፡ የሱ ጉማ አንድ ሦስተኛው ላይ እስከሚደርስ ከአንድ ሦስተኛው የጨመረ በሱ ውስጥ የሷ የጉማ የወንድ ጉማ ግማሽ ይሆናል፡፡ ይህም ዐም ኢብኑ ሹዐይብ ካባቱ ከአያቱ ለዘገበው ዲሥ ነው፡፡ «የሴት ጉማ እንደ ወንድ ጉማ ነው፡፡ ከሷ ጉማ አንድ ሦስተኛው ላይ እስከሚደርስ ድረስ፡፡»

የዒራቆ ምርጫ/መዝሀብ ደግሞ የሷ ጉማ መጀመሪያውኑ የወንድ ጉማ ግማሽ ነው፡፡ ሸዕቢ (ዓሚር ኢብኑ ሹራሒል አል-ኩፊ) ከአንድ ሰው ጋር በቂያስ ጉዳይ ላይ ተከራከሩ፡፡ አለውም አል-አሕነፍ ኢብኑ ቀይስ ቢገደልና አብሮት ትንሽ ሕፃን ልጅ ቢገደል ጉማቸው እኩል ይሆናል ወይስ አል-አሕነፍ እንዲበልጥ ይደረጋል፡፡ ሰፊ አዕምሮና ጠንካራ ቻይነት ስላለው? ሰውየው አለ፡- «ይልቁንስ እኩል ነው የሚሆኑት» እንግዳውስ ቂያስ ምንም አይደለም ማለት ነው፡፡

አውዛዒ ከአቡ ሐኒፋ ጋር በመካ ተገናኙ፡፡ አውዛዒም አሉ፡- ምን ሆናችሁ ነው እጆቻችሁን የሩኩዕ እና የሱጁድ ጊዜ የማታነሱት? አቡ ሐኒፋ አሉ፡- በዚህ ጉዳይ ላይ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በትክክል የመጣ የለም፡፡ አውዛዒም አሉ፡- «እንዴት እንዲህ ይባላል ዙህሪ ከሳሊም ከአባቱ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አውርቶኝ እያለ

እሳቸው ሁለት እጆቻቸውን ሶላት ሲከፍቱና ሩኩዕ ሲወርዱ፣ ከሩኩዕ ሲነሱ ያነሳሉ ብሎ አቡ ሐኒፋም አሉ፡- ሐማድ ከኢብራሂም ከዐልቀማ እና ከአስወድ ከኢብኑ መስዑድ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሁለት እጃቸው ሶላትን ሲከፍቱ እንጅ አያነሱም ነበረ፤ ከዚያ ለምንም አይመለሱበትም ነበረ፡፡ አውዛዒም አለ፡- እኔ ከዙህሪ ከሳሊም ከአባቱ አወራለሁ፡፡ አንተ ደግሞ ሐማድ ከኢብራሂም አወራኝ ትላለህ? አቡ ሐኒፋም አሉ፡- ሐማድ ከዙህሪ ይበልጥ ፊቅህ የሚያውቅ ነበር፡፡ ኢብራሂም ደግሞ ከሳሊም ይብልጥ ፊቅህ አዋቂ ነው፡፡ አልቀማ ደግሞ ከኢብኑ ዑመር አይተናነስም፡ ፡ ኢብኑ ዑመር የሰሓብይነት ብልጫ ቢኖረውም እንኳ አስወድ ደግሞ ብዙ ትሩፋቶች አሉት፡፡ ዐብደላህ ደግሞ እሱ ዐብደላህ ነው፡፡ አውዛዒ ዝም አሉ፡፡» ከአቡ ሐነፋ ተዘግቧል፤ እሳቸው ብለዋል፡- «ይህ እኛ ያለንበት ጉዳይ አስተያየት ነው፡፡ አንድንም እሱን በመቀበል አናስገድድም፡፡ አንልምም እሱን መቀበል ግዴታ ነው፡፡ በማስገደድ ከርሱ የተሻለ ነገር አጠገቡ ያለ ሰው ያምጣው»

ሁሉም ይከተለዋል፡፡ ሱንና ትክክል ስትሆን አንድም አይነቅፉትም፡፡ ከተገኘም በአረዳድ ልዩነት ነው፡፡ አንዱ ለሌላው የሚረዳውን ይሰጣል፡፡ ቃሉ እስካሰማቸው ድረስ ሁለቱም ቡድኖች ዘንድ የሚቃረነው ትክክለኛ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ፡፡

የፖለቲካዊ ግጭት ተጽዕኖ በእምነታዊና ፊቅሃዊ ልዩነቶች

ሳንጠቅስ ከምናልፋቸው ጉዳዮች ከልዩነቶች ያወሳነው የኡምማው ብዙኃን ተጨባጭ ጉዳይ ነበር፡፡ የአያሌው ብዙኃን ነበር፡፡ ልዩነቶችም የፊቅሃዊ ጉዳዮችን አያልፉም ነበር፡፡ ያቺ የምትደከምና የምትወገድ ከቁርኣንና ከሱንና የሆኑ አስመሳዮች ሁሉ በላይ የሚሆኑ ወደሆኑ ማስረጃዎች በሚመለሱበት ጊዜ ሁሉም ለሐቅ ታዛዥ ይሆናል፡፡

ነብያዊ በሆነው በተከበረው ሥርዓት ጥላ ሥር የግጭቱ ምክንያት እንዳልነው በጉዳዩ ለአንዱ ሱንና አለመድረስ፣ ለሌላው ደግሞ መድረስ ወይም ማስረጃ በመረዳት መለያየት፣ ወይም በቃል ከመሆን አይዘልምና፡፡ ነገር ግን እዚያ ጋ አዲስ የተገኘ ሌላ ጉዳይ አለ፡፡ እሱም የሦስተኛውን ኸሊፋ ዑሥማን ረዲየሏሁ ዐንሁ መገደል ፈተና ተከትሎ የመጡት ፖለቲካዊ ልዩነቶች ናቸው፡፡ እንዲሁም የኺላፋው ወደ ኩፋ መሸጋገር ከዚያም ወደሻም ከታላላቅ ክስተቶች በዚህ መሃል የተከሰተውም እነኚህ ክስተቶች ወደልዩነት ክበብ ሌሎች በውጭ የነበሩትም ጉዳዮችም አስገብቷል፡፡ የሀገሩ ወይም ከተማው ሁሉ ሰው ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና የደረሳቸውን ለመሞጨጭና አያሌዎቹ ከተሞች ሰዎች ዘንድ የተለየ በጥኝቃቄ የተሞላ ዕይታ ለማየት አግዟል፡፡ በብዙኃኑ ፖለቲካ ድጋፍ ወይም ተቃውሞ

ሁኔታዎች ተጽኖ ያደርጉበታል፡፡ ኢራቅ ደግሞ በታላላቅ ሁለት ከተሞቿ (በኩፋና በበስራ) ለፖለቲካ አመለካከቶች መብላላትና ውስብስብነት ወደተለያዩ አቅጣጫዎችም ለማረመድ ምቹ አካባቢ ተደርጎ ተይዞ ነበር፡፡ በሱ ውስጥ ሺዓ ተነሳ፡፡ ጀሚዒያ እና ሙዕተዝላም ግልጽ ሆኑ፡፡ ኸዋሪጆችም ተሠራጩ፡፡ በርካታ የዝንባሌና የፈጠራ ሰዎችም እንደዚሁ የውሸት ሐዲሥ መቅጠፍም ተጀመረ፡፡ የፖለቲካዊ ዓላማ ያላቸው ተረቶችም መከወን በሰው አንደበቶችም ፉክክሮች መኖር ተጀመረ፡፡

ኢማሙ ማሊክ ስለኩፋ (እሷ የፉክክር ሀገር ናት) ብለዋል፡፡ ዙህሪም አሉ፡- ሐዲሥ ከኛ ጋ ስንዝር ሆኖ ይወጣል፡፡ በኢራቅ ክንድ ሆኖ ይመለሳል፡፡ እነዚህ ነገሮች ኢራቃዉያን ፉቀሀአዎችን እራሳቸው ጥያቄዎችን እንዲይዙ፣ ሱንናዎችንና አከባሮችን ለመቀበል መስፈርቶችን እንዲያኖሩ አድርጓቸዋል፡፡ ከበፊታቸው የነበሩት ሰዎች ዞር ብለው የማያዩትን - ያም የሆነበት ምክንያት ዲናቸውን የሚያበላሽ ነገር ከዝንባሌና ከፈጠራ ከሚበጣበጡ ቡድኖች አስተሳሰብ ወደፊቂሃቸው እንዳይገባ አስበው ነው፡፡ ከኢራቃዉያን ውጭ የሆኑ እነዚያ ከኢራቃዉያን ሐዲሥ ለመውሰድ ስጋት መጨረሻው ያደረሳቸውንስ ምን ትላለህ?

የሒጃዝ ሰዎች እስከሚያስቡ ድረስ ኢራቃዉያንን ወይም የሻማዉያንን ሐዲሥ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሒጃዞች ዘንድ መሠረት ከሌለው፡፡

ከሒጃዝ ዑለማዎች ለአንዱ እንዲህ ተባለ፡- «የሱፍያን አስ-ሠውሪ ሐዲሥ ከመንሱር አል-ሙእተምር ከኢብራሂም አን-ነኻዒ ዐልቀመተል ነኻዒ ከዐብደሏህ ኢብኑ መስዑድ .... ሰንሰለቱ ይህ የሆነ ኢስናድ ላይ ምን አስተያየት አለህ እሱ ደግሞ በኢራቃዉያን ዘንድ ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ ኢስናድ ነው? አለ» በሒጃዝ መሠረት ከሌለው አልቀበልም፡፡ ዐብ-ባስ ረቢዓ ኢብኑ አቢ ዐብዱር-ረሕማንን ሚኒስተርና አማካሪ አድርጎ ያዘው፡፡ እሱም የመዲና ሰው ነው፡፡ ይቅርታ እንዲያደርግለት ጠየቀውና ከአጭር ጊዜ በኋላ ወደ መዲና ተመለሰ፡፡ አሉትም፡- ኢራቃዉያንና ሰዎቿን እንዴት አየህ? አለም እሱ፡- የኛ ሐላል (የተፈቀደ ነገር) የነሱ ሐራም (እርም የሆነ) የኛ ሐራም ደግሞ የነሱ ሐላል የሆኑ ሰዎችን አየሁ፡፡ በሷ ውስጥም በዚህ ዲን ላይ ተንኮል የሚሠሩ ከአርባ ሺ በላይ የሆኑ ሰዎችን ትቼ መጥቻለሁ፡፡ ከሳቸውም ቀጣዩ አባባል ተዘግቧል፡- «ልክ ወደኛ የተላከው ነብይ ወደነሱ ከተላከው ነብይ የተለየ ይመስላል፡፡ እነዚህ አባባሎች የታሰበባቸው በኢራቅ ያሉት የዝንባሌና የፈጠራ ሰዎች ቢሆኑ በኢራቅ ያሉ የሱንና ሰዎችና ብዙኃኖቻቸው ባይሆኑም ነገር ግን በፊቅህ እንቅስቃሴ መጨረሻቸው የራቀ ተጽዕኖ ያላቸው ከፊል ጉዳዮች ግልጽ የሆነ ጥቆማ አላቸው፡፡ እንዲሁም የሁለቱ

ሀገሮች ፉቀሀእ አቋሞችንና የማውጣጣት መንገዶቻቸውና ስልቶቻቸውን ያመለክታሉ፡፡ የሒጃዝ ሰዎች ሱንናን በደንብ ሸምድደናል፡፡ ከሷም ምንም አላመለጠንም ብለው ያስባሉ፡፡ መዲና በውስጥዋ አስር ሺ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባዎች ከሑነይን ዘመቻ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እዛው የተዋቸው እስከ ዕለተ ሞታቸው የኖሩባት ነበሩ፡፡

ዑመር ኢብኑ ዐብዱል ዐዚዝ ወደ ከተሞች ሰዎች ሱንናንና ፊቅህን ሊያስተምሯቸው ይጹፉላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን እሱ ወደመዲና ሰዎች ሲጽፍ ያለፈውን ሲጠይቋቸው አጠገባቸው ያለውን ሱንና ወደሌሎቹ እንዲልክ እንዲያሳውቁት ነበር የሚጽፈው፡፡ በመዲና የሰሓባን ሐዲሥና ፊቅህን ንግግራቸውንም ጭምር ተሸካሚ/አዋዋ ሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብና እነዚያ ማሊኪያና ሻፊዒያ፣ ሐናቢላ ዟሀሪያና ሌሎችም ከነሱ ላይ የተማሩ ባልደረቦቹ ነበሩ፡፡ ከታቢዒዮች የመዲና ዑለሞች ወይም ምሁራኖች በእጃቻቸው ያሉት ሱንናዎችና የሰሓባ አሠሮች የፊቅህን ፍላጎት ለማሟላት በቂ ናት ብለው ያስባሉ፡፡

አስተያየትን በሁሉም ዓይነቶቹ ለመያዝ የሚያስገደድ ምንም ነገር የለም፡፡ ከፊላቸው ከዚህ በተቃራኒ በሚያይበት ጊዜ አስተያየትን ይይዛል፡፡ በሱው እስከታወቀ ድረስ ቅፅል ስምም ሆኖ እስከተጠራበት ጊዜ እንደ ረቢዐሀ ኢብኑ ዐብዲረሕማን የማሊክ ሸይኽ የሆኑት ያ ረቢዐቱ ረዕይ» የሚል ቅፅል ስም ያገኙት ነገር ግን አድፊና አመዛኝ የሆነው ብዛት ለሱንናና ዐሰር ዑለማኦች ነበር፡፡

ኢራቆችማ እንደ ኢብራሂም አን-ነኻዒና ባልደረቦቹ ከሱንናዎች ዕድላቸው ቀላል አይደለም ያስቡ ነበረ፡፡ ከሰሓባዎች ብዙ ቁጥር ሦስት መቶን ያለፈ በርግጥ በመካከላቸው ኖሯል፡፡ አብዛኞቻቸው ከፊቀሀአዎች ነበሩ፡፡ በግንባር ቀደማቸው ዐበደላህ ኢብኑ መስዑድ ያ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባዎች ይበልጥ የአላህን መጽሐፍ የሚያውቀው ይገኝበታል፡፡

በኸሊፋነታቸው ጊዜ ውስጥ ዐሊይም ረዲየሏሁ ዐንሁ በመካከላቸው እንደሚገኙበት አቡ ሙሰል አል-ዐሽዐሪ እና አማርም ሌሎችም፡፡ ኢብራሂም አን-ነኻዒ አብሮት የኢራቅ አብዛኞቹ ምሁራኖች አሉ፡፡ ሁላቸውም ያስቡ ነበር - የሸሪዓ ሕግጋቶች ምስጢራቸው የታወቀ ነው፡፡ የባሮቹ ጥቅሞች ያሉበትን ጉዳይ ያካተቱ ናቸው፡፡ እነሱም በጠንካራ መሠረቶች ላይ ተገንብተዋል፡፡ እናም እነዚያን ድንጋጌዎችና ጥቅሞች ጠባቂ በሆኑ ከቁርኣንና ከሐዲሥ የሚታወቁ ምክንያቶች ቅርንጫፋዊ የሆኑት ሕግጋቶች ለነዚያ ጥበቦች ተብለው ነው የተደገጉት፡፡

ፊቅህ ማለት እሱ ያ ሕግጋቶች የተደነገጉበትን ጥበቦች የሚያጠና፣ ዓላማዎቿን የሚረዳ ነው፡፡ ሕግጋቶችን በመኖርም ሆነ ባለመኖር ከጥበቦቻቸው ጋር የተሳሰሩ ለማድረግ፡፡

የዒራቅ ዑለማዎች እንደሚያስቡትም ሁሉ የሸሪዓ ማስረጃዎች አላቂዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ክስተቶች አያልቁም፡፡ ማስረጃዎች ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በመሞታቸው ተቋርጠዋል፡፡ በቁርኣንና በሐዲሥ የተደነገጉ መመሪያዎች ጥበቦች ካልተስተዋሉ በሰዎች ዘንድ የሕግጋትን ፍላጎት መግታት አይቻልም፡፡

ከሐሰን የዑበይዱላህ አን-ነኻዒ ልጅ ተወራ፡- ለኢብራሂም አን-ነኻዒ አልኩት አለ፡- ይህን ፈትዋ ሲታደርግበት የሚሰማህን ሁሉ ሰምተሀዋል? አይደለም አለ፡፡ ባልሰማህው ነገር ፈትዋ ታደርጋለህ እንዴ? አልኩት፡፡ ሰምቻለሁም፤ ያልሰማሁትም ደግሞ መጣልኝ፡፡ በዚያ በሰማሁት ላይ ገመትኩኝ፡፡ ያቺ የዒራቅ ት/ቤት ነበረች፡፡ አሠር ከጠፋ አስተያየት ነበረ፡፡

ሰዒድ ኢብኑ መሰይብ እና የመዲና ዑለማዎችማ ለምክንያቶቹ ትኩረት አይሰጡም ነበር፡፡ ወደማስረጃው ወይም ወደሰሓባ ንግግር መድረስ ሲያቅታቸው እንጅ፡፡ እንዴት ሊያቅተውስ ይችላል እሱ እያለ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ፍርድን አልፈረዱም፤ አቡበክርም ዑመርም ዑሥማንም ዐሊይም እኔ ያወኩት ቢሆን እንጅ!

የመዲና አካባቢ እንዳልመጣባትም ሁሉ ከመለዋወጥ በዒራቅ አካባቢ ላይ እንደመጣው ከክስተቶችም በውስጧ አልተከሰተም በዒራቅ የተከሰተው፡፡ ስለዚህም ከመዲና ዑለማዎች ብዙዎቹ አንዳቸው ስለሆነ ነገር ሲጠየቁ የተሰማ ነገር ካለው ይመልሳሉ፡፡ አለዚያም አላውቅም ይል ነበር፡፡

መስሩቅ ስለሆነ መስአላ ተጠየቁና አላውቅም አሉ፡፡ በግምት ገምትና ንገረን አሉት፡፡ እግሬ እንዳትንሸራተት እፈራለሁ አለ፡፡

የመዲና ሰዎች አሠር በሌለበት ጉዳይ በአስተያየት ከመናገር መፍራታቸውን ከሚገልጽ ነገር ኢብኑ ወህብ የተናገሩት ነው፡፡ ማሊክ እንዲህ አለ፡- «ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የሙስሊሞች መሪ የዓለማት ዓይነታ ሆነው ስለሆነ ጉዳይ ይጠየቃሉ፡፡ ከሰማይ ወሕይ እስከሚወርድላቸው ድረስ አይመልሱም ነበር፡፡ የዓለማቱ ጌታ መልክተኛ በወሕይ እንጅ የማይመልሱ ከሆኑ ከታላቅ ድፍረት ይቆጠራል፤ በአስተያየቱ ወይም በቂያስ ወይም ጥርጣሬውን በሚያሳምርበት ሰው በመከተል ወይም በልምድ ወይም በባሕል ወይም በፖለቲካ ወይም በስሜት ማጣመም ወይም በመገለጽ ወይም በእንቅልፍ ልብ ወይም ነገሩን በጥሩ አድርጎ

በመቁጠር ወይም በመገመት የመለሰው መልስ አላህ ብቻ ነው እርዳታ የሚለመነው፤ ወይም በሱ ላይ ብቻ ነው መመካት፡፡»

ልዩነቱ በሁለቱ ት/ቤቶች መካከል የተሟሟቀ ከመሆኑ ጋር በሁለቱ ቡድኖች መካከል ሕያሴ መለዋወጥ ከመገኘቱ ጋር ከሁለታቸው የትኛውም ከመለየያት ሥርዓት አልተወገደም፡፡ ካለፉት ክርክሮች እንደተገለጸልን ሁሉ በሁለቱ ት/ቤት ሰዎች መካከል ከተካሄዱት ብዙ ክርክሮች በተጨማሪ ከነሱ አንዱም ከልዩነት ሥርዓት ድንበሮች አልወጣም፡፡ በከሀዲነት መመደብ የለም፡፡ በአመጸኝነትም አስቀያሚ በሆነ ፈጠራ በመወንጀልም ማግለልም አልነበረም፡፡

ከአቡ ሹብሩማ ተወራ፡፡ እሱም አለ፡- እኔና አቡ ሐኒፋ የጀዕፈር ኢብኑ ሙሐመድ ኢብኑል ሐነፊያ ላይ ገባን፡፡ ሰላም አልኩትም፡፡ ጓደኛውም ነበርኩ፡፡ ከዚያም ወደ ጀዕፈር ዞርኩና አልኩትም አላህ ያጣቅምህና ይህ ከዒራቅ ሀገር የሆነ ሰው ነው፡፡ ዕውቀትና ሰፊ አዕምሮም አለው፡፡ ጀዕፈር አለኝ፡- ያ ሃይማኖቱን በአስተሳሰቡ የሚገመግመው ሊሆን ይችላል? ከዚያም አለ ኑዕማን ነው እሱ? አቡ ሐኒፋም አሉ፡- አዎ አላህ ያሳምርህና፡፡» ጀዕፈርም አለ፡- አላህን ፍራ፤ ሃይማኖቱን በአስተሳሰብህ አትገምግም፡፡ የመጀመሪያ ቂያስ ያደረገው ኢብሊስ ነው፡፡ አላህ ለኣደም ሱጁድ በማድረግ ያዘዘው ጊዜ አለም፡- እኔ ከሱ የተሻልኩ ነኝ፡፡ ከእሳት ፈጠርከኝ፡፡ እሱን ደግሞ ከጭቃ ፈጠርከው» ከዚያም አቡ ሐኒፋ አሉ፡- እስኪ ንገረኝ መጀመሪያዋ በአላህ መጋራት፣ መጨረሻዋ ማመን ስለሆነችዋ ቃል? አቡ ሐኒፋ አላውቅም አሉ፡፡ ጀዕፈር አሉ፡- እሷ ከአላህ በቀር በእውነት የሚያመልኩት የለም «ላ ኢላሀ ኢለላህ» ነች፡፡ በእውነት የሚያመልኩት የለም፤ ላ ኢላሀ ቢልና ከዚያም ቢተው ከሀዲ ይሆናል፡፡ ይቺ መጀመሪያዋ በአላህ ማጋራት መጨረሻዋ ደግሞ በአላህ ማመን የሆነች ቃል ነች፡፡ ከዚያም አቡ ሐኒፋ አሉ፡- ወዮልህ! በአላህ ዘንድ የትኛው ነው ይበልጥ ታላቁ አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ መግደል ወይስ ዝሙት መሥራት? ይልቁንስ ነፍስ መግደል ነው እንጅ አሉ ጀዕፈር፡፡ ጀዕፈርም አሉ፡- አላህ ነፍስ በመግደል ጉዳይ ላይ ሁለት ምስክሮችን ተቀብሏል፡፡ በዝሙት አራትን እንጅ አልተቀበለም፡፡ ቂያስ እንዴት ይቆምልሃል? ከዚያም አሉ፡- በአላህ ዘንድ የትኛው ነው ታላቁ ፆም ወይስ ስግደት አሉ፡፡ ይልቁንስ ሶላት ነው እንጅ አሉ፡፡ ታዲያ ለምንድነው ሴት የወር አበባ ስታይ ፆምን ቀዷ አውጥታ ሶላትን ቀዷ የማታወጣው? አንተ የአላህ ባሪያ አላህን ፍራ ቂያስ አታድርግ፡፡ እኛ እኮ ነገ እኔም አንተም አላህ ፊት እንቆማለን፡፡ እኛ እንላለን አላሁ ዐዝ-ዘ ወጀል አለ፡- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አሉ፡፡ አንተና ባልደረቦችህ ደግሞ ትላላችሁ፡፡ ይህን ቂያስ አድርገን መስለን አላህ ደግሞ በኛም በናንተም የፈለገውን ይሠራል፡፡ የኢማሙ

ጀዕፈር ጥያቄዎች አንድ እንደ አቡ ሐኒፋ የሆነ ሰው ከመመለስ አያቅተውም፡፡ ነገረ ግን ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች ጋር ያለው ሥርዓት እሱ ነው ዝም እንዲሉ ያደረጋቸው፡፡

ካለፉት ክርክሮች ወይም ውይይቶች ከፍ ያለው ነብያዊ ሥርዓት ነው፡፡ የተወያዮች ምንጭ ነበር ማለትን እንረዳለን፡፡ ልዩነትም በወንድማማቾች መካከል ከመገናኘት የሚጋርዱ መጋረጃዎችን አልገነባም፡፡ ስለዛች ጊዜ የታሪክ ጸሐፊዎች ጭካኔ (ጊልዛ) ካንዱ አንዱ የተቀባበሉት አብዛኛው በፍልስፍና ቡድኖች መካከል የሚገኝ ነበር፡፡ እነዚያም ልዩነቶቻቸው ወደ እምነታዊ ጉዳዮች የደረሱ ከፊሎቹ ለራሳቸው ሌሎችን በክህደትና በአመጽ በፈጠራ እስከመፈረጅ ፈቅደው ነበር፡፡ በነኚህ ቡድኖች ውስጥም ቢሆን የታሪክ ገጾች መመዝገቡ የሚቻል የልዩነት ሥርዓት ሳያገኙ አልቀረም፡፡

ኢብኑ ዐብ-ባስ ከኸዋሪጆች ጋር ያደረጉት ክርክር

ከዐብደላህ ኢብኑል ሙባረክ ተወራ፡- አለ፡- «ኢክሪማ ኢብኑ ዑመር አወራን፡፡ ሰማክ አል-ሐነፊ አወራን አለ፡፡ ኢብኑ ዐብ-ባስ ሲል ሰማሁት ዐሊይ አለ ኸዋሪጆችን እስከሚወጡ ድረስ አትዋጉዋቸው፤ እነሱ ይወጣሉ አለ፡፡ አልኩኝ አንቱ የአማኞች አዛዥ፡- አቀዝቅዘው ይሰገዱ፤ እኔ በነሱ ላይ ገብቼ ንግግራቸውን መስማት እፈልጋለሁ፡፡ አናግራቸዋለሁም አለም፡፡ ከነሱ እፈራልሀለሁ፡፡ ኢብኑ ዐብባስም አሉ፡- አንድንም ሰው የማላስቸግር ባህሪ ያለኝ ጥሩ ሰው ነበርኩኝ አለ፡፡ የየመን ልብሶችን በጥሩ ሁኔታ ለበስኩኝ፡፡ ፀጉሬንም አበጠርኩ፡፡ ከዚያም እነሱ ቀይሉላ በተኙበት ገባሁባቸው፡፡ አሉኝም ይህ ልብስ ደግሞ ምንድነው? ቁርኣን አነበብኩላቸው፡፡ «የአላህን ጌጥ ያቺን ለባሮቹ የፈጠራትን ከሲሳይም ጥሩዎቹን እርም ያደረገ ማነው? በላቸው» (አል-አዕራፍ 7፡32)

አልኩም፡- «በእርግጥም ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ከየመን ልብሶች ጥሩ የሚባለውን ሲለብሱ አይቻቸዋለሁ፡፡ አሉም እንግዳውስ ችግር የለም፡፡ ምን አመጣህ?» አልኩም ከጓደኛዬ ዘንድ ነው የመጣሁባችሁ፡፡ እሱ ደግሞ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የአጎት ልጅና ባልደረባቸውም ነው፡፡ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ደግሞ ስለወሕዩ ከናንተ ይበልጥ ያውቃሉ፡፡ ቁርኣንም በነሱ ውስጥ ነው የወረደው፡፡ ከነሱ እነግራችኋለሁ፡፡ ከናንተም እነግራቸዋለሁ፡፡ ምንድነውየጠላችሁት? ከፊሎቹ የከለከሉ ሲሆኑ አሉ፡- ከሱ ጋር መነጋገርን ተጠንቀቁ፡፡ በእርግጥ ቁረይሾች ክርክረ ብርቱ ሕዝቦች ናቸው፡፡ አላህ ዐዝ-ዘ ወጀል እንዲህ ብሏል፡-

بَلْ هُمْ قَوْمٌ خَصِمُونَ [٤٣:٥٨]

«... በእውነት እነርሱ ክርክረ ብርቱ ሕዝቦች ናቸው:: » (አዝ-ዙኽሩፍ 58)

ከፊሎቹ ደግሞ አነጋግሩት አሉ:: ከነሱም ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ወደኔ ቀረቡልኝ:: አሉም፡- ከፈለክ ተናገር:: ከሻ ደግሞ እንናገራለን:: እኔም አልኳቸው ይልቁንስ እናንተ ተናገሩ:: እነሱም አሉ፡- ሦስት ነገሮችን በሱ ላይ ተልጠንብሀል:: ፍርዱን ወደሰዎች አድርገሀል:: አላህ እንዲህ ብሏልና፡-

إِنِ الْحُكْمُ إِلَّا لِلَّهِ ۖ

« ... ፍርዱ ለአላህ ብቻ ነው::» (አል-አንዓም 6፡57)

«» (ሱረቱ ዩሱፍ 12፡40-67)

እኔም አልኳቸው፡- አላህ ከትዕዛዙ ፍርዱን በዲርሀም አንድ አራተኛ በርግጥ አድርጓል:: በጥንቸል፣ በሴትና በባሏ መካከልም

وَإِنْ خِفْتُمْ شِقَاقَ بَيْنِهِمَا فَابْعَثُوا حَكَمًا مِّنْ أَهْلِهِ وَحَكَمًا مِّنْ أَهْلِهَا

«(እናንተ ዋቢዎች) የመካከላቸውንም ጭቅጭቅ ብታውቁ ከቤተሰቦቹ ሽማግሌን ከቤተሰቦችዋም ሽማግሌን ላኩ:: » (አን-ኒሳእ 4፡35)

በሰውየውና በባለቤቱ በባሪያው መፍረድ ይበልጣል ወይስ በኡምማው መመለስና ደማቸው እንዲጠበቅ ብትንትናቸው እንዲሰበሰብ ይሻላል? አዎ አሉ:: አሉ ሌላው ደግሞ የሙእሚኖች አዛዥ መሆኑን መራቅ ነው:: የአማኞች አዛዥ ካልሆነ ታዲያ እሱ የከሀዲዎች አዛዥ ነው እንዴ አልኳቸውም:: ንገሩኝ እስኪ በናንተ ላይ ከአላህ መጽሐፍ ካነበብኩኝ ከረሱል (ሰ.0.ወ) ሐዲሥም ካመጣሁላችሁ ትመለሳላችሁን አልኳቸው:: አዎ አሉ:: እኔም አልኳቸው፡- በእርግጥ ሰምተችኋል ወይም በእርግጥ ደርሷችኋል ብዩ አስባለሁ:: ነገሩ የሑደይቢያ ዕለት ሱሐይል ኢብኑ ዐምር ወደ ረሱል (ሰ.0.ወ) መጣ:: ነብዩም (ሰ.0.ወ) ለዐሊይ አሉ፡- ጻፍ! ይህ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ የተስማማበት ነው አሉም አንተ የአላህ መልዕክተኛ መሆንህን ብናውቅ ኖሮ ባልተዋጋህን ነበር:: የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.0.ወ) አሉ፡- አንተ ዐሊይ አብሰው:: ከዚያም ወጣሁ:: አልኳቸው:: አዎ አሉ:: አሉ ተዋጋ አልሰደበም አልማረከም (በጀመልና በሲፊን ዘመቻ ማለታቸው ነው)

እናታችሁን ትሳደባላችሁ ከሷ የተፈቀደ ታደርጋላችሁ ከሌላዋ የተፈቀደ የምታደርጉትን አዎ ካላችሁ በአላህ መጽሐፍ ካዳችሁ፤ ከእስልምናም ወጣችሁ:: እናንተ በሁለት ስህተቶች ውስጥ ሆናችሁ:: ከዚያ የሆነን ነገር ባመጣሁላቸው

ቁጥር እላችኋለሁ ከሷ ወጣሁ እነሱ ደግሞ ይላሉ፡- አዎ አለ፡፡ ከነሱ ሁለት ሺ ተመለሱ፤ ስድስት ሺ ቀሩ፡፡

እነዚህ ሰይፎቻቸውን ለጦርነት የመዘዙት ወገኖች ናቸው፡፡ ከነሱ የነቀፉትን ሰዎች ደም የፈቀዱ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከዚሁ ጋር በእውነት ሲከራከሯቸው ከነሱ አብዛኞቻቸው ይመለሳሉ፡፡ በቁርኣን ሲገስጻቸውም ይገሰጻሉ፡፡ ወደ ውይይትም በተጠሩ ጊዜ በተከፈቱ ልቦች እሺ ይሉ ነበር፡፡ ዛሬ ሙስሊሞች ከዚህ ጉዳይ የት ናቸው

**ክፍል ሦስት**

**በማውጣጣት የመሪዎች ስልቶች መለያየት**

**የፊቅህ መንገዶች (መዛሂቦች)**

ከሰሓባዎች ጊዜና ከታላላቆቹ ታቢዒዮች በኋላ ግልጽ የሆኑት የፊቅህ መንገዶች ወይም መዛሂቦች ከፊል ሰዎች አስራ ሦስት መዛሂቦች ናቸው ይላሉ፡፡ ሁሉም ባለቤቶቻቸው ከአህለል ሱንና የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ያ የሙስሊሞች ሕዝቦችና የአጠቃላያቸውም የነበረውና አሁንም ያለው መዝሁብ የሆነው፡፡ ነገር ግን ከነዚህ መሪዎች ውስጥ የስምንቶቹ ወይም የዘጠኞቹ ፊቅህ እንጅ የመሰብሰብን ዕድል ያገኘ የለም፡፡ ከፊቅሃቸው የተሰበሰበውም ተለያይቷል፡፡ ከፊላቸው ፊቅሃቸው ሁሉ የመሰብሰብ ዕድል አግኝቷል፡፡ ከሌሎቹ አኳያ በከፊሉ ያጠረ ሲሆን ከነዚያም ከነዚያ ከተሰበሰበው የመዝሃቦቻቸው መሠረት ታወቁ፡፡ የፊቅህ ስልቶቻቸውም እነዚያ እነሱ በመጀመሪያ

1/ አል-ኢማሙ አቡ ሰዒዲን አል-ሐስን ኢብን የስሪን አል-በስሪ (110 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

2/ አል-ኢማሙ አቡ ሐኒፋ አን-ኑእማን ኢብኑ ሣቢት ኢብኑ ዙጢ (150 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

3/ አል-ኢማም አል-አውዛዒ አቡ አምር ዐብዱር-ረጀሕማን ኢብኑ ሙሐመድ (157 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

4/ አል-ኢማም ሱፍያን ኢብኑ ሰዒድ ኢብኑ መስሩቅ አስ-ሰውሪ (160) ዓ.ሂ. ሞቱ፡፡

5/ አል-ኢማም አለይስ ኢብኑ ሰዕድ (175 ዓ.ሂ.) ሞቱ፡፡

6/ አል-ኢማም ማሊክ ኢብኑ አነስ አል-አስበሒ 179 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

7/ አል-ኢማም ሱፍያን ኢብኑኡየይና (179 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

8/ አል-ኢማም ሙሐመድ ኢብኑ እድሪስ አሽ-ሻፊዒይ (204 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

9/ አል-ኢማም ኢብኑ ሐንበል (241 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

አል-ኢማም ዳዉድ ኢብኑል ዐሊይ አል-ኢስትሃኒ አል-በግዳዲ አዝ-ዛህሪ በመባል የታወቁትም አሉ፡፡ የቁርአንና የሱንናን ግልጹን በመያዝ ወደዚህ የተጠጉ ወይም ቅፅል ስም የተደረገላቸው (270 ዓ.ሂ) ሞቱ፡፡

ከነዚህ ውጭም ብዙዎች አሉ፡፡ እንደነ ኢስሓቅ ኢብኑ ራህወይሂ (238 ዓ.ሂ) ያለፉት፡፡

አቡ ሰውር ኢብራሂም ኢብኑ ኻሊድ አል-ከልቢ በ240 ዓ.ሂ ላይ የሞቱ፡፡

ሌሎችም መዝሃቦቻቸው ያልተሠራጩ ተከታዮቻቸው ያልበዙ ለታወቁት የመዛሂብ ባለቤቶች ተከታይ ተብለው የተቆጠሩ አሉ፡፡ እነዚያ መዝሃቦቻቸው መሠረት የያዙት እስከዛሬው ዕለታችን ድረስ የቆዩዋቸው በሁሉም የኢስላም ሀገሮች ለሷ ብዙ ተከታዮች ያላት ከመሆን የማትወገደው ፊቅሃቸውና መሠረቱ ፊቅህን የመማርና የፈትዋ መሽከሪከሪያ ከመሆን ያልተወገደው በሕዝቡ ዘንድ እነዚያ እነሱ አራቶቹ መሪዎች አቡ ሐኒፋ፣ ማሊክ፣ ሻፊዒ እና አሕመድ ናቸው፡፡

የታወቁ መሪዎች ስልቶች

ሦስቶቹ መሪዎች ማሊክ፣ ሻፊዒና አሕመድ የሒዲሥና የአሠር ፉቀአዎች ይመደባሉ፡፡ እነሱ ናቸው የመዲናን ሰዎች ፊቅህ የተቀበሉት፡፡ ዕውቀታቸውንም የተሸከሙት፡፡

ኢማሙ አቡ ሐኒፋማ እሳቸው የአስተያየት ሰዎችን (አስሓቡል ረእይ) የፊቅህ ወራሽ ናቸው፡፡ በጊዜያቸው የነሱን ትምህርት ቤት አሳዳጊ ናቸው፡፡

በሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብ ት/ቤት በሰሓባዎች ፊቅህና ዐሰር ላይ የተመሠረተ ማሊኪያና ሻፊዒያና ሐናቢላ በነሱ አካሄድ የሄዱበት መካከልና በኢብራሂም አን-ነኻዒ ያ እስኪጠፉ አስተያየት ላይ የሚደገፍ ት/ቤት መካከል የነበረው ልዩነት፡፡ ይህ ልዩነት ከሁለቱ ት/ቤቶች ያንዱን ስልት ወደተከተለ ሰው ሁሉ መሸጋገሩ ተፈጥሯዊ ነበር፡፡ አንድም ሰው በዚህ ጊዜ ውስጥ ልዩነት ጥንካሬ መቅለሉን የሚከዳ የለም፡፡ ያም ኸሊፋነት ወደ ዐብ-ባስ ልጆች ከተሸጋገረ በኋላ ዐብባሲዮች የሒጃዝን ከፊል ታላላቅ ዑለማዎች ሱንናን እንዲያሰራጩ ወደ ዒራቅ ወስደዋል፡፡ ከነሱ ውስጥ ራቢዐት ኢብኑ አቢ ዐብዱረሕማን እና የሕያ ኢብኑ ሰዒድ ሒሻም ቢን ዑርዋ፣ ሙሐመድ ኢብኑ ኢስሓቅ ሌሎችም ከፊል የዒራቅ ዑለማዎችም ወደ መዲና ሄደው ከዑለማዎቿ እንደተማሩም ሁሉ፡፡

እንደነ አቡ ዩሱፍ ያዕቁብ ኢብኑ ኢብራሂም እና ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን እነዚያ ከማሊኪ የተማሩት ብዙ የዒራቃዉያን አስተያየቶችና አመለካከቶችም ወደሒጃዝ እንደተሸጋገሩ ሁሉ … የሒጃዞቹም አመለካከት ወደ ዒራቅ እንደተሸጋገረው፡፡ ከዚህም ጋር ሦስቶቹን መሪዎች ማሊክን፣ ሻፊዒንና አሕመድን በመካከላቸው ተቀራራቢ ስልት ከውነው እናገኛቸዋለን፡፡ በከፊል የማውጣጣት ስልቶችና መንገዶቹ ቢለያዩ እንኳ አል-ኢማሙ አቡ ሐኒሃ ከነሱ በስልቱ የተለዩ ቢሆኑም እንኳ

1/ የኢማሙ አቡ ሐኒፋ ስልት፡-

አል-ኢማም አቡ ሐኒፋ ከሦስቱ መሪዎች ስልቶች ግልጽ በሆነ ቅርጽ ለተለየ ስልት ምልክት ሆኗል፡፡ የመዝሀቡ ሕጎች እርሱ እንደቀረጻት በማለቱ ውስጥ ታጥራለች፡፡ «እኔ የአላህን መጽሐፍ እይዛለሁ፤ ካገኘሁት በሱ ውስጥ ካለገኘሁት የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሥ እይዛለሁ፡፡ ከሳቸው የተሠራጩ ትክክለኛ አሠሮችን፤ በአላህ መጽሐፍ ውስጥና በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ውስጥ ካላገኘሁት የባልደረቦቻቸውን ንግግር እይዛለሁ፤ ከዚያም ከነሱ ንግግር ወደሌላ አባባል አልወጣም፡፡ ነገሩ ወደ ኢብራሂምና ወደ ሸዕቢ እና ኢብኑል ሙሰይብ (ሰዎችን ቆጠሩ) እነሱ እንደታገሉት እኔም መታገል እችላለሁ፡፡»

እነዚህ ለአቡ ሐኒፋ መዝሀብ ታላላቆቹ መሠረቶች ናቸው፡፡ ቅርንጫፋዊ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የሆኑ ከነዚህ ታላላቅ መሠረቶች የተቀናዘሉ ወይም ወደነሱ የሚመለሱ እሷ ያቺ ልዩነት ግልጽ የሚሆንባት ነች ማለታቸውን ይመስል፡፡ «ዓም የሆነ ቃል የሚያመለክተው ቁርጠኛ መሆኑ እንደኻስ ነው» የሰሓቢይ መዝሀብ ከዓም የተቃረነ ሲሆን የሱ ለይ ነው» እና «የአውሪዎች ብዛት አመዛኙነቱን አያስይዝም» እና «ከሸርጥ እና ከገለጻ/ሲፋ የምንረዳው ሑክም ከግምት

አለመግባቱ» እና «መጠንቀቁ በሚያስቸግር ጉዳይ ላይ የአንድን ሰው ሐዲሥ አለመቀበል» እንዲሁም «ትዕዛዝ በቁርጥ ግዴታነትን ያስፈርዳል የሚቀይረው እስካልመጣ ድረስ» «ፈቂህ የሆነ ዘጋቢ በተቃራኒው ከሠራ በሱ አስተያየት እንጅ በዘገባው አይደለም መሠራት ያለበት» «ግልጽ የሆነውን ቂያስ ከሚቃረነው የአንድ ሰው ሐዲሥ ማስቀደም» «ጥሩ (ኢስትሕሳን) ነው የተባለውን መያዝ ቂያስን መተው ያ ነገር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ»

ስለዚህም ከኢማሙ አቡ ሐኒፋ ማለቱን ዘግበዋል፡- «ይህ ዕውቀታችን አስተያየት ነው፤ እሱም ከቻልነው ይበልጥ የተሻለው ነው፡፡ ከሱ ይበልጥ የተሻለ ያመጣልንን ሰው እንቀበለዋለን፡፡»

2/ የኢማሙ ማሊክ ስልት/ የጥናት ዕቅድ፡-

ኢማሙ ማሊክ የተለየ የጥናት ዕቅድ/ስልት አላቸው፡፡ እሳቸውም ይሉ ነበር፡- «አንድ ሰው በመጣ ቁጥር ጅብሪል በሙሐመድ ላይ ያወረደውን ለክርክሩ ስንል እንተዋለን እንዴ»

በእርግጥም የሳቸው መጽሐፍ የሒጃዛዉያን የኢማም ሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብ ት/ቤት ባልደረቦች ናቸው ማለት አልፏል፡፡ የማሊክን መዝሀብ ሕጎች እንደሚከተለው መጠቅለል ይቻላል፡-

/ የማያሻማ የሆነን የቁርኣን ማስረጃ መያዝ (ነስ)

/ ከዚያ አሻሚ የሆነን የቁርኣን ማስረጃ (ዛሀረነስ) (አል-ዑሙም)

/ ከዚያ (መፍሁም አል-ሙኻለፋ)ን እሱም ብያኔው ከተነገረው ማስረጃ ጋር የሚጋጭ ማስረጃ

/ ከዚያም (መፍሁመል መዋፈቃ)ን እሱ ደግሞ ብያኔው ከተነገረው ማስረጃ ጋር የሚጣጣም ማስረጃ ነው፡፡

/ ከዚያ ማስረጃው የሚጠቁመውን ነገር መያዝ ምክንያትን መጠቆምን ይመስል እንደ አላህ አባባል፡-

/ እነኚህ አምስት መሠረቶች ናቸው፡፡ ከሐዲሥም እንደዚሁ አምስት አለ፡፡ አስር ይሆናሉ፡፡

/ ከዚያ የዑለማኦች ስብስብ ነው (ኢጅማዕ)

/ ከዚያ ቂያስን መያዝ

/ ከዚያ የመዲና ሰዎች ሥራ

/ ከዚያ ለማቅለል ቂያስን መልቀቅ (ኢስቲሕሳን)

/ ከዚያ መንገዶችን ለመዝጋት መበየን

/ ከዚያ ከሸሪዓ ጋር የሚስማማን ጥቅም መሥራት

/ ከዚያ የሰሓቢይ ንግግር (ሰነዱ ትክክለኛ ሲሆንና ከታላላቆቹ ሲሆን)

/ ከዚያ ልዩነትን መጠባበቅ (የተቃዋሚው ማስረጃ ጠንካራ ከሆነ)

/ ከዚያ ኢስቲስሓብ

/ ከበፊታችን የነበሩ ሰዎች ሕግ

4/ የኢማሙ ሻፊዒ ስልት/የጥናት ዕቅድ

የኢማሙ ሻፊዒ መዝሀብ ሕጎችና መሠረቶችማ እሷ በኡሡል ሪሳላ የሚባል መጽሐፋቸው ያ በእስልምና ውስጥ ስለኡሡል ሰብሳቢ የሆነ የመጀሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጠቀለሉት ነው፡፡

እሳቸውም አሉ፡- «መሠረት ማለት ቁርአንና ሐዲሥ ነው፡፡ ከሌሉ በነሱ ላይ በማቅጣጫት/በመገመት ሐዲሡ እስከረሱል ድረስ ሰንሰለቱ ከተቀጠለና ትክክለኛ ከሆነ እሱው ነው የሚፈለገው፡፡ ከዚያም የዑለማዎች ስብስብ ከአንድ ሰው ሐዲሥ ይበልጣል፡፡ ሐዲሥ አሻሚ ያልሆነው ይቀደማል፡፡ አሻሚ ከሆነ ያልሆነው ጋር የተመሳሰለው በላጭ ነው፡፡ ሐዲሦች አቻ ከሆኑ ሰነዱ ይበልጥ ትክክለኛ የሆነው በላጭ ነው፡፡ ሰነዱ የተቆረጠ ሐዲሥ ተቀባይነት የለውም፤ የሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብ ብቻ ሲቀር፡፡ አንድ መሠረት በሌላው መሠረት ላይ አይቀየስም፡፡ መሠረት ደግሞ ለምን እንዴት አይባልም፡፡ ለምን እሚባለው በቅርንጫፋዊ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ በመሠረት ማስከተሉ ከተቻለ ትክክል ይሆናል ለማስረጃነትም እሱን መጠቀም ይቻላል፡፡»

እንግዳውስ ኢማሙ ሻፊዒ ቁርአንንና ሐዲሥን በድንጋጌ እኩል አድርገው ነው የሚያዩት፡፡ በሐዲሥ ከትክክለኛነትና ከመቀጠሉ ውጭ ምንም ዓይነት መስፈርት አያስቀምጡም፡፡ እሱ መሠረት ስለሆነ መሠረት ደግሞ ለምን እንዴት አይባለውም ሐዲሡ የታወቀ መሆንም የግድ አይደለም፡፡

ኢማም አቡ ሐኒፋ መጠንቀቁ በሚያስቸግር ጉዳይ ላይ እንደሸረጠው እንደዚሁም ሐዲሡ የመዲናን ሰዎች ተግባር አለመጋጨትንም አልገደበም፡፡ ነገር ግን እሳቸው ከሙርሰሎች/ሰንሰለታቸው ከተቆረጠ ሐዲሦች የሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብን እንጅ አልተቀበሉም፡፡ ምክንያቱም እሱ ጋ የተቀጠሉ መንገዶች አለውና፡፡ በዚህ ጉዳይ ማሊክንና ሰውሪን በጊዜው ያሉትንም ሰዎች እሷን እንደማስረጃ ይወስዷት የነበሩትንም የሐዲሥ ሰዎች ኢስቲሕሳንን እንደማስረጃ መውሰድንም አልተቀበለም፡፡ ከዚያ ከማሊኪያና ከሐነፊያ የተለየ ሲሆን፡፡ የታወቀ የሆነውንም አባባል አለ፡- «ጥሩ ነው ያለ ሰው በእርግጥም ሕግ አወጣ፡፡» «መሳሊሐል ሙርሰላንም» እንዳልተቀበለ ሁሉ» ማስረጃነቷንም መለሰ፡፡ እንደዚሁም ግልጽ የሆነ ሕግ ያለው ምክንያት ላይ ባልቆመ ቂያስ ማስረጃ ማድረግ

ጠልቷል፡፡ የመዲና ሰዎችን ሥራ እንደማስረጃ መቀበልንም ጠልቷል፡፡ በሐነፊያዎችም ላይ በሐዲሦች መሥራት መተዋቸውን ተቃውሟል፡፡ እንደሹህራና መሰል ያስቀመጧቸው መስፈርቶች ስላልተሟሉ፡፡ እሱ እንደ ማሊክ የሒጃዚዮችን ሐዲሥ ብቻ በመያዝ እንዳላሳጠረ ሁሉ፡፡

እነኚህ በጥቅሉ የኢማሙ ሻፊዒ መዝሀብ ይበልጥ አስፈላጊና ግልጽ መሠረቶች ናቸው፡፡ በውስጧ ከሐነፊያና ከማሊኪያ መሠረቶች የማይደበቅ የሆነ ልዩነት አለ፡፡

4/ የኢማሙ አሕመድ ኢብን ሐንበል ስልት፡-

ኢማሙ አሕመድ ኢብን ሐንበል የመዝሀቡ ሕጎች ወደ ኢማሙ ሻፊዒ መዝሀብ ሕጎች የበረታ ቅርበት አላቸው፡፡ እሳቸው ቀጣዩን ይይዛሉ፡-

አንደኛ፡- የቁርአንና የሐዲሥ ማስረጃዎችን እነዚህን ካገኘ ወደሌላ አይዟዟርም፡፡ ትክክለኛና ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከተጠጋ ሐዲሥ ምንም አያስቀድምም፡፡ «የመዲና ሰዎችንም ሆነ አስተያየትን ወይም ቂያስን ወይም የሰሓቢይን ንግግር ወይም ተቃራኒን ባለማወቅ ላይ የተመሠረተን የዑለማኦች ስብብስብም»

ሁለተኛ፡- በመስአላው ከቁርአንና ከሐዲሥ ማስረጃ ካላገኘ ወደ ሰሓባ ፈትዋ ይሸጋገራል፡፡ የሰሓቢይን ንግግር ካገኘ ከሰሓባዎች የሚቃረነውን የማያውቅ ሆኖ ወደሌላ አያልፈውም፡፡ ሥራን ወይም አስተያየትን ወይም ቂያስን አያስቀድምም፡፡

ሦስተኛ፡- ሰሓባዎች ሲለያዩ ደግሞ ከንግግራቸው ወደ ቁርአንና ሱንና የቀረበውን ይመርጣል፡፡ ከንግግሮቻቸው አይወጣም፡፡ወደቁርአንና ወደ ሐዲሥ ይበልጥ የሚቀርበው ግልጽ ካልሆነለት ደግሞ ልዩነቱን ያወራና ከሷ ባንዱ ንግግር አይቆርጥም፡፡

አራተኛ፡- የተቆረጠና የሚጠገን የሆነን ድክመት ያለበትን ሐዲሥ ይይዛል፡፡ በርዕሱ ሌላን ያላገኘ ጊዜ የሚገፈትረውም የሰሓቢይ ንግግር ወይም የሰሓቢይን ንግግር ወይም ከሱ የሚለይ የዑለማእ ስብስብ ከቂያስም ያስቀድመዋል፡፡

አምስተኛ፡- ቂያስ እሳቸው ዘንድ የችግር ጊዜ ማስረጃ ነው፡፡ ካለፉት ማስረጃዎች አንዱንም ሳያገኙ ሲቀሩ ወደሱ ይጠጋሉ፡፡

ስድስተኛ፡- መንገዶችን መዝጋት የሚባለውን ማስረጃ ይጠቀሙታል፡፡

5/ የኢማም አዛሂሪ ስልት

የዛሂሪያን መዝሀብ ሕጎችና መሠረቶቹን ባጭሩ መዳሰስ አስፈላጊ ነው፡፡ ያም የሆነበት ይህ መዝሀብ ተጽዕኖ ካላቸው ኢስላማዊ መዝሀቦች አንዱ ስለሆነ ነው፡፡ በእርግጥም ከኺላፍ ዓይነቶች የበረታው በዛሂሪያና በሐነፊያ ከዚያም በማሊኪያ ከዚያም ሐናቢላ ከዚያም ሻፊዒያ መካከል ተኝገቷል፡፡ በእርግጥም ዳዉድ ለሻፊዒ በብዙ ደረጃ ያምን ነበር፡፡ ከዛሂሪያ መዝሀብ መሠረቶች ይበልጥ ግልጽ የሆኑት የተከበሩትን የቁርኣን አንቀጾች ግልጾችና ሱንናን መያዝ እነሱን ማስቀደም መዕናዎችንና ጥበቦችን ጥቅሞችን ከመጠባበቅ ለሷ ተብሎ ነው የተደነገገችው ተብሎ የሚገመተውን፡፡ እሱ ጋ በቂያስ አይሠራም፡፡ ጥበቢቷ በመጀመሪያው ቦታ ላይ በግልጽ ካልተነገረች በሁለተኛው ቦታ ላይ ደግሞ መኖሯ እርግጠኛ ካልሆነ ልክ ብይኑ ይደረጋል፡፡ ጥበቡን ለማረጋገጥ እንደመጣ ነገር፡፡ በኢስቲሕሳን መሠረትም እርም እንደሆነ ሁሉ በሰሓባዎች ጊዜ በተገኘው የሰሓባዎች መስማማት ይሠራል፡፡ በሙርሰልም በተቆረጠ ሐዲሥም አይሠራም፡፡ በማሊኪያና ሐነፊያ ሐናቢላ ተቃራኒ ከበፊታችን ባሉት ሰዎች ሸሪዓ አይሠራም፡፡

ለአንድም ሰው በአስተሳሰብ መሥራት አይፈቀድም፡፡ አላህ ስላለ፡-

«በመጽሐፉ ውስጥ ምንንም ነገር አልተውንም፡፡» (አል-አንዓም 6፡38)

በግልጽ የተነገረን ብይን ወደሌላ ማሸጋገር የአላህን ድንበር መሸጋገር ነው፡፡ ለአንድም ሰው በመፍሁመል ሙኻሊፍ መሥራት አይፈቀድም፡፡ ማስረጃውን ሳያውቁ ሌላን ሰው መከተል በተራ ሰው ላይ እርም ነው፡፡ በአዋቂ ላይ እርም እንደሆነ ሁሉ ማንኛውም አካለ መጠን የደረሰ ሰው ከጥረት የሚችለውን ማድረግ አለበት፡፡

ለኛም ንግግር አለን

እውነታው ኢማሙ ወደሚከተላቸው መሪዎች የተጠጉት መርካታ መሠረቶች ናቸው፡፡ እነሱ ከንግግሮቻቸው የተውጣጡ መሠረቶች ናቸው፡፡ ከነሱ እነኚህን መሠረቶች ማውራት በትክክለኛ ሰነድ አልተገኘም፡፡ ይህን ማረጋገጥ መሷም መከላከል በነሱ ላይ ነቀፋዎችንና መልሶችን ማምጣት እራስን ማስገደድ እሷን የሚቃረን ላይም መመለስ በዚሁ ሁሉ ነገር ራስን መወጠር ከአላህ መጽሐፍ እና ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ይህ ሁሉም አስቀያሚ የሆነውን ልዩነት ከሚሩ ግልጽ ተጣሪዎች ናቸው፡፡ ያም መሪዎቹ ራሳቸው ያላለሙት የሆነው ይህ ነገር ከሙስሊሞች የመጨረሻዎቹን ከታላላቅ ጉዳዮች አርቋቸዋል፡፡ በወራዳ ነገሮች ቢዚ አደረጋቸው፡፡ ኡምማው ወደዚያ ወደ ወራዳ አዘቅት ዛሬ የምትንከባለልበት ወደሆነው እንድትወርድ አደረጋት፡፡

## ክፍል አራት

## የልዩነት ምክንያቶችና ዕድገቱ

የመለያየት ምክንያቶች ከነብይነት ጊዜ እስከ ፉቀሃኦች ጊዜ

ልዩነት ማስተዋል በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ እንደ ፊቅህ ተፈጥሯዊ ጉዳይ መሆኑን ከተቀበልን ሰዎች በአዕምሮዎቻቸው በግንዛቤዎቻቸው በአረዳዳቸው የተለያዩ ሆነው ስለተፈጠሩ ልዩነት በነብይነት ጊዜ በቅን ኸሊፋዎች ጊዜ በብዙ ሰሓባዎች መካከል የተገኘ ጉዳይ መሆኑን ማመን የግድ ይሆናል፡፡ ይህን ደግሞ በርካታ ክስተቶች ይመሰክሩለታል፡፡ ይህን መካዱ ይህን ሃይማኖት የሚያገለግለው ነገር የለውም፡፡ እሱን መግለጽም የዚህን ደዕዋ ተምሳሌታዊነት ይነካል ብለን እንደማናምን ሁሉ የነዚያ የሚለያዩ ሰዎች ሐሳብ እውነትነትንም፡፡ ይልቁንስ ማለት እንችላለን፡፡ እነኚህን ልዩነት በማውሳት ውስጥ የዚህን ሃይማኖት ተጨባጫዊነት መግለጽ አለበት፡፡ እሱ ከሰዎች ጋር እነሱ ሰዎች መሆናቸውን አምኖ ነው ከነሱ ጋር የሚዋዋለው፡፡

አላሁ ተዓላ ፍጡራኑን በሱ ላይ ከፈጠረው ነገር የተለያዩ ግፊቶች የሚከራከሩባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን አማኝ የሆነች ነፍስ የምትረጋጋበት ያ ልዩነት ከዐቂዳ/እምነት ድክመት ያልተነሳ ወይም ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የሚጠሩበት ጉዳይ እውነት መሆኑን ከመጠራጠር የመጣ አለመሆኑን ይልቁንስ ሐቅን መፈለግ የደንጋጊውን ሐሳብና ከብይኖች ማግኘትን መፈለግ የሁሉም ተለያይዎች ፍላጎት ነበር፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የነዚያ ድንጋጌዎች ምንጭ ስለነበሩ የልዩነቱ ዕድ ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሚያደርሰው መንገድ የረዘመ አልነበረም፡፡ በእርግጥም አይተናል ባለፉት ክስተቶች መሃል የልዩነት ምክንያቶች በጥቅሉ ማስረጃውን ለቋንቋዊ ወይም ለምርምራዊ ምክንያቶች ባረዳድ ከመለያየት ያልወጣ መሆኑን አይተናል፡፡ ያም ከአላህ መጽሐፍ እና ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና በፊታቸው ያለውን በማብራራት ነው፡፡

እነኚህ ምክንያቶች በጀርባቸው ምንም ዓይነት ሐሳቦችን አልደበቁም፡፡ ምናፍቃኖች ሊያሳድጓት ይጓጉላት የነበረችውን የልዩነት ዘር የምትሞክር፡፡ ስለዚህም እነዚህ ልዩነቶች በፍጥነት ይጠፉ ነበር፡፡ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በመገናኘት ወይም ከፊላቸው አግኝተውት ከሌሎቹ በራቀ ማስረጃ መዳኘት የጥሩ አፈጣጠር ባለቤት ዓላማው የትም ቢገኝ ሐቅን መፈለግ ነውና፡፡

ገለልተኛ ከፊል የልዩነት ምክንያቶች ከጊዜ ወደሌላ ጊዜ መሽጋገራቸው የተለመደ ነው፡፡ በየጊዜው የልዩነትን ምክንያቶች በጀርባቸው የሚያሳጥሩ ግርዶሾችን ማስቀመጥ ይከብዳልና፡፡ ነገር ግን በኢስላማዊ ሜዳ ላይ የሚፈጠሩ ነገሮች ነበሩ፡፡ የልዩነትን መንፈስ የሚያቀጣጥሉ ምክንያቶችን የወለደች፡፡

ሦስተኛው ኸሊፋ ዑሥማን ኢብ ዐፍ-ፋን ረዲየሏሁ ዐንሁ ከተገደሉ ጊዜ ጀምሮ ኢስላማዊ ከተሞች ከባድ ለሆኑ ችግሮች ተዳርገዋል፡፡ ከፊል ወደ ልዩነት ክበብ ከውጭ ያሉትን ጉዳዮች ያስገቡ ክስተቶችን ፈጥራለች፡፡ ካሁን በፊት እንደጠቆምነው የየአገሩና ከተማ ሰዎች ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ቅጥፈትን ፈርተው የደረሳቸውን ብቻ ይዘው ሌላ አለመቀበል ደረጃ አድርሷቸዋል፡፡ የኩፋና በስራ ት/ቤቶች ለፖለቲካዊ ዕይታዎች መብላላት እንደለም አካባቢ ሆነው ዘልቀዋል፡፡ የተለያዩ ቡድኖችም በዝተዋል፡፡ እንደ ኸዋሪጆች፣ ሺዓ፣ ሙርጂአ፣ መዕተዚላና ሀጅሚያም ሌሎችም ከፈጠራና ዝንባሌዎች ባለቤቶች፡፡ እነዚያ ቡድኖች በሙብዛታቸው አዕምሯዊና የማስተዋል ስልቶች በዝተዋል፡፡ ለየቡድኑ ሁሉ መነሻዎች ተገኙለት፡፡ ከሕግ አውጪው ማስረጃዎች ጋር ሲዋዋሉ መነሻ ሕጎችም ሸሪዓዊ ምንጮችንም በማብራራት ጊዜ አዲስ በተገኙ የተለያዩ ጉዳዮች ባለው አቋሞቿም ሕጎችንና ገደቦችን ወደማስቀመጥ ፍላጎት መገለጽ ጀመረ፡፡ ስልቶችንና ከአምላካዊ ራዕይ የክስተቶች ብይኖች የማውጣጫ ወደመወሰን፡፡ በሱ ላይ መለያየት የሚፈቀድና የማይፈቀድን መወሰንም፡፡

ከአላሁ ተዓላ ችሮታ መሆኑ እርግጥ ነው፤ የፊቅሁን ዘርፍ በሱ ላይ መለያየቱ ከሚፈቀደው ክበብ ውስጥ ማድረጉ፡፡ ያም ፊቅህ ማለት አንድ ፈቂህ የክስተቱን ብይን ከማስረጃው ማወቅ ስለሆነ ነው፡፡ ዝርዝራዊና ከፊላዊ ከሆኑት ደንጋጊው ብይኖቹ ላይ እንዲያመለክቱ ካስቀመጣቸው ማስረጃዎች ከቁርአን አንቀጾችና ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሦች፡፡ ፈቂህ የደንጋጊውን «ሻሪዑ»ን ብይን ሊያገኝ ወይም ሊስማማ ይችላል፡፡ ያንን ላይስማማም ይችላል፡፡ ነገር ግን እሱ በሁለቱም ሁኔታዎች ብይኑ ላይ ለመድረስ አዕምሮው የሚችለው የመጨረሻውን ችሎታ ከመለገስ የበዛ አይገደድም፡፡ የደረሰበት የሻሪዑ ብይን እንኳ ባይሆንም እሱ በእውነታውና በግቦቹ በውጤቶቹ ወደሱ የቀረበ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ልዩነት ሕጋዊ ሆኗል፡፡ ያም ሁለት ነገሮች በውስጡ ስለተካተቱ ነው፡፡

አንደኛ፡- ለሁሉም ተለያይ ቡድኖች ለማስረጃነት የሚበቃ ማስረጃ መኖር ነው፡፡ ለማስረጃነት የሚሆን ማስረጃ የሌለው ይወድቃል፡፡ በጭራሽ አይቆጠርም፡፡

ሁለተኛ፡- ተቃራኒውን መዝሀብ መያዝ ወደ ውሸት ወይም ከንቱ ነገር ላያደርስ ነው፡፡ ያ ነገር ካለ ከመጀመሪያውም ተበላሸ፡፡ ለአንድም ሰው በምንም

ሁኔታ እሱን ማለቱ አይቻልም፡፡ በነዚህ ሁለት ነገሮች ኢኽቲላፍ ከኺላፍ ይለያል፡ ፡ ኢኽቲላፍ ማለት እነዚህ ሁለቱ የተወሱት መስፈርቶች የተሟሉበት ነው፡፡ እሱ የአዕምሮና የኢጅቲሃድ ዕይታ መገለጫዎች መገለጫ ነው፡፡ በብዛት ምክንያቶቹ ስልታዊና ገለልተኛ ናቸው፡፡ ኺላፍ ማለት ደግሞ እሱ ያ ሁለቱንም መስፈርቶች ወይም አንዱን ያጣ ነው፡፡ እሱ ከመጨማደድና ከዝንባሌ ከመጋጨት መገለጫዎች አንዱ መገለጫ ነው፡፡ ወደ ገለልተኝት የሚወስደው አንድም ምክንያት የለውም፡፡

የፊቅሃዊ ልዩነቶች ምክንያቶችና በፉቀሃኦች ጊዜ

እነዚያ ኡምማው መዝሀቦቻቸውን በመያዝ ላይ የተስማሙት ፉቀሃኦች እነዚያን ሁለት ያለፉ መስፈርቶች ለመያዝ ጓግተዋል፡፡ ሰዎች በዚያ ጊዜ ውስጥ የነበሩትን የፊቅህ ልዩነቶች ምክንያቶች ለመወሰን ግልጽ የሆነን መለያየት ተለያይተዋል፡፡ ከነሱ ውስጥ እነዚህን ምክንያቶች በማውሳት ያበዛ አለ፡፡ መካከለኛም አለ፡፡ ከዚሁ ጋር እነዚህን ምክንያቶች ወደቀጣይ ጉዳዮች መመለስ ይቻላል፡፡

1/ ከቋንቋ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች

ያም በሕግ አውጪው ንግግር ውስጥ አሻሚ የሆነ ቃል መምጣትን ይመስል፡፡ እሱም ለብዙና ለተለያዩ ትርጉሞች የተኖረ ነው፡፡ «ዐይን» የምትባለውን ለተመልካች ዐይን እና ለፈሳሽ ምንጭ ለንጹሕ ወርቅ ለስላይ ለሌሎችም ትርጉሞችም የሚጠቀሟትን ቃል ይመስል፡፡

በሻሪዑ ንግግር ውስጥ ከጠቋሚ ነፃ ሆና ስትመጣ የተኖረችላቸው ትርጉሞች እኩል ይሆናሉ፡፡ ሁሉም የታሰበ መሆኑን በማስቻል - ተመራማሪዎቹ ያንን ቃል ትርጉም ለመስጠት የትኛውንም የተኖረለትን ትርጉም ቢሆንም ወይም ሁሉንም ትርጉሞቹን ይለያያሉ፡፡

ፈቀሃኦች «አል-ቁርእ» በሚለው ቃል ሻሪዑ የሻው ምንድነው በማለት ተለያይተዋል፤ በቀጣዩ የአላህ ንግግር ላይ፡-

«የተፈቱ ሴቶች ነፍሶቻቸውን (ከማግባት) ሦስት ቁርእ ይጠብቁ፡፡» (አል-በቀራህ 2፡228)

«ቁርእ» የሚለው ቃል በወር አበባ ጥራትና በወር አበባ መካከል አሻሚ ነው፡፡ ፉቀሃኦች በተፈታች ሴት ዒዳ ተለያይተዋል፡፡ በወር አበባ ነው የሚሆነው ወይስበወር አበባ ጥራት ከነሱ ሒጃዛዉያኖቹ የተፈታች ሴት ዒዳ ሦስት የወር አበባ ጥራት ነው ብለዋል፡፡ የዒራቅ ሰዎች ደግሞ እሱ ሦስት የወር አበባ ነው ብለዋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ከቃሉ ሁለት አጠቃቀም ይኖረዋል፡፡ ሐቂቃ እና መጃዝ፡፡ ፋቀሃኦች ቃሉ በዚያ ማስረጃ ውስጥ ከሻሪዑ ማስረጃዎች በየትኛው ትርጉም ነው የመጣው በማለት ይለያያሉ፡፡ በመጀመሪያ ዑለማኦች መጃዝ በሻሪዑ ንግግር ውስጥ አለ የለም በማለት በእርግጥ ተለያይተዋል፡፡ ብዙዎቹ አረጋግጠውታል፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ የለም ብለዋል፡፡ እንደ ኡስታዝ አቡ ኢስሓቅ አል-ኢስፊራዒኒ እና ሸይኽል ኢስላም ኢብን ተይሚያ፡፡

እነዚያ የለም ያሉት እንደማስረጃ የወሰዱት መጃዝ ማለት እሱ ቃሉን በመጀመሪያ ከተኖረለት ነገር ውጭ መጠቀም ነው፡፡ «አንበሳ» የሚለውን ቃል ተጠቅሞ ጀግና ሰው መሻትን ይመስል፡፡ የሻሪዑ ማስረጃዎች የሸሪዓን ሕግጋቶች ለመግለጽ ነው የመጣችው፡፡ አንድን ቃል ተጠቅሞ ከተኖለት ውጭ መሻት ደግሞ ከታሰበለት ገለፃ ጋር ይጋጫል፡፡ አሁን በዚህ ርዕሰ ጥናት ላይ አይደለንም፡፡ ብዙኃኖቹ ዑለማኦች በሻሪዑ ቃል ውስጥ መጃዝ ይገኛል በሚለው ሄደዋል፡፡ ኢብኑ ቁዳማ እና ከኡሱሊዮች ሌሎችም በሻሪዑ ማስረጃ ውስጥ የለም ብሎ መካድ የኩራት ዓይነት ነው ብለዋል፡፡ ስለዚህ ዑለማኦች የሻሪዑን ንግግር ሐሳብ በመረዳት ይለያያሉ፡፡ በሐቂቃ በመጃዝ መካከል በሚመላለስ መዋቅር በመጣ ጊዜ ወይም ሁለቱንም ነገሮች የሚያስመች ነጠላ ቃል የመጣ ጊዜ ከፊሎቹ በሐቂቃው መዕና ሲተረጉሙት ሌሎቹ ደግሞ የመጃዙን ትርጉም ይሰጡታል፡፡ ያም እንደ «ሚዛን» ቃል ነው፡፡ ሐቂቃው ያ ሰዎች ነገሮችን የሚመዝኑበት ዕቃ ነው፡፡ በመጃዝ ደግሞ ለፍትሕም ይመጣል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

«ሰማይን አጓናት፤ ትክክለኛነትንም ደነገገ፤ በሚዛን (ስትመዝኑ) እንዳትበድሉ፤ መመዘንንም በትክክል መዝኑ፤ ተመዛኙንም አታጓድሉ፡፡» (አር-ረሕማን 55፡7-9)

ሚዛን በመጀመሪያዋም በሁለተኛዋም በፍትሕ ነው የተጠቀሙት፡፡ አላሁ ተዓላ እንዳለው፡-

«መልዕክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን፡፡ ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደነርሱ አወረድን፡፡» (አል-ሐዲድ 57፡25)

በሦስተኛዋ ቁሳዊ ትርጉሙ ነው የተሻበት፡፡ እሱም ነገሮች የሚመዘኑበት መሣሪያ ነው፡፡ ለዑሩድ የግጥም ሚዛን ለነሕውም የንግግር ሚዛን እንደሚባለው የሱው ዓይነት ነው፡፡ ሲልሲለህ የሚለው ቃልና ሌሎችም፡፡

አንዳንድ ጊዜ መጃዙ በመዋቅር ላይ ይሆናል፡፡ ቀጣዩን የአላህ ቃል ይመስል፡-

«የኣደም ልጆች ሆይ! ሀፍተረ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድነረ፡፡ አላህን የመፍራትም ልብስ» (አል-አዕራፍ 7፡ 26)

ልብስ ከሰማይ እሱ ልብስ ሆኖ አለመውረዱ የታወቀ ነው፡፡ ላባም እንደዚሁ፡፡ ነገር ግን አላሁ ተዓላ ዝናብን አወረደ፡፡ ዕፅዋትንም አበቀለ፡፡ እንስሳንም ፈጠረ፡፡ ሱፍም አለበሰው፤ ፀጉርንም ውብርንም (የግመል ፀጉር) ጥጥም አበቀለ፤ የተልባ እግርም ከሱ ልብስ እንዲወሰድ፤ ምክንያት ወደተደረገለት ነገር ተጠጋ፡፡ እሱም ልብሱ ነው፡፡ በምክንያቱ ምትክ እሱም አላሁ ተዓላ ሁሉን ነገር ከሱ ሕያው ያደረገው ውሃ ነው፡፡ «ኢፍዐል» የሚለው ቅርጽ የትዕዛዛዊ ግስ ቅርጽ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ «ላ ተፍዐል» የሚለው ደግሞ የክልከላ፤ ትዕዛዝ በጥቅሉ ግዴታነትን ያመለክታል፡፡ በጥቅሉ ክልከላ ደግሞ እርምነትን ያስጠቅማል፡፡ ያ እሱ የሁለቱመ ቅርጾች የሐቂቃ እውነተኛ አጠቃቀም ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም መጀመሪያ ከተኖረለት መዕና ውጭ ይመጣል፡፡ ትዕዛዝ ተወዳጅነትን አመልክቶ ይመጣል፤ እንደ አላህ አባባል፡-

«ከነሱ መልካምን ነገር ብታዉቁ ተጻጻፏቸው፡፡» (አን-ኑር 24፡33)

መምራት እንደ አላሁ ተዓላን አባባል ይመስል፡-

«ሁለት ምስክሮችን አስመስክሩ» ወይም አባባሉን ይመስል «እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ በዕዳ በተዋዋላችሁ ጊዜ ጻፉት፡፡» (አል-በቀራህ 2፡282)

ዛቻ የአላሁ ተዓላን አባባል ይመስል፡-

«የሻችሁትን ሥሩ (ዋጋችሁን ታገኛላችሁ)፤ እርሱ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና፡፡» (ሱረቱ ፉሲለት 41፡40)

ከዚያም ሌላ፡-

ክልከላም እንደዚያው ከእርምነት ውጭ አመልክቶ ይመጣል፡ እንደመጣላትን ማዋረድን ይመስል፡፡ የአላሁ ተዓላን አባባል ይመስል፡-

«ከነርሱ (ከከሀዲዎች) ብዙዎችን ወገኖች በርሱ ወደአጣቀምንበት ጸጋ ዓይኖችህን አትዘርጋ፡፡» (አል-ሒጅር 15፡88)

ኢርሻድም የአላህን አባባል ይመስል፡-

«ለናንተ ቢገለጹ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ፡፡» (አል-ማኢዳህ 5፡ 11)

ሌሎችም ትዕዛዛዊ ቅርጽ ሌላ ቅርጽ ይዞ እንደሚመጣም ሁሉ፡፡ እንደዚሁ ክልከላም በኸበርና በአፍራሽ ቅርጽ ይመጣል፡፡ ይህ ሁሉ ፉቀሃአቹ

ለመለያየት ተጽዕኖ አለው፡፡ በመንገዶቻቸውም ከማስረጃዎቹ ሸሪዓዊ ሕጎችን በማውጣጣትም፡፡

አንዳንድ ጊዜ የዑለማኦች መዝሀቦች ማስረጃውን በመረዳት ይለያያሉ፡፡ በውስጡ የመጣችው ቃል ሁኔታዎች ስለተለያዩ፡፡ ትርጉሟ እንኳ ባይለያይ በአላሁ ተዓላ አባባል ውስጥ መለያየታቸውን ይመስል፡

«ጸሐፊም ምስክርም (ባለጉዳይ ጋር) አይጎዳዱ፡፡» (አል-በቀራህ 2፡282)

ከፊሎች የተሻበት ችግር ከጸሐፊውም ከመስካሪውም መገኘት ነው ወደማለት ሄዱ፡፡ ያም ጸሐፊው ያልተነገረውን በመጻፍ መስካሪውም ከተጨባጭ በተቃራኒ በመመስከር፡፡ የነዚህ ማስረጃ የኢብኑ ዐብ-ባስ ረዲየሏሁ ዐንሁ ቂራአ ነው፡- «ወላ ዩዳሪር ካቲቡን ወላ ሸሂድ» ሌሎቹ ደግሞ የታሰበው ችግር በነሱ ላይ መድረስ ነው ወደሚለው ሄደዋል፡፡ ከሥራዎቻቸው መከልከልን ይመስል፡፡ በማይመቻቸው ጊዜ ጸሐፊነትንና መስካሪነትን መገደዳቸውን ይመስል፡፡ ወደዚህ የሄደ ሰው ማስረጃው የኢብን መስዑድ ቂራአ ነው፡- «ወላ ዩዳረ ካቲቡን ወላ ሸሂድ» ቃሉ በተሚሞች ቋንቋ የተጨፋለቀ የጠበቀ በሆነ ጊዜ ግሱ ባለቤቱ ለታወቀ ቅርጽና ባለቤቱ ላልታወቀ ቅርጽ መሆኑ ያስመቻል፡፡ ስለዚህ ነው ይህ ልዩነት የመጣው፡፡ የተጨፈለቀውን በትኖ ማንበብ የሒጃዚዮች ቋንቋ ቢሆን እንኳን የዚህን ዓይነት የመለያየት ምክንያቶች የሚከታተል ሰው በሱ ላይ ብዙ ምሳሌዎችን ያገኛል፡፡ ነጠላ በሆኑ ቃላቶችና በተለያዩ የመዋቅር ዓይነቶች ውስጥ በሷ ላይ የሚመጣበትንም ከሁለገብነትና ከልዩ ከስድና ከተገደበ ከጅምላና ከዝርዝር ከዚህም ሌላ፡፡ በዚህ በጠቀስነው ውስጥ የዘጋነው ላይ የሚያቃ አለ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በቦታው ማወቁ ከሚቻለው ሁሉ፡፡

2/ ከሐዲሦች አዘጋገብ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች

ከምክንያቶች ይህ ዓይነቱ ዘርፈ ብዙና የተለያዩ ውጤቶች ያሉት ነው፡፡ ለቀደምት ዑለማኦች የተከሰቱት አብዛኛዎቹ የፊቅህ ልዩነቶች ከሱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሐዲሡ ወደሆነ ተመራማሪ (ሙጅተሂድ) አይደርስም፡፡ በአንድ አንቀጽ ዛሂር ወይም ሌላ ሐዲሥ በሚያስፈርደው ፈትዋ ያደርጋል ወይም ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ብያኔ ባለፈበት መስአላ ላይ ቂያስ በማድረግ፡፡ ወይም በፊት የነበረውን ብያኔ እስከእለት ድረስ እንዲቀጥል በማድረግ ወይም መሠረቱ ነፃነት እና አለ መገደድ ነው በሚለው ተንተርሶ ወይም ከምርምር መንገዶች የቱንም ይዞ ፈትዋ ያደርጋል፡፡

ለጥናት በቀረበው ክስተት ወደሌላው ሙጅተሂድ ተመራማሪ ሐዲሥ ሊደርስ ይችላል፡፡ በሱ መሠረት ፈትዋ ያደርግና የሁለቱ ፈትዋ ይለያያል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሐዲሡ ወደ ሙጅተሂዱ ይደርስና ነገር ግን እሱ በሱ መሠረት ለመሥራት የሚከለክል ምክንያት ያያል፡፡ ሰነዱ ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ድረስ ትክክለኛ አለመሆኑን ማመንን ይመስል፡፡

ያልታወቀ ወይም ተጠርጣሪ ወይም ሸምደዳው (ሒፍዞ) መጥፎ የሆነ ሰው በዘጋቢዎቹ ሰንሰለት ውስጥ ስለተገኘ ወይም ለመቆረጡ ወይም (ሙርሰል) ሰሓቢዩ ያልተጠቀሰ ለመሆኑ፡፡ ወይም በአንድ ፍትሓዊ ሸምዳጅ ሐዲሥ ላይ ሌሎቹ የማይገድቡትን ገደቦች የሚገድብ ለመሆኑ አንዳቸው በሐዲሡ ይሠራል ትክክለኛ መንገድ እሱ ጋ የተቀጠለ ስላለው፡፡ ሌላው ደግሞ በሱ መሠረት አይሠራም፡፡

ከነኚህ ከተወሱት ምክንያቶች አንድ ምክንያት ስላለበት ስለዚህ ንግግሮቹ ይለያያሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የዑለማኦች አባባሎች ይለያያሉ፡፡ አስተያየታቸው በሐዲሡ ትርጉሞችና በሚያመለክተው ነገር ስለተለያየ ያም ንግግሮቻቸው እንደተለያየው ነው በቀጣይ ጉዳዮች ላይ፡፡ አልሙዛበና፣ አል-ሙኻበራ፣ አል-ሙሓቀላ፣ አል-ሙላመሳ፣ አል-ሙናበዛ፣ አል-ገረር ምክንያቱ በማብራሪያው ላይ ስለተለያዩ ነው፡፡

«ሙዛበና» ማለት የተምሩን እሸት በዛፉ ላይ እያለ በደረቅ ተምር መሸጥ ነው፡፡

«ሙኻበራ» መሬትን ለገበሬ በስምምነት መስጠት

«ሙሓቀላ» ቡቃያ መሸጥ፡፡

«ሙላመሳ» የንክኪ ሽያጭ በመንካቱ ብቻ ሽያጩ ይፀድቃል፡፡

«ሙናበዛ» ልብስን መወርወር ወይም ጠጠር በልብሱ ላይ በመወርወር የሚፀድቅ ነው፡፡

«ገራር» መኖር አለመኖሩ ወይም ብዛትና ማነሱ የማይታወቅን መሸጥ ወይም ማስረከብ የማይችለውን መሸጥ፡፡

ሐዲሡ ለከፊላቸው በአንድ መንገድ በሆነ ቃል ሊደርስ ይችላል፡፡ ለሌላ ሙጅተሂድ ደግሞ በተለየ ቃል ሊደርስ ይችላል፡፡ ያም ከሁለት አንዳቸው ከሐዲሡ ትርጉም ያለሱ የማይሞላን ቃል ይጥልን ይመስል ወይመ የሐዲሥ ትርጉም እሱ በመውደቁ ይቀየርን ይመስል፡፡

ሐዲሡ ከመጅተሂዶቹ ወደ አንዱ ከመጣበት ምክንያት ጋር ተቆራኝቶ ሊደርስ ይችላል፡፡ የተታሰበበትን በአግባቡ ይረዳል፡፡ ወደሌላኛው ደግሞ

ከመጣበት ምክንያት ጋር ሳይቆራኝ ይደርሰዋል፡፡ አረዳዱ የተለየ ይሆናል፡፡ አንዱ ዘጋቢ የሐዲሡን ከፊል ይሰማና ሌላው ደግሞ ሙሉ ሐዲሡን ሊሰማ ይችላል፡፡ ሐዲሡን ከመጽሐፍ በተሳሳተ ቃል ወይም በተቀየረ ሊወስድ ይችላል፡፡ በዚያ ላይ ይመሠረታል፡፡

ሌላው ደግሞ ከተጠቀሰው ጉዳይም ምንም ሳይገባበት ይወስደዋል፡፡ በዚያ መሠረት ንግግሮች ይለያያሉ፡፡ ሐዲሡ በሙጅተሂዱ ዘንድ ትክክለኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እሱ ከሱ ይበልጥ ትክክለኛ በሆነው ተጋጭቷል ማለትን ያምናል ወይም የጠነከረ ጠንካራውን ያስቀድማል ወይም ከሁለቱ ማስረጃዎች ጠንካራው የትኛው እንደሆነ ግልጽ ሳይሆንለት ይቀራል፡፡

አንድ ሙጅተሂድ ሐዲሡን የሚሽር ነገር ሊያገኝ ይችላል ወይም ሁለገብነቱን የሚለይ ወይም ገደብ አልባነቱን የሚገድብ ሌላው ሙጅተሂድ ደግሞ ያንን ላያውቅ ይችላል መዝሀቦቻቸው ይለያያሉ፡፡

ከኡሡል ሕጎችና ከማውጣጣት ደንቦች ጋር የሚያያዙ ምክንያቶች

ኡሡለል ፊቅህ በመባል የሚታወቀው የትምህርት ዓይነት እሱ «የፊቅህን ማስረጃዎች በጥቅሉ ማወቅና የአጠቃቀሞቻቸውንም ሁኔታ የተጠቃሚውንም ሁኔታ ማወቅ ነው፡፡»

ይህ የትምህርት ዓይነት ማለት ተመራማሪዎች (ሙጅተሂዶች) የምርምሩንና ከዝርዝር ማስረጃዎቻቸወ ቅርንጫፋዊ የሸሪዓ ሕጎችን የማውጣጣቱን ሥራ መስመር ለማስያዝ ያስቀመጧቸው ሕጎችና ደንቦች ክምችት ነው፡፡ ሙጅተሂዶች በኡሡል ልዩነቶቻቸው ሕጎች የሚወስዱላቸውን ማስረጃዎች ይወስናሉ፡፡ ለየአንዳንዱ ማስረጃነትም ማስረጃ ያመጣሉ፡፡ ለማስረጃዎቹ አካላዊ የሆኑትን ሁለ ባህሪያት ይገልፃሉ፡፡ ከነሱ የሕጎች አወሳሰድ መንገዶች ግልጽ እንዲሆኑ፡፡

ከነዚያ ማስረጃዎች ከያንዳንዱ ማስረጃ የሸሪዓዊ ሕግ አወሳሰድ መንገዶችን ይወስናሉ፡፡ ከመጀመሪያ እስከ ሸሪዓዊ ብያኔው ድረስ የሚከተሏቸውንም እርምጃዎች ጭምር፡፡ እነዚህ ሕጎችና ደንቦች የሙጅተሂዶች መዛሂብ በሷ ላይ ተለያይተዋል፡፡ ከዚህ በሷ ላይ ካለው ልዩነት ሁሉም የሚሄዱበት የፊቅህ መዝሀቦች ልዩነት ተፈጠረ፡፡ ከፊል መሪዎች የሰሓቢይ ፈትዋ ከታወቀና የሚቃረነው ከሌለ ከሰሓባዎቹ ራሳቸው ማስረጃ ነው ይላሉ፡፡ በሰሓቢይ ትክክለኛነት መተማመን ሰሓቢይ ፈትዋ ያደረገውን ነገር ፈትዋ አላደረገም በማስረጃ ላይ ተመሥርቶ እንጅ ወይም ከማስረጃ ተረድቶ ወይም ከረሱል

(ሰ.ዐ.ወ) ሰምቶ ሐዲሡ ያልታወቀ ወይም ወደኛ ያልደረሰ ነው ማለትን ታሳውቃለች፡፡

ከፊሎቹ በሰሓቢይ መዝሀብ ይህን ዓይነት አስተያየት የላቸውም፡፡ ማስረጃው ሰሓቢዩ ከረሱል ሰ.ዐ.ወ) ያወራው እንጅ ለራሱ የሚያስበው አይደለም አሉ፡፡ የፉቀሃኦቹ መዝሀቦችን ይህን መሠረት በማድረግ ይለያያል፡፡ ከፊል ሙጅተሂዶች «መሳሊሐል ሙርሰላን» ይይዛሉ ማለትም እነዚያ በሸሪዓው ውስጥ በራሳቸው ጥቅም ናቸው የሚል ያልተገኘ ጉዳዮች በውስጡ ጥቅም አይደሉም የሚልም እንዳልተገኘ ሁሉ እነሱ ጥቅ ተብለው ከመቆጠርም ካለመቆጠርም ስድ የሆኑ ሙጅተሂዱ በነዚያ ነገሮች ውስጥ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ባገኘ ጊዜ ያንን ጥቅም መሠረት በማድረግ እንደ ማስረጃ ይወስደዋል፡፡ ሻሪዑ እነዚህን ሕጎች ለባሮች ጥቅሞች እንጅ አልደነገገም ማለትን በማየት፡፡

ሌሎች ደግሞ ይህንን የማይይዙ አሉ፡፡ ሕጎች የሚወሰዱለት ነገር ነው ብለው አያስቡትም፡፡ ንግግሮቻቸው በክስተቶች ላይ ይህን መሠረት በማድረግ ይለያያል፡፡ ሌሎች ነገሮችም የዚህ ዓይነት ሙጅተሂዶች የተለያዩበት አለ፡፡ በኡሡለል ፊቅህ መጽሐፎች ውስጥ «አል-አዲለቱል ሙኽተለፉ ፊሃ» በነሱ ጉዳይ የተለያዩባቸው ማስረጃዎች በመባል የሚታወቁ፡፡

«ሰደዘራኢዕ» መንገዶችን መዝጋትና «አልስቲሕሳን» ጥሩ ብሎ መቁጠር «አል-አስቲስሓብ» የመጀመሪያው ፍርድ እንዲቀጥል ማድረግ፣ «አል-አኽዝቢል አሕወጥ» ይበልጥ ለጥንቃቄ የሚረዳውን መያዝ፣ «አል-አኽዝቢል አኸፍ» ቀላሉን መያዝ፣ «አል-አኽዙቢል አስቀል» ከባዱን መያዝ፣ «አልዑፍ» ባህል፣ «አል-ዓዳ» ልምድ ሌሎችም፡፡ ከፊል ማስረጃዎች በሚያመለክቱት ጋር በተያያአዙ ጉዳዮች ላይም ልዩነት እንዳለ ሁሉ፡፡ በነዚያ በሚያመለክቱት መንገዶችም ከነሱ እንደማስረጃ በሚወሰደውም፡፡ ከዚህም ሁሉ በብዙ ዘርፎች ውስጥ የፊቅህ ልዩነቶች ተገኙ፡፡

እነዚህ አስፈላጊና ግልጽ የሆኑ የፊቅህ ልዩነቶች የሚመለሱባቸው ምክንያቶች ናቸው፡፡ ባጭሩ ጠቁመናቸዋል፡፡ እስከ መጨረሻው ሁሉንም ምክንያቶች ማወቅ የፈለገ ሰው ወይም አብዛኛዋን ከነምሳሌዎቿ ይህን ጉዳይ ለመዳሰስ ድሮም አሁንም የተዘጋጁትን መጽሐፎችን ያንብብ፡፡

## ክፍል አምስት

## በመሪዎች መካከል የነበሩት የልዩነት አሻራዎችና ሥርዓቶቹ

አኢማዎቹ በብዙ ኢጅቲሃዳዊ ጉዳዮች ተለያይተዋል፡፡ ሰሓባዎች ታቢዒዮች ከዚያ በፊት እንደተለያዩ ሁሉ እነሱ ባጠቃላይ በቅኑ መመሪያ ላይ

ናቸው፡፡ ልዩነቱ ከዝንባሌ ወይም ፍላጎት ወይም ጥላቻን ከመፈለግ እስካልመነጨ ድረስ፡፡ ከነሱ አንዳቸው የአቅሙንና የሚቻለውን ይለፋ ነበር፡፡ ሐቅን ማግኘትና አላህ ጀል-ለ ሸእኑሁ እንዲወድለት ማድረግ እንጅ ዓላማ የሌለው ሲሆን፡፡ ስለዚህ የዕውቀት ባለቤቶች በሁሉም ጊዜያቶች ውስጥ በኢጅቲሃዳዊ መስአላዎች ውስጥ የሙፍቲዎችን ፈታዋ ይቀበሉ ነበር፡፡

ትክክለኛውን ትክክል እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ለተሳሳተው ከአላህ ምሕረትን ይለምናሉ፡፡ በሁሉም ጥርጣሬን ያሳምራሉ፡፡ የቃዲዎችን ፍርድ ይቀበላሉ፡፡ በየትኛውም መዝሀብ ላይ ቢሆንም፡፡ ቃዲዎች ደግሞ ያስፈለገ ጊዜ ከመዝሀባቸው በተቃራኒ ይሠራሉ፡፡ ምንም ዓይነት ችግር ሳይሰማቸው ወይም ወደ አንድን አባባል ላይጨመድዱ ሁሉም ከዚያው ምንጭ ነው የሚጠጣው፤ ማስረጃዎቹ ቢለዩ እንኳ በብዛት ምርጫዎቻቸው በማለታቸው ይጀምራሉ፡፡

«ይህ ለጥንቃቄ አመች ነው» ወይም «ጥሩ ነው» ወይም «የሚገባው ይህ ነው» ወይም «ይህን እንጠላለን» ወይም «ይህ አይደንቀኝም» አያጣብቡም፤ አይወነጅሉም፤ ማስረጃ ያለውን ሐሳብ አይከለክሉም፤ ይልቁንስ ለሰዎች ማግራት ነው ያለው፡፡

በሰሐባዎችና በታቢዒዮች መካከል፣ ከነሱም በኋላ በስመላን የሚቀራ የሚያነብ ነበረ፡፡ ከነሱም የማያባት አለ፡፡ ከነሱም በሚሰማ ድምጽ የሚያነብ አለ፡፡ ከነሱም በማያሰማ ድምጽ የሚያነብ አለ፡፡ ከነሱም በፈጅር ሶላት ቁኑት የሚያደርግ ነበረ፡፡ ከነሱም የማያደርግ አለ፡፡ ከነሱ በነስርና በትውኪያ በመበጣትም ከነሱም በዚህ ውዱእ የማያደርግ አለ፡፡ ከነሱም ሴት በመንካት ውዱእ መፈታቱን የሚያምን አለ፡፡ ከነሱም ይህን የማይል አለ፡፡ ከነሱም የግመልን ሥጋ ከሙብላት እሳት በቀጥታ ያገኘችውን ከሙብላት ዉዱእ የሚያደርግ አለ፡፡ ከነሱም ይህ ችግር የለውም የሚል አለ፡፡ ይህ ሁሉ ከፊላቸው ከከፊላቸው ኋላ ለመስገድ አልከለከለም፡፡

አቡ ሐኒፋና ባልደረቦቹ ሻፊዒና ሌሎች መሪዎችም ከመዲና ኢማሞች ኋላ ይሰግዱ እንደነበረው ከማሊኪያና ሌሎችም በስመላን በሚሰማም ድምጽ ሆነ በማይሰማ ማንበብ በላያቸው ላይ ግዴታ ባያደርጉም ረሺድ ኢማም ሆኖ አሰገደ እሱ በእርግጥ የተበጣ ሆኖ ፡፡ አል ኢማም አቡ ዩሱፍ ደግሞ ከሱ ኋላ ሰገደ፡፡ ሶላቱንም አልመለሰም እሱ ጋ መበጣት ዉዱእ የሚፈታ ቢሆን እንኳ፡፡

ኢማሙ አሕመድ ኢብኑ ሐንበል ነስርና ዋግምት ዉዱእ ያፈርሳሉ ይሉ ነበር፡፡ ታዲያ ተጠየቁ፡- መሪው ደም ከወጣውና ውዱእ ካላደረገ ከሱ ኋላ ይሰገዳል አሉ፡፡ «እንዴት ነው ከኢማሙ ማሊክና ከሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብ ኋላ

የማልሰግደው» ሻፊዒ ሱብሒን ከአቡ ሐኒፋ መቃብር አጠገብ ሰገዱና ቁኑት አላደረጉም፡፡ ቁኑት እሳቸው ዘንድ የበረታ ሱንና ከመሆኑ ጋር፡፡ ስለዚያ ጉዳይ አሏቸው፡፡ እሳቸውም አሉ፡- «ባሉበት ሆኜ እቃረናቸው እንዴ» መልሰው ብለዋል «ወደ ዒራቅ ሰዎች መዝሀብ ልንወርድ እንችላለን»

ማሊክ አላህ ይማራቸውና የመዲናን ሰዎች ሐዲሥ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከመሪዎች ሁሉ ይበልጥ ያረጋገጡ ነበሩ፡፡ ከኢስናድም ይበልጥ የታመኑ ነበሩ፡፡ የዑመርን ጉዳዮችና የዐብዱላህ ኢብን ዑመርን አባባሎችም፣ የዓኢሻንና የባልደረቦቻቸውን ከሰባቱ ፉቀሃኦች አላህ ለሁላቸውም ይውደድላቸውና ይበልጥ ዐዋቂ ነበሩ፡፡

በሳቸውና በመሰሎቻቸው ዒልመሪዋያና ፈትዋ ተቋቋመ፡፡ በእርግጥም ሐዲሥን አውርቷል፡፡ ፈትዋም አድርገዋል፡፡ መጽሐፋቸውን «አል-ሙወጠእን» ጽፈዋል፡፡ ያ ከሒጃዝ ሰዎች ጠንካራውን ሐዲሥ በውስጡ ማምጣትን ያሰቡበት የሆነ እሳቸው ዘንድ የተረጋገጠውን የሰሓባ ንግግሮችና የታቢዒኦችን ፈትዋዎች እንደዘገቡም ሁሉ እንደፊቅህ ርዕሶችን ርዕሶችን ሰጥተውታል፡፡ ተራውንም አሳምረውታል፡፡

«አል-ሙወጠእ» የኢማሙ ማሊክ የአርባ ዓመት ትግል ፍሬና ውጤት ነው ተብሏል፡፡ እሱ የመጀመሪያ በኢስላም የዘለቀ የሐዲሥና የፊቅህ መጽሐፍ ነው፡፡ በውስጡ ባካተተው ቁምነገር ላይ በጊዜያቸው ከነበሩ የሒጃዝ ዑለማኦች ሰባ ዓሊሞች ተስማምተውበታል፡፡ ከዚሁ ጋር «መንሱር» ብፋ ፍሬዎችን አስጽፎ በከተሞች ላይ ማሰራጨትንና ሰዎችን በውስጡ ባለው ፊቅህ እንዲሠሩ ልዩነትን ለመቁረጥ ማስገደድን የሻ ጊዜ ኢማሙ ማሊክ የመጀመሪያው ተቃዋሚ ሆኑ፡፡ ከሳቸው ቀጣዩን ማለታቸው ተዘግቧል፡-

«አንተ የአማኞች አዛዥ ይህን አትሥራ፤ ሰዎች ብዙ አባባሎች ደርሰዋቸዋል፡፡ ብዙ ሐዲሦችን ሰምተዋል፡፡ ብዙ ዘገባዎችንም ዘግበዋል፡፡ ሰዎች ሁሉ ቀድሞ የደረሳቸውን ይዘዋል፡፡ ከሰዎች ግጭት አመጡት፡፡ ሰዎች ተዋቸው የሁሉም ሀገር ሰዎች ለራሳቸው የመረጡትን ....» ኸሊፋውም አለ፡- «አንተ የዐብደላህ አባት አላህ ይግጠምህ»

ምን ዓይነት ሰው ነው ይህ ታላቅ መሪ ሰዎች እሱ ከሱንና የሰማውን ጥሩ ነገር ያስቀመጠበትን ከዕውቀት የሸመደደውንና የተረዳውን ጠንካራ ነገር ያን በመዲና ሰዎች ዘንድ ልዩነት የሌለበትን በጊዜው ውስጥ ከነበሩት ዑለማኦች ዘንድም ልዩነት የሌለበትንበውስጡ ያስቀመጠውን መጽሐፉን በግድ እንዳይሠሩበት ይቃወማል፡፡

የለይሥ ኢብን ሰዕድ መልዕክት ወደ ኢማሙ ማሊክ

ከልዩነት ሥርዓት በላጭና ጥሩ ምሳሌዎች ያቺ የዕውቀት አስደናቂ ደብዳቤ ነች፡፡ ያቺ የግብጽ ፊቂህና መሪዋ ዐዋቂዋ አለይሥ ኢብኑ ሰዕድ ወደ ኢማሙ ማሊክ የላካት በውስጧ አስተያየታቸውን እያቀረቡ በብዙና ከፍ ባለ ሥርዓት ታጅቦ ብዙ ኢማሙ ማሊክ የሚሄዱበትና አለይሥ ኢብኑ ሰዕድ ደግሞ ይቃረኗቸው በሆኑበት ጉዳዮች ዙሪያ፡፡ መልዕክቱ ረጅም ስለሆነ ያንን ከፍ ያለ ሥርዓት የሚያሳየውን ክፍል እናቀርባለን፡፡ ያ የዚህ ኡምማ ቀደምቶች በጥላው ሥር የተለያዩበት የተከበሩትም ዑለሞቿ ለይስ ኢብኑ ሰዕድ ይላል፡-

«ሰላም ባንተ ላይ ይሁን፡፡ እኔ ያንን ከሱ በስተቀር በእውነት የሚያመልኩት የሌለውን ጌታ አመሰግናለሁ፡፡ ካሁን በኋላ እኛንም አንተንም ደህና ያድርገን፡፡ በቅርቢቱም ዓለም በመጨረሻይቱም ዓለም አላህ መጨረሻውን ያሳምርልን፡፡ መጽሐፍህ ደርሶኛል፡፡ በውስጡ ያንን የሚያስደስተኝን የሁኔታችሁን መስተካከል የምታወሳበትን ያንን ለናንተ ያዘውትርላችሁ፡፡ በእርዳታ ይሙላውም፡፡ በማመስገኑና ከበጎው በመጨመሩ ...

ከዚያም ይላል፡-

«ነገሩ ደርሶሀል፡፡ እኔ እናንተ ዘንድ ሰው ባለበት ተቃራኒ በሆኑ ነገሮች ለሰዎች ፈትዋ የማደርግ መሆኔ፤ እኔም በራሴ ላይ መፍራት እንዳለብኝ፡፡ ሰዎች የመዲናን ሰዎች ተከታዮች ናቸው፡፡ ያቺን ሂጅራ ወደሷ የሆነውን አገር ቁርአንም በሷ ላይ ወርዶ ስለሷ ስለዚያ የጣፍከው ትክክል ነው፡፡ እኔ ጋ እንደምትወደው ነው የሆነው፡፡ አንድንም ከዐዋቂዎች የሚቆጠር ለብቻ የሆኑ ፈትዋዎችን የሚጠላ አላገኘም፡፡ ያለፉትንም የመዲና ዑለማኦች ይበልጥ የሚያከብርም በተስማሙበትም ፈትዋቸውን ይበልጥ የሚይዝ ከኔ ይበልጥ ምስጋና ለአላህ ለዓለማቱ ጌታ ይገባው አጋር የሌለው ሲሆን»

ከዚያም ኢማሙ ለይስ ኢብኑ ሰዕድ በደብዳቤው ይቀጥላል፡፡ በሱና በኢማሙ ማሊክ መካከል ያሉትን የልዩነት ዓይነቶች እያመጣ፡፡ በመዲና ሰዎች ሥራ ማስረጃነት ዙሪያ የገለፀ ሲሆን ከመጀመሪያዎቹ ቀደምቶች ብዙዎች እነዚያ ከነብዩ ት/ቤት የተመረቁ ወደ ምድር ምስራቆችና ምዕራቦች ተሸከመዋል፡፡ እነሱ ጂሃድ እያደረጉ ከአላህ መጽሐፍ እና ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሥ ታቢዒዮችም በብዙ ጉዳዮች መለያየታቸውን ገልጸዋል፡፡ እንደዚሁም ከነሱ በኋላ የመጣም እነ ረቢዐቱ ኢብኑ አቢ ዐብዱረሕማንን ይመስል ከፊል በሱ ላይ የያዛቸውን ነጥቦች ያወሳል፡፡ ከዚያም ይላል፡-

«ከዚያም ጋር ለአላህ ምስጋና ይገባውና ረቢዓ ጋር ብዙ በጎ ነገሮች አሉ፡፡ መሠረታዊ የሆነም አዕምሮ ጮሌ የሆነ ምላስ ግልጽ የሆነ ደረጃ በእስልም ጥሩ የሆነ አካሄድ ለወንድሞቹ እውነተኛ የሆነ ፍቅር ለኛ በተለይ አላህ ይማረው በሥራው በጎ ነገር አላህ ይመንዳው»

ከዚያም በሱና በኢማሙ ማሊክ መካከል የልዩነት ምሳሌዎች ያወሳል፡፡ ብዙ ጉዳዮችን በዝናብ ሌሊት ሶላትን መሰብሰብን ይመስል፡፡ በአንድ ምስክርና በመሐላ መፍረድን ይመስል፡፡ እጅ በጅ ያልሆነ የመሕር ገንዘብ የፍቺ ጊዜ እንጅ አይወሰድም፡፡ ኢስቲስቃእ ዝናብ ለመጥፋት የሚሰገደው ሶላት ላይ ሶላቱን ከኹጥባ ማስቀደምን ይመስል፡፡ ሌሎችም የልዩነት ጉዳዮች፡፡ ከዚያም በደብዳቤው መጨረሻ ላይ አለ፡-

«ይህን የሚመስሉ በርካታ ነገሮችን ትቻለሁ፡፡ እኔ አላህ አንተን እንዲገጥምህ እወዳለሁ፡፡ የመኖርህንም ርዝመት ለሰዎች በዚያ ነገር ጥቅምን ተስፋ ስለማደርግ፡፡ የአንተ ዓይነት የጠፋ እንደሆን ከጥፋት ስለምሰጋ በመኖርህ ከመደሰቴ ጋር ሀገሩ እንኳ ቢርቅ ይህ እኔ ጋ ደረጃህ ነው፡፡ ባንተ አስተያየቴም ነው፡፡ አረጋግጠው ወሬህን ወደኔ መጻፍህን አትተው፡፡ ሁኔታህንና የልጅህን የቤተሰብህንም ጉዳይህንም ጉዳይ ካለህ ወይመ ካንተ ጋር ለተያያዘ ማንም ሰው እኔ ያ ነገር ደስ ይለኛል፡፡ ይህን የጻፍኩልህ እኛ በደህና እያለንነው፤ ምስጋና ለአላህ ይገባው፤ አላህን እንለምናለን፤ እኛንም እናንተንም በሰጠን ማመስገንን እንዲለግሰን በሱ በኛ ላይ ባጣቀመው መሙላትንም ሰላም በናንተ ላይ ይስፈን፤ የአላህ ርኅራሄም»

በልዩነት ሥርዓት የተሞሉ በርካታ ሳይንሳዊ የረቀቁ ውይይቶች የሕይወት ታሪክና የታሪክ የክርክርና መሰል መጽሐፎች የሰበሰባቸው አሉ፡፡ አንድ ሰው የልዩነትን ሥርዓት በዕውቀት ባለቤቶች መካከል ሊያጣ አይቀርብም በጭፍን መከተልና ከሱ ጋር የተጎዳኘው በዒልም ባለቤቶች ባህሪና ወደ ዕውቀቱ ራሱ ያላቸው ዕይታ ከወገንተኝነትና ከእንቅፋት ከተሰራጨ በኋላ እንጅ፡፡ በተለይ ሜዳው ኢማሙል ገዛሊ ከሚላቸው ዑለማኦች አምሳያ ካገለለ በኋላ፡፡ «ከታቢኦቹ ዑለማኦች በመጀመሪያው ዓይነት የዘወተረና ጥርት ያለውን ዲን የተያያዘ በቀደምት ዑለማኦች ባህሪ የቀጠለ ቀርቶ ነበር፡፡ በተፈለጉ ጊዜ ይሸሹና ይዞሩ ነበር፡፡»

ኹለፋኦች በነሱ ፍለጋ ላይ ችክ ለማለት ተገደዱ፡፡ ዳኝነትና የመንግሥት ሰልጣኞች ላይ ለመሾም፡፡ በዚህ በተባረከ ትውልድ ቦታ ዱንያን በዲን የሚፈልግ ሰፈራ ያ ዝቅ ያለው ሰፈራ በዚያ እሱ በተሻለው ቦታ በዚህ ጉዳይ ላይ ኢማሙል ገዛሊ ይላሉ፡-

«የነዚያ ጊዜያቶች ሰዎች አዩ፡፡ የዑለማኦቹን ክብደት መሪዎችና ባለሥልጣኖች ወደነሱ መዞራቸውን ከነሱ የዞሩ ከመሆናቸው ጋር፡፡ ዕውቀትን ለመፈለግ አንገቶቻቸውን ቀና ቀና አደረጉ፡፡ ክብርን ለማግኘት ከባልስልጣኖቹ ዝናን ለማግኘት በፊትዋ ዒልሞች ላይ ተደፉ፡፡ ነፍሶቻቸውን ለሹማምንቶቹ አቀረቡ፡፡ ተዋወቋቸውም፡፡ ሹመቶችንና ከነሱ ጋር ግንኙነቶችን ጠየቁ፡፡ ከነሱ የተሳካለት አለ፡፡ የተሳካላትም ከልመና ውርደትና ከመተናነስ ውርደት አልዳነም፡፡ ፉቀሃኦች ተፈላጊ ከሆኑ በኋላ ፈላጊ ሆኑ፡፡ ከባለሥልጣኖች በመዞር የተከበሩ ከሆኑ በኋላ ወደነሱ በመዞር ተዋረዱ፡፡ አላሁ ተዓላ የገጠመው ብቻ ሲቀር ከአላህ ሃይማኖት ምሁራኖች በሁሉም ጊዜያቶች»

ኢማሙል ገዛሊ የዑለማኦችን ተጨባጭ ዱንያ ታርጌታቸው ከሆነች በኋላ ዲን ብቸኛ ወደባለስልጣኖች በር የሚያደርስ በር ከሆነ በኋላ የነሱን ፍቅር የማትረፍ ፍላጎት የምሁራኖቹን ቅርጽ የሚይዙትን ጭፍሮች ወደዒልም መፈለግ የሚገፋ እንደሆነ በእርግጥ ስሎታል፡፡

ኢማሙ ማሊክ አላህ ይማራቸውና ይላሉ፡- «ይህ ዕውቀት ከአራት ሰዎች አይወሰድም፤ ከነሱ ውጭ ከሆነ ይወሰዳል፡፡ ከቂል አይወሰድም፡፡ ወደፈጠራው ከሚጣራው የዝንባሌ ባለቤትም አይወሰድም፡፡ በሰዎች ወሬዎች ውስጥ ከሚዋሽ ቀጣፊም፣ በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሥ ላይ ባይጠራጠር እንኳ፤ ደረጃና ጥሩ ሰውነት ጥሩ ዒባዳ ካለው ሰውም የሚሸከመውንና የሚያወራውን የማያውቅ የሆነ ጊዜ፡፡» ደግሞም ብለዋል፡- «ይህ ዕውቀት ሃይማኖት ነው፤ ሃይማኖታችሁን ከማን እንደምትይዙ ተመልከቱ፡፡ በእርግጥ ሰባ የሚሉ ሰዎችን አግኝቻለሁ፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- እነኚህ ታማኞች ዘንድ (ወደ ረሱል /ሰ.ዐ.ወ/ መስጂድ አመለከቱ) ምንም ነገር ከነሱ አልወሰድኩም፤ አንዳቸው በግምጃ ቤት ኃላፊ ቢሆን ታማኝ የሚሆን ነገር ግን እነሱ ከዚህ ነገር ሰዎች ያልሆኑ ኢብኑ ሺሃብ ወደኛ በመጣ ጊዜ በበሩ ላይ እምንጋፋ ሆን»

ባህሪዎቻቸው እንዲህ የሆኑ ሰዎች በመካከላቸው ትልቅ ልዩነት አይከሰትም፡፡ ከተከሰተም ለእውነታ ተብሎ ነው፡፡ ዝንባሌ ደግሞ አፍንጫውን ከሐቅ ውጭ ወደሱ የማይጠራ ልዩነት ውስጥ አያስገባም፡፡ የተከበሩት ዑለማኦቻችን በመንገዷ ላይ የሄዱባቸውን ሥርዓቶች መሠረት እንድናደርግ እነሱን ለኛ ጥሩ አርአያ እንድናደርግ እነኛ የተከበሩ ባህሪዎቻቸው የምንከተላቸው ምሳሌዎች እንዲሆኑ ከጥሩ ቀደምት ሰለፎች በታላላቅ መሪዎች መካከል ከነበሩት የልዩነት ሥርዓት ናሙናዎች እናቀርባለን፡፡

አቡ ሐኒፋና ማሊክ

የመሪዎችን መዝሀቦች ስናቀርብ በአቡ ሐኒፋና በማሊክ መካከል የነበረውን ታላቅ ልዩነት አሳልፈናል፡፡ ሁላቸውም መዝሀቡን በመተመለከተ የሚሞረከዟቸው መሠረቶች መለያየታቸውንም ነገር ግን ይህ በመካከላቸው ካለው የዕድሜ ልዩነት ጋር አልከለከለም፡፡ አንድኛው ሌላውን ማክበር አብሮት ከታላቅ ሥርዓት ጋር ከመሆን በፊቅህ አካሄዳቸው የተለያየ ከመሆኑ ጋር ቃዲ ዒያድ «አል-መዳሪክ» በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ዘግበዋል፡፡ እሳቸውም አሉ፡- «ለይሥ ኢብኑ ሰዕድ አለ፡- ማሊክን በመዲና አገኘሁትና አልኩት፡- እኔ ላብን ከግንባርህ ላይ ስታብስ አይሃለሁ አለ፡፡» አቡ ሐኒፋ ጋር ስለሆንኩ ነው ያላበኝ አንተ ግብፃዊ እሱኮ በእርግ ፈቂህ ነው፡፡ ለይሥ አለ፡- ከዚያም አቡ ሐኒፋን አገኘሁት፡፡ አልኩትም፡- ይህ ሰው ስለአንተ ምን ዓይነት ጥሩ ነገር ያወራል! (ወደማሊክ እያመለከተ) አቡ ሐኒፋም አሉ፡- ከሱ ይበልጥ በእውነተኛ መልስና ሙሉ በሆነ ትችት የፈጠነ አላየሁም፡፡

**ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን እና ማሊክ**

ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን ከአቡ ሐኒፋ ተማሪዎች ይበልጥ የታወቀ ነው፡ ፡ እሱ የመዝሀቡ ሰብሳቢ ነው፡፡ ወደ ማሊክ ሄደና ሦስት ዓመት አብሯቸው ቆየ፡፡ «ሙወጣእን» አዳመጠ፡፡ አንድ ቀን ሁለቱ መሪዎች ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰንና ሻፊዒ አንድ ላይ ያጠናሉ፡፡ ሙሐመድ አሉ፡- «መምህራችን (አቡ ሐኒፋን ሽቶ ነው) ከናንተ መምህር ይልቅ ዐዋቂ ነው (ማሊክን ሽቶ ነው)፡፡ የኛ መምህር ዝም ማለት የለበትም፡፡ የናንተ መምህር ደግሞ መናገር የለበትም - ልክ በዚህ ጉዳይ ኢማሙ ሻፊዒን የሚያማክር ይመስል፡፡» ኢማሙ ሻፊዒ አሉ፡- «በአላህ ይዤሃለሁ ማነው የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ይበልጥ የሚያውቀው ማሊክ ወይስ አቡ ሐኒፋ» ሙሐመድ አለ፡- «»ማሊክ ነገር ግን አቡ ሐኒፋ ይበልጥ ቂያስ ይችላሉ፡፡ ሻፊዒ ይላሉ፡- አዎ አልኩኝ፡ ማሊክ ከአቡ ሐኒፋ ይበልጥ የአላህ መጽሐፍ ያውቃሉ፡፡ የአላህን መጽሐፍና የረሱልን ሱንና ይበልጥ የሚያውቅ ለመናገር የተሻለ ይሆናል፡፡ አል-ኢማም ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን ዝም አሉ፡፡

**ሻፊዒና ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን**

ኢማሙ ሻፊዒ እንዲህ ይላሉ፡- አንድ ቀን ከሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን ጋር አጠናን፡፡ በኔና በሰ መካከል ንግግርና ልዩነት ተፈጠረ፡፡ ወደ ደም ቧንቧዎቹ ስመለት ምታቸው እስከጨመረ ድረስ ቁልፎቹም እስከተበጣጠሱ ድረስ፡፡ ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን ይላል፡- «»ማንም ሰው ከኛ የሚለያይ ልዩነቱ ደግሞ በኛ ላይ የሚጸድቅብን ሰው ቢኖር ሻፊዒ ነው ለምን አሉት አለ ለገለፃውና በጥያቄውና በመልሱ በማዳመጡ ጠንቃቃ ስለሆነ፡፡

እነኚህ እነሱ ከኡምማው ዑለማኦች ሥርዓቶች የልዩነት ሥርዓት ከፊል ናሙናዎች ናቸው፡፡ ከነሷ ቀጣዩን እናውጣጣለን፡-

በጥሩ ክ/ዘመናት የኡምማው ኋላ ቀደምቶችን ተከትሎ ይጓዝ ነበር፡፡ ሁሉም ከነብይነት ሥርዓት ነው ምንጩ፡፡ የጥሩ ቀደምቶች ሥርዓት ሰውን ከማቁሰልና ከማራከስ መራቅ ላይ ብቻ ያጠረ አልነበረም፡፡ ይልቁንስ ከዑለማኦች በዚያ ትውልድ ከተሰራጩት ሥርዓቶች ዕውቀትን ሲማሩ ማረጋገጥና በማያውቁት ነገር መዘባረቅን መራቅ ነበር፡፡ ስህተት ላይ መውደቅን በመፍራት ፈትዋን መራቅ ላይ በመጓጓት የቁት ባለቤት አለ፡፡ ከዐብዱረሕማን ኢብን አቢ ለይላ ተነገረን አለ፡ ፡ በዚህ መስጂድ ውስጥ አግኝቻለሁ (በረሱል /ሰ.ዐ.ወ/ መስጂድ ውስጥ) መቶ ሀያ የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሰሓባ ከነሱ አንድም ከሐዲሥ ወይም ከፈትዋ የሚጠየቅ የለም ወንድሙ ያንን ቢመልስለት እንጅ የሚወድ ቢሆን እንጅ፡፡ በሌላ አባባል ደግሞ ጥያቄዋ ወደ አንዳቸው ትቀረብና ወደሌለኛው ይመልሳት ነበር፡፡ ሌለኛው ደግሞ ይመልሳታል ወደሌለኛው በመጀመሪያ ወደጠየቃት ሰውዬ እስከምትመለስ ድረስ፡፡

እነዚህ ሰዎች ከህፍረት ስሜቶች ስሜት በላይ ወጥተዋል፡፡ አንዳቸው አንድ ጥያቄ ፊት ይቆሙ ነበር ወንጀልን ፈርተው፡፡ ከዚህ ጭምርት ነው አንድ ሰው ማሊክ ኢብኑ አነስን ስለሆነ ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡ ወገኖቹ ይህን እንዲጠይቅ የስድስት ወር ጉዞ ከሚሆን ቦታ እንደላኩትም አወሳላቸው፡፡ ማሊክ አሉ፡- ያን የላከህን እኔ መልሱን እንደማላውቅ ንገረው፡፡ ሰውየው አለ ማነው የሚያውቃት ታዲያ ማሊክ አሉ አላህ ያሳወቀው ነው መላእክቶች አሉ፡፡

«ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም፡፡» (አል-በቀራህ 2፡ 32)

ከማሊክ አሁንም ተዘግቧል እሳቸው ከአርባ ስምንት ጥያቄዎች ተጠየቁ፡፡ ከነሱ በሠላሣ ሁለቶቹ አላውቅም አሉ፡፡

ከኻሊድ ኢብኑ ኺዳሽ ተወራ አለ ከዒራቅ ወደ ማሊክ አርባ ጥያቄዎችን ይዤ መጣሁ፡፡ ስለነሱም ጠየቅኩት፡፡ ከነሱ በአምስቶቹ ጥያቄዎች ላይ እንጅ አልመለሰም፡፡

ኢብኑ ዐጅላን ይል ነበር፡- ምሁሩ (ዓሊሙ) አላውቅም ማለትን የሳተ ጊዜ የሚገድል ቦታ ላይ ተመታ ማለት ነው፡፡

ከማሊክ ከዐብዱላህ ኢብን የዚድ ኢብኑ ሁርሙዝ ተወርቷል፡- ለአንድ ዓሊም ተገቢ ነው፤ አቀማማጮቹን አላውቅም ማለትን ማስወረስ ያ በእጆቻቸው ላይ የሚሸሹበት መሠረት እንዲሆንላቸው አንዳቸው የማያውቀውን ነገር በተየጠቀ ጊዜ አላውቅም እንዲል፡፡ አቡ ዑመር ኢብኑ ዐብዱል በርአለ (463 ዓ.ሂ ሞተ)

ከአቡ ደርዳእ በትክክል ተዘግቧል እሳቸው ማለታቸው አላውቅም ማለት የዕውቀት ግማሽ ነው፡፡

**ማሊክና ኢብኑ ዑየይና**

ኢብኑ ዑየይና የማሊክ ጓደኛና ባልደረባው ነበር፡፡ ኢማሙ ሻፊዒ ይላል፡ - ማሊክና ኢብኑ ዑየይና ጓደኛሞች የሆኑት ማሊክና ኢብኑ ዑየይና ባልነበረ የሒጃዝ ዕውቀት ይጠፋ ነበር» ከዚሁ ጋር ተዘግቧል፡- አንድ ጊዜ ኢብኑ ዐይየና ሐዲሥ አወራና አሉት፡- ማሊክ ደግሞ በዚህ ሐዲሥ ላይ ካንተ ይለያል ባዩ አለ ከማሊክ ጋር ታቆራኘኛለህ እኔና ማሊክ እኮ ጀሪር እንዳለው እንጅ አይደለንም፡፡

ሦስተኛ ዓመቱን የጀመረ የግመል ግልገል ከሌላ ጋር በገመድ ተቆራኝቶ ሲታሰር ጠንካራ የሆኑ የስምንት ወይም የዘጠኝ ዓመት ግመሎች ጋር መዝለል አይችልም፡፡

ለሱፍያን ኢብኑ ዑየይና የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አባባል ይነገራቸዋል፡፡ «ሰዎች የግመሎችን ጉበቶች በዒልም ፍለጋ ሊመቱ ይቀርባል፡፡ በመዲና ላይ ካለው ዒልም ይበልጥ አዋቂ የማይገኝ ሆኖ» ለሱፍያን ይባለዋል ማነው እሱ ይላል እሱማ ማሊክ ኢብኑ አነስ ነው ይላልም፡- «ከሐዲሦች ትክክለኛውን እንጅ አያስተላልፍም ነበር፡፡ ሐዲሥንም ከታማኝ ሰዎች እንጅ አይይዝም ነበር፡፡ መዲና ማሊክ ኢብኑ አነስ ከሞተ በኋላ የምትበላሽ እንጅ አይመስለኝም፡፡»

**ማሊክና ሻፊዒ**

ኢማሙ ሻፊዒ ይላሉ፡- «ማሊክ ኢብኑ አነስ አስተማሪዬ ነው፡፡ ከሱ ነው ዕውቀትን የወሰድኩት፡፡ ዑለማኦች የተወሱ ጊዜ ማሊክ ነው ኮኮቡ፡፡ ማንም ሰው ሊመጣደቅብኝ የሚገባ የለም ከማሊክ ኢብኑ አነስ የበለጠ፡፡» ይሉም ነበር፡፡ ሐዲሥ ከማሊክ ዘንድ ከመጣልህ በሁለት እጆችህ አጥብቀህ ያዘው፡፡ ማሊክ ኢብኑ አነስ በሐዲሥ የተጠራጠረ ጊዜ ሁሉንም ይጥለው ነበር፡፡

**አሕመድ ኢብኑ ሐንበልና ማሊክ**

ከአቡዙርዓ አዲመሽቂ ተወራ አለ፡- አሕመድ ኢብኑ ሐንበልን ከሱፍያንና ከማሊክ በዘገባ የተለያዩ ጊዜ የማን ይይዛል ተብሎ ሲጠየቅ አለ ማሊክ በልቤ ላይ ታላቅ ነው አለ፡፡ አውልኩኝ ማሊክና አውዛዒስ የተለያዩ ጊዜ? አለም ማሊክ እኔ ጋ ይበልጥ የተወደደ ነው፡፡ አውዛዒ ከመሪዎቹ ቢሆን እንኳ አሉት ኢብራሂምስ (ነኻዒ) ኢብራሂም ከማሊክ ጋር መቆራኘት የለበትም ማለትን የሚያምን ይመስላል፡፡ እሱ ከሐዲሥ ሰዎች ስላላደላ አለም ይህንን ከጊዜው ሰዎች ጋር

አድርገው፡፡ የተለዩ የአንድን ሰው ሐዲሥ መሸምደድ የሚሻን ሰው ተጠየቀ፡፡ አሉት የማንን ሐዲሥ ትመርጥለታለህ? የማሊክን ሐዲሥ ይሸምድድ አለ፡፡

### የከፊል ዑለማኦች አስተያየት በአቡ ሐኒፋ ላይ

ሹዕበቱ ኢብኑል ሐጃጅ በሐዲሥ መስክ የአማኞች አዛዥ ነበረ፡፡ አቡ ሐኒፋ ደግሞ በዚያ ባወቅነው ደረጃ ከራዕይ ባለቤቶች ነበረ፡፡ የሁለቱ አካሄድ ከመለያየት ጋር ሹዕባ ሲበዛ አቡ ሐኒፋን ያከብሩ ነበር፡፡ በመካከላቸው ውዴታና መላላክ ይሰበስባቸው ነበር፡፡ የአቡ ሐኒፋን ታማኝነትም ያረጋግጥ ነበረ፡፡ ሐዲሥ እንዲያወሩም ይጠይቃቸው ነበረ፡፡ የሞታቸውን መርዶ በደረሳቸው ጊዜ እንዲህ አለ፡- «በእርግጥ አብሮት የኩፋ ፊቅህ ሄደ፡፡ አላህ ለኛም ለርሱም ርኅራሄውን ይቸረን» እና

አንድ ሰው የሕያ ኢብኑ ሰዕድ ኢብኑል ኸጣንን ስለአቡ ሐኒፋ ጠየቀ፡፡ እሱም እንዲህ አለ፡- «አላህ ዘንድ አይሸላለምም፡፡ አላህ ዐዝ-ዘ ወጀል በማያውቀው ነገር እኛ በአላህ ይሁንብኝ ከንግግሩ የሆነን ነገር ጥሩ ነው ብለን ካየነው እንይዛለን፡፡ »

እንደዚሁም ልዩነትና አስተሳሰቦች አለመስማማት አንድንም በጓደኛው ዘንድ ጥሩ የሚለውን ከመያዝና በዚህ ነገር ደረጃውን ከማውሳት ንግግሩን ወደሱ ከማስጠጋት አይከለክልም ነበረ፡፡

ከዐብደላህ ኢብኑል ሙባረክ በርካታ ዘገባዎች አሉ፡፡ አቡ ሐኒፋን በማወደስ፡፡ ከሳቸው በጎን ነገር ሁሉ ያወራ ነበረ፡፡ ያወድሰውም ነበረ፡፡ ከንግግሩ ይወስድም ነበረ፡፡ ያሞግሰውም ነበረ፡፡ ለአንድም ሰው በመስጂድ ውስጥ እንዲነካው አይፈልግም ነበረ፡፡ አንድ ቀን ከፊል አቀማማጮቹ አቡ ሐኒፋን ሊያወግዙ ሞከሩ፡፡ አለውም ዝም በል በአላህ ይሁንብኝ አቡ ሐኒፋን ብታይ ኖሮ አዕምሮንና ጮሌነትን ታይ ነበረ፡፡

ከኢማሙ ሻፊዒ እንዲህ ማለታቸው፡- አንድ ቀን ማሊክ ስለዑሥማን አል-ቡቲ ተጠየቁ፡፡ አሉም መካከለኛ ሰው ነበረ፡፡ ስለኢብን አቢ ሱብሩማም ተጠየቁና አሉ፡- መካከለኛ ሰው ነበረ ተባለ፡፡ አቡ ሐኒፋስ? ወደዚህ ምሰሶዎቻቸው ቢመጣ (የመስጂዱን ምሰሶዎች ሸተው ነው) እንጨቶች ናቸው ብሎ ቢከራከራችሁ እነሱ እንጨቶች ናችሁ ብላችሁ ትጠራጠሩ ነበር፡፡ በክርክር ጮሌነታቸው እየጠቆሙ፡፡ ኢማሙ ሻፊዒማ ማለታቸው ከሳቸው መዘገቡን ምን አመዛው (ሰዎች በፊቅህ የአቡ ሐኒፋ ቤተሰቦች ናቸው»

የነዚህ ሰዎችመቀመጫዎች በጎ ነገር እንጅ አይወሳባቸውም ነበር፡፡ ከዚሁ ኡምማ መሪዎች ጋር መጠባበቅ ግዴታ የሆነበትን ሥርዓቶች መተላለፍ የሞከረ

ሰው ወደትክክለኛው መንገድ ይመለሳል፡፡ በሱንና አንድም በሚጠላው በመንካት መካከል ይጋረዳል፡፡

ፈድል ቢን ሙሳ አስ-ሲናኒ የተባሉት  ተጠየቁ፡፡ ስለነዚህ አቡ ሐኒፋን የሚተቹ ሰዎች ምን ትላለህ? አለ፡፡ አቡ ሐኒፋ ከዕውቀት የሚረዱትንና የማይረዱትን ይዞላቸው መጣ፡፡ ምንም ነገር አልተወላቸውም፡፡ ተመቀኙት፡፡

እነዚህ ከሐዲሥ መሪዎች የተዘገቡ ከፊል አባባሎች ናቸው፡፡ ለአቡ ሐኒፋ ከሄዱበት አብዛኛው ጉዳይ ከሳቸው የተለዩ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከሳቸው ጋር መለያየታቸው እሳቸውን ከማሞገስና ከማወደስ ከበጎ ነገር እሳቸው ባለቤቱ የሆኑትን ከማውሳት አልከለከላቸውም፡፡ ያም በነሱና በሱ መካከል ያለው ልዩነት ከዝንባሌ የመነጨና የበላይነትንም መፈለግ አለመሆኑን ስለተማመኑ ነው፡፡

ይልቁንስ ሐቅን መፈለግ ሁሉንም የጠፋ ጉዳይ ነበር - አላህ ይማራቸውና - እነኚህ የተከበሩ ሥነ-ምግባሮች ታላቅ ሥርዓቶች ባልነበሩ የብዙዎቹ ፊቅህ ከጥሩ ቀደምቶቻችን ይጠፋ ነበር፡፡ ከማንም ሰው አይከለክሉም ነበር፡፡ በዚያ ነገር ውስጥ የዚህን ኡምማ ፊቅህ ሕይወቷ በሱ ጥላ ሥር እንጅ የማይስተካከለውን መጠበቅ አለበት ማለትን ስለሚያውቁ እንጅ

**በሻፊዒይ የከፊል ዑለማኦች አስተያየቶች**

ኢብኑ ዑየይና እሱ በደረጃው ማን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከተፍሲር እና ከፈትዋ የሆነ ነገር ሲመጣበት ወደ ሻፊዒ ይዞር ነበር፡፡ ይልም ነበር፡- ይህንን ጠይቁ፡፡ በብዛት ያየው ጊዜ ይል ነበር፡- ይህ ከጊዜው ወጣቶች በላጭ ነው፡፡

የሻፊዒ የሞት መርዶ በደረሰው ጊዜ አለ፡- ሙሐመድ ቢን እድሪስ ከሞተ በእርግጥ ከጊዜው ሰዎች በላጩ ሰው ሞተ ማለት ነው፡፡

የሕያ ኢብኑ ሰዕድን አል-ቀጣን ይል ነበር፡- እኔ ለሻፊዒ በሶላቴ ውስጥ እንኳ ዱዓ አደርግለታለሁ፡፡

ዐብደላህ ኢብኑ ዐብደል ሐከምና ልጁ በኢማሙ ማሊክ መዝሀብ ላይ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ይህ ዐብደላህ ኢብኑ ዐብዱል ሐከምን ልጁን ሙሐመድን ኢማሙ ሻፊዒን በመያዝ አደራ ከማለት አልከለከልም ብሎታልና፡፡ ይህን ሸይኽ ተያያዥ (ሻፊዒን ሽቶ ነው)አንድንም በዕውቀት መሠረቶች ወይ አለ፡፡

ከፊቅህ መሠረቶች ከሱንና ያረጋገጠ አላየሁም ልጁ የአባቱን ምክር የያዘ ይመስላል ይላልና ሻፊዒ ባልነበረ በአንድም ሰው ላይ እንዴት እንደሚመልስ አላውቅም ነበረ፡፡ በሱ ነው ያወኩትን ያወኩት፡፡ እሱ ነው ቂያስን ያስተማረኝ - አላህ ይማረውና፡፡ በእርግጥም የሱንና እና የሐዲሥ የደረጃና የበጎ ሰው ነበረ፡፡ ከጮሌ ምላሱ ጋር ከትክክለኛ አጥብቆ ተረጂ አዕምሮ ጋር፡፡

**በኢማሙ አሕመድና በኢማሙ ሻፊዒ መካከል**

ከዐብደላህ የኢማሙ አሕመድ ልጅ ተወራ እሱም አለ ለአባቴ አልኩት ሻፊዒ ማለት ምን ዓይነት ሰው ነበረ? እኔ አንተ ለሱ ዱዓ ስታበዛ እሰማሃለሁና አለም አንተ ልጄ ሆይ! ሻፊዒ አላህ ይማረውና ለዱንያ እንደ ፀሐይ ለሰዎች እንደ ጤንነት ነበረ ተመልከት እስቲ ለነዚህ ለውጥ ወይም ምትክ አላቸውን?

ከሷሊሕ የኢማሙ አሕመድ ልጅ ተወራ አሉም የሕያ ኢብኑ መዕን አገኘኝና አለ፡- አባትህ ከሚሠራው ድርጊት አያፍርም አልኩም ምንድነው የሚሠራው አለም ከሻፊዒ ጋር አየሁት፡፡ ሻፊዒ ጋልቦ እሱ በእግሩ እየሄደ የእንስሳዋን ገመድ ይዞ፡፡ ያንን ለአባቴ ነገርኩት፡፡ አለም ካገኘሀሁ አባትህ ይልሀል በለው ፊቅህን ማወቅ ከፈለክ ና እና በሌላ በኩል እርካቡን ያዝ፡፡

ከአቡ ሐሚድ ኢብኑ አሕመድ አልበስሪ ተወራ አለም በአሕመድ ኢብኑ ሐንበል ዘንድ ነበረ፡፡ በሆነ መስአላ እየተዋወስን አንድ ሰው ለአሕመድ አለ፡- አንተ የዐብደላህ አባት ሆይ በዚህ ጉዳይ ላይ ትክክለኛ የሆነ ሐዲሥ የለም? አለም በዚህ ጉዳይ ትክክለኛ ሐዲሥ እንኳ ባይኖር ይህንን ሐዲሥ ሻፊዒ የሚለው የሱ ማስረጃ ደግሞ በሱ ይበልጥ የተረጋገጠ ማስረጃ ነው የሚሆነው፡፡ ከዚያም አለ አሕመድ ለሻፊዒ አልኩኝ በእንዲህ እንዲህ መስአላ ምን ትላለህ? መልስ ሰጠበት፡፡ አልኩም ከየት ነው ይህን ያልከው? ስለሱ ሐዲሥ ወይስ ቁርአን አለ እንዴታ አለ እንጅ በዚያ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሥ አነሳ፡፡ እሱ ደግሞ ነስ ቃል በቃል የሆነ ሐዲሥ ነው፡፡

አሕመድ አላህ ይማራቸውና ይሉ ነበር፡- ስለሷ ሐዲሥ የማላውቀውን መስአላ የተጠየቁ ጊዜ እል ነበር ሻፊዒ እንዲህ ይላል፡- እሱ መሪ አዋቂ ከቁረይሽ ስለሆነ፡፡

ከዳዉድ ኢብኑ አል-ኢስብሃኒ ተወራ አለ ኢስሓቅ ኢብን ረሀወይህን ሲል ሰማሁት፡- አሕመድ ኢብኑ ሐንበል በመካ አገኘኝና አለ ና ዓይኖችህ የሱን አምሳያ አይተው የማያውቁትን ሰው ላሳይህ ሻፊዒን አሳየኝ፡፡ የአሕመድ ኢብን ሐንበል ለሻፊዒ የነበራቸው አስተየያት ተማሪው በአስተማሪው የተደነቀ መሆኑ አይገርምም፡፡ በደረጃ ለሱ ያመኑ መሆኑም ነበረ፡፡ ግን ሻፊዒን እራሱን አሕመድ የሱ ተማሪ መሆኑ በደረጃና በሐዲሥ ዕውቀት ለሱ ከማመን አልከለከለውም፡፡ ይለውም ነበር አንቱማ በሐዲሥና በዘጋቢዎቹ ከኔ ይበልጥ አዋቂ ናችሁ፡፡ ሐዲሡ ሰሒሕ ከሆነ አሳውቁኝ፡፡ የኩፋ ወይም የበስራ ወይም የሻም ቢሆንም ትክክለኛ ከሆነ እሄድበታለሁና፡፡

ሻፊዒ ከአሕመድ ሲያወሩ በስም አይጠሯትም ነበር፡፡ (እሳቸውን ለማክበር ሲሉ) ይሉ ነበር ከባልደረቦቻችን ታማኙ አወራን፡፡ ሐደሠና ሲቀቱ ማን አስሓቢና አው አንበአና አው ሲቀቱ አው አኽበረና»

ከዚህ በኋላ እነዚህ ፈጣን ምልክታዎች ናቸው ቀደምቶቻችን ከነበሩበት በርካታ ሥርዓት ከፊሉን የምትገልጽልን ከከፍተኛ ሥነ-ምግባር ልዩነት ከማይነካው ከፍተኛ ሥርዓት የኢጅቲሃድ መለያየት ተጽዕኖ የማያደርግበት እነዚህ ከሙሐመድ ት/ቤት የተመረቁ ሰዎች ሥርዓቶች ናቸው፡፡ ዝንባሌ በነሱ ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም፡፡ የሕይወት ታሪኮችና የትውልዶች መናቂቦች የታሪክ መጽሐፎች በቁጥር የማያልቁ የተከበሩ አቋሞችን ሰብስበዋል፡፡

ከታላላቅ ዑለማኦች የተለያዩ ክርክሮችንም ያቺ ሥርዓት ድሯ ኢስላማዊ ከፍ ያለው ሥነ-ምግባር ማኅ ደግሞ የሆነች ለኛ እኛ በሁሉ ነገራችን በብትንትን ውስጥ እየኖርን መመለስ ይገባናል፡፡ ወደተባረከችው ዛፍ ጥላ ሥር በነዚያ በተከበሩት ሥርዓቶች ላይ እንገኝ፡፡ እነዚያ ጥሩ ቀደምቶቻችን የተውልንን የተከበረችዋን ኢስላማዊ ሕይወት ለመጀመር በመንቀሳቀስ ላይ እውነተኞች ከሆንን

እኛ እነዚህ ሥርዓቶች ያልተከበሩባቸው አቋሞች መኖራቸውን አንክድም፡፡ ወይም ከነዚያ ካወሳናቸው ከተሻሉ ባህሪያቶች ያገለሉ መኖራቸውንም ነገር ግን እሷ ከነዚያ በጭፍን ተከታዮች ወይንም የኋላዎቹ እነዚያ የወገንተኝነት ሩሕ የጠጡና በጭፍን መከተል ላይ የዘወተሩ በፉቀሃኦቹ ልዩነት ምክንያቶች በስተ ጀርባ የተደበቀውን ከፍ ያለ ዕውቀታዊ ሩሕ እውነታን ያልተረዱ እነዚያን ከፍ ያሉ ሥርዓቶች እውነታን በመፈለግ እውነተኛ አስተሳሰብ የመነጨች የሆነችን በልቦቻቸው ያልተጣለላቸው ጥበበኛው ሻሪዕ ያለመበትን ዓላማ ማግኘትንም ያልታደሉ ሰዎች አቋሞች ነበሩ፡፡

እሱ ከነዚያ ኢማሙል ገዛሉ ስለነሱ ያሉት ሳይሆኑ አይቀርም፡- «ፉቀሃኦች ተፈላጊዎች ከሆኑ በኋላ ፈላጊዎች ሆኑ፡፡ ከባለሥልጣኖች በመዞር የተከበሩ ከሆኑ በኋላ ወደነሱ በመዞር ተዋራጆች ሆኑ» ተፈላጊ የራሱ ሊቅ ነው፡፡ መነሻው እውነት እንጅ አይሆንም፡፡ ፈላጊ ደግሞ እራሱን ሸጧል፡፡ ገዢውን እሚያስደስት ነገር እንጅ አያንጎራጉርም፡፡ ያንን ኢስላማዊውን ፊቅህ ያዳበረውን የዚህን ሃይማኖት ተጨባጭነት ያረጋገጠችውን የሰዎችን ጥቅሞች መጠባበቁንም ያረጋገጠችውን ጸጋ የነበረው ልዩነት አዞሩ ወደ አሳማሚ ቅጣት በሙስሊሞች ከልዩነት አደገኛ ምክንያቶች አንዱ ምክንያት ሆነ፡፡ ይልቁንስ ጥቅም በሌለው ነገር የኡምማውን አቅም ብዙውን ወደሚበታትኑ ጥላቻዎች ተቀየረ፡፡ በሷ መቸገር በማይባበት ነገር ተቸገረች፡፡

ባለፉት ገጾች ከፊል ጎኖችን የተመለከትነው ልዩነት ከሰዎች ከፍ ያሉ ሥርዓቶቻቸውን ጠቅሰን የነበረው እሱ ያ ጸሐፊዎች መጽሐፎቻቸውን ያስቀመጡበት ልዩነት ነው፡፡ «በፉቀሃኦች ልዩነት ምክንያቶች» ድሮም አሁንም ያ እነዚያን ምርጥ ክ/ዘመናት ተከትሎ የመጣው ልዩነትማ እሱ ሌላ ዓይነት ልዩነት ነው፡፡ ለሱ የተለዩ ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉት ሁላ፡፡

## ክፍል ስድስት

## ከምርጥ ክ/ዘመናት በኋላ ልዩነትና ሥርዓቶቹ

ከአራተኛው የሂጅራ ክ/ዘመን በኋላ ኢጅቲሃድ አበቃ፡፡ ፀሐዩም ገባች፡፡ በጭፍን መከተልም የተሰራጨ ሆነ፡፡ መጽሐፎችና መድብሎችም ተፈጠሩ፡፡ በሰዎች ንግግር መነጋገር ከሙጅተሂዶቹ በአንዱ መዝሀብ ፈትዋ ማድረግ ንግግሩን መያዝ ከሱ መዝገብ በሱ መዝሀብ ፊቅህን መማር ከዚህ ምንም ነገር አልነበረም፡፡ በአንደኛና በሁለተኛ ክ/ዘመን ሦስተኛው ክ/ዘመንማ መመራመር እሱ ነበር የተሰራጨው አልተወገደም፡፡ አንዳንድ ዑለማኦች ተጠግተዋል፡፡ ከዕውቀት ባለቤቶች በቀደሟቸው ሰዎች ሕጎችና መሠረቶች ላይ ወደሙተንተን ነገር ግን ጭፍን መከተል ሳይከተሏቸው ንግግሮቻቸውን በማረጋገጥ የአራተኛው መቶ ሰዎችማ በነሱ ውስጥ ዑለማኦችና ተራ ሰዎችም ነበሩ፡፡ ተራ ሰዎችማ ከዕውቀት ባለቤቶች ይማሩ ነበር፡፡

ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ልዩነት በሌለባቸው መስአላዎች ከአብዛኛዎቹ ሙጅተሂዶች የሚወራውን እንደ ንጽሕናና ስግደት፣ ጾም፣ ዘካትና መሰል ጥያቄዎችን በሷ በተወራላቸው መሠረት ይሠሩ ነበር፡፡ መጠየቅ የሚያስፈልጋቸው ረቂቅ ጉዳዮች ከተከሰቱባቸው ስለዚያ ጉዳይ የዕውቀት ባለቤቶችን ይጠይቁ ነበር፡፡ ያ ዓሊም የሚከተለውን መዝሀብ ታሳቢ ሳያደርጉ የተለዩት ሰዎችና ከነሱ የዕውቀት ሰዎችማ ሐዲሥን ይማሩ ነበር፡፡ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሦችና ከባልደረቦቻቸው አሳር ይማሩ ነበር፡፡ በጥያቄዋ አብረውት ሌላን ነገር የማይሹበትን ከታወቀ ሐዲሥ ወይም ከሰሓባዎቹና ከታቢዒዮቹ ብዙሃኖች ግልጽ የሆኑ አባባሎች፡፡ አንዳቸው በመስአላው ልቡ የሚረጋገበትን ካላገኘ አዘጋገቡ ስለተጋጨ አመዛኝነቱ ግልጽ

ስላልሆነ ይህንንም የመሰለ ከፉቀሃኦች ወደተቀደሙት ንግግር ይመለሳል፡፡ ሁለት አባባሎችነ ካገኘ ይበልጥ ታማኞቻቸውን ይይዛል ከመዲና ሰው ቢሆንም ወይም ከኩፋ ሰው፡፡

ከነሱ የተኸሪጅ ሰዎች በግልጽ ተነግሮ ያላገኙትን ነገር ያብራሩት ነበር፡፡ በመዝሀቡም ውስጥ ይመራመሩ ነበር፡፡ በዚያ በሚመራመሩበትም መዝሀብ ይጠሩ ነበር፡፡ ይባል ነበር፡- እገሌ ሻፊዒይ ነው፤ እገሌ ደግሞ ሐነፊያ ነው፡፡ እዛጋ መዝሀቡን ይዞ መጓዝ ሳይኖር ከዚያ በኋላ ሁኔታው እንደዛ እንደሆነው፡፡ ከነሱ የሐዲሥ ሰዎች ወደ መዝሀቦች ያስጠጓቸዋል፡፡ መስማማቱ ስለተሰራጨ ነሳኢ ወይም በይሀቂ ወይም ኸጣቢ ወደ ሻፊዒይ ይጠጉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ዳኝነት ተመራማሪ እንጅ አይሾምም ነበር፡፡ አንድ አዋቂ ፈቂህ አይባልም ነበር ተመራማሪ የሆነ እንደሁ ሲቀር

### ከአራተኛው ክ/ዘመን በኋላ የነበረው ሁኔታ

ከአራተኛው ክ/ዘመን በኋላማ ሁኔታው ተቀየረ፡፡ ሑጀተል ኢስላም አል-ገዛሊን (5.5 ሞተ) እንተዋቸው ያንን እንዲገልጹልን እሳቸውም ይላሉ፡- «ዕውቅ ኸሊፋነት ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ የተመሩት ቅኖቹ ኸሊፋአቶች ተሾሚት፡፡ ስለ አላሁ ተዓላ የሚያውቁ ምሁራን መሪዎች ነበሩ፡፡ ድንጋጌዎቹን አዋቂ በፈትዋዎች ይሠሩ ነበር፡፡ በፍርዶች አንዳንድ ጊዜና ከምክክር ቅሮ የሌላቸው ክስተቶች ላይ እንጅ ከፉቀሃኦች እርዳታን አይፈልጉም ነበር፡፡ ዑለማኦች ለኣኼራ ዕውቀቶች ራሳቸውን አገለሉ፡፡ ተጠናከሩበትም፡፡ ፈትዋዎችን ከዱንያ በሰዎች ሕጎች ጋር የሚያያዘውን አንዱ ወደሌላው ያሸጋግሩት ነበር፡፡ ወደ አላህ ዞሩ፡፡ በሁሉም ትግላቸው ከሕይወታቸው ታሪካቸው እንደተዘገበው ከነሱ በኋላ ኸሊፋነት የደረሰ ጊዜ (ከኹለፋኡ በኋላ) ወደተሾሚት ሰዎች ሳይገባቸውና በፈታዋ ዕውቀትም ራሳቸውን ሳይችሉ በድንጋጌዎችም ከፉቀሃኦች እርዳታን ለመፈለግ ተገደዱ፡፡ በሁሉም ሁኔታቸው ከነሱ ጋር በማድረግ በዕለት ከእለት እንቅስቃሴያቸው ሕግጋቶቻቸው ፈትዋ ለመጠየቅ ከታቢዒዮቹ ምሁራኖች እንደቀደምቶቹ የቀጠለ ነበረ፡፡ የጠራውን ሃይማኖት የያዘ በቀደምቶቹ ዑለማኦች ባህሪ ላይ የዘወተረ የተፈለጉ ጊዜ ይሸሹና ይዞሩ ነበር፡፡ ኸሊፋዎቹ ዳኝነትና ሥልጣኖችን ለመሾም እነሱን በመፈለግ ችክ ወደማለት ተገደው ነበር፡፡ የዚያን ዘመን ሰዎች የዑለማኦችን ክብር አይቷል፡፡ የመሪዎችንና የሹማምንቶችን ወደነሱ መዞርም እነሱ ከነሱ የዞሩ ከመሆኑ ጋር

ዕውቀትን ለማግኘት አንገቶቻቸውን ቀና ቀና አደረጉ፡፡ ክብርን ወደማግኘት ለመድረስና ከሹማምንቶቹ ዘንድ ልቅናን ለማግኘት ፈተናዎችን

በመማር ላይ ተደፉ፡፡ ነፍሶቻቸውን ለባለሥልጣኖቹ አቀረቡ፡፡ ተዋወቋቸው፡፡ ሹማምንቶችንና ከነሱ ጋር ግንኙነቶችን ፈለጉ፡፡ ከነሱ የተከለከለ አለ፡፡ ከነሱም የተሳካለት አለ፡፡ የተሳካለትም ከልመና መተናነስና ራስን ከማቅረብ ውርደት አልዳነም፡፡ ፉቀሃኦች ተፈላጊዎች ከሆኑ በኋላ ፈላጊዎች ሆኑ፡፡ ከባለሥልጣኖች በመዞር የተከበሩ ከሆኑ በኋላ ወደነሱ በመዞር የተዋረዱ ሆኑ፡፡ ከአላህ ሃይማኖት ዑለማኦች በማንኛውም ወቅት አላህ የገጠማቸው ሲቀሩ በነዚያ ጊዜያቶች በብዛት የተዞረው ወደፈተናዋና ዳኝነቶች ነበር፡፡ እነዚህ ነገሮች በሹመቶችና በመንግስት ሥልጣኖች አስፈላጊ ስለነበሩ፡፡

ከዚያም ከነሱ በኋላ ከባለሥልጣኖቹና ከአዛዦቹ የሰዎችን ንግግሮች በእምነቶችህ ሕጎችና በወሬ ክርክርን የሚሰሙ መጡ፡፡ ሰዎች በፍሎሶፊ ትምህርት ላይ ተደፉ፡፡ በሱም ውስጥ መጽሐፎችን መጻፍ አበዙ፡፡ በውስጥ የክርክሮችን መንገዶች አስተካከሉ፡፡ በንግግሮች ውስጥ የተቃራኒዎችን ጥበቦች አውጣጥተዋል፡ ፡ ዓላማቸውም ከአላህ ሃይማኖት የሚያጠፋውን መከልከል ነው ብለዋል፡፡ ከሱንናም መከላከልና የፈጠራን ሰዎች መከልከል

ከነሱ በፊት የነበሩት ፈታዋን መማራቸው ለዲንና የሙስሊሞቹን ሕጎች መሸከም ነው፡፡ ለአላህ ፍጡራኖች አዝነን እነሱንም ለመምከር ከዚያያ በኋላ በፊሎሶፊ ውስጥ መዘባረቅን ትክክል ነው ብሎየማያምን በሱ ውስጥ የክርክርን በር መከፈትንም የማያምን መጣ፡፡ የሱ በር በመከፈቱ አስቀያሚ ወገንተኝነቶች መከፈት ስለተወለደ ደምን ወደማፍሰስና ሀገርን ወደማጥፋት የሚያደርሱ የተሰራጩ ክርክሮች ነፍሱ በፊቅህ ወደመከራከርና በተለይ በሻፊዒና በአቡ ሐኒፋ መዝሀብ በላጩን ወደመግለጽ ያዘነበለች ሰዎች ፊሎሶፍንና የትምህርት ዓይነቶችን ተወውና በተለየ ሁኔታ በሻፊዒና በአቡ ሐኒፋ መካከል ወዳሉት የልዩነት ጥያቄዎች ላይ ጎረፉ፡፡

በማሊክና በሱፍያን በአሕመድ በሌሎችም መካከል የነበረውን ልዩነት ችላ አሉት፡፡ ዓላማቸው የሸሪዓውን ረቂቅ ነገሮች ማውጣጣት ነው አሉ፡፡ የመዝሀቡን ጥበበችም መሳል ነው የፈትዋ መሠረቶችንም መደልደል ነው በውስጧ መጽሐፎችን ማዘጋጀትን አበዙ፡፡ ማውጣጣቶችንም በሷ ውስጥ የክርክሮችንና የመጽሐፍ ዝግጅቶችን ዓይነቶች አረጋግጠዋል፡፡ እነሱ እስካሁን ድረስ በሱ ላይ ቀጥለዋል፡፡ ከጊዜያቶች ከኛ በኋላ አላህ ምን እንደሚያስገኝ አናውቅም፡፡ ይህ ነው በሌላ ሳይሆን በልዩነቶችና በክርክሮች ላይ ለመደፋት ቀስቃሽ የሆነው፡፡

የዱንያ ሰዎች ነፍሶች ከመሪዎች ከሌላ መሪ ጋር ወደመለያየትና ከዕውቀቶች ወደሌላ ዕውቀት ብትዘነበል አሁንም አብሯቸዋ ይዘነበሉ ነበር፡፡

የለፉበትም እሱ የሃይማኖት ዕውቀት ነው፡፡ እነሱም ወደ ዓለማት ጌታ መቃረብ እንጅ ሌላ ፍላጎት እንደሌላቸው ከመናገር ወደኋላ አይሉም፡፡

በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች ከመከታተል ቀጣዩን እናገኛለን፡፡

1/ ኢማሙል ገዛሊ አላህ ይማራቸውና በነዚያ ቃላቶች ውስጥ እጃቸውን በዚያ ኡምማው ላይ በደረሰው እውነተኛው በሽታ ላይ አስቀምጠዋል፡፡ ከቅኖቹ መሪዎች በኋላ በሁለቱ የዕውቀቱ ዓለም መሪዎችና በፖለቲካ መሪዎች መካከል በተከሰተው የደፈረሰ መቆራረጥ ውጤት ሳቢያ የመጣ ታሪካችንን በዚያች ከሷ በመቸገር ባልተወገድነው ምልክት ጠባሳ መለዮ ያደረገ ኢስላማዊ ያልሆኑ ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች ተገኝቷል፡፡ መነሻዋም ፖለቲከኞች ኢስላማዊ ሸሪዓዊ ፖለቲካን አለማወቅ የሆነ እኛ ጋ ጥናታዊ ግምታዊ የሰዎችን ጉዳዮች የማይዳስስና የዕለት ከዕለት ችግራቸውን በዚያ ተግባራዊ በሆነ መንገድ እነዚያ ጉዳዮች በሰሓቦችና በታቢኦች ጊዜ ይታከሙበት በነበረው የማይንከባከብ ፊቅህ አለን፡፡

አብዛኛዎቹ የፊቅህ ጉዳዮች አብዘኞቹ የኡሱል ጥያቄዎች ግምታዊ ጉዳዮች እንጅ አይደሉም፡፡ ውይይቶችና ክርክሮች የልዩነት ጉዳዮች የወለዷቸው

2/ ከነዚያ ከተሳሳቱ ድርጊቶች በኋላ ፊቅህ መለወጡ ነው፡፡ የሰዎቹን ሕይወትና ክስተቶቹን በሸሪዓ ሕጎች ከማስተካከያ ስልት ተፈላጊ የሆነውን ተጨባጭ በጎ ወደማድረጊያ ስልት ያ ተጨባጭ ምንም እንኳ ቢሆን ያ ደግሞ ሙስሊሞች ዘንድ የድንጋጌን ሕይወት በአንድ የሆነን አለመረጋጋት ዓይነት አውርሶታል፡፡

ብዙውን ጊዜአንድን ጉዳይ ከአንዱ ሰው በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ እዚኛው ፊቅህ ዘንድ (ሐላል) የተፈቀደ እዚያ አጠገብ ደግሞ የተከለከለ ያረገ ጉዳይ ነው፡፡ እሱ ከፊቅህ መሠረቶች አንዱ መሠረት መሆኑ ብቻ ይበቃል፡፡ በፊቅህ ርዕሶች ስፊር እስም (አልመኻሪጁ ወልሒየል) በመባል ታውቋል፡፡ ማውጫዎችና ዘዴዎቻቸው ማለት ነው፡፡ ይህን ርዕስ እንከን የለሽ የሆነ ዕውቀት ማወቅና በሱ ውስጥ ብቃት ያለው መሆን የፊቅሁ ዕውቀት ለመስፋቱና ለጮሌነቱ ከሱ ውጭ ካለ ሰው ለመብለጡ ማስረጃ ሆነ ነበረ፡፡ ጊዜ በሄደ ቁጥር የዲን ሥልጣን በባለቤቶቹ ላይ በደከመ ቁጥር ይህ ነገር ይባባሳል፡፡ ሰዎችም በሸሪዓ ጉዳይ ይሞላላቃሉ፡፡ ጉዳዩ እስከደረሰ ድረስ ከፊል በፈትዋ ላይ ያሉ ሰዎች ዘንድ እነሱ ምንም ማስረጃ በሌለ ፈትዋ ማድረግ መጀመር ትክክለኛነቱን የሚያምኑበት የሆነን በዚህ ነገር በሰዎች ላይ ማቅለል ወይም ማክበድ አለበት ብለው ያ ደግሞ ድንበሮችን ላለማለፍ ዋስትና ይሆናል፡፡ ከፊላቸው ለከፊሉ አስተዳደሮች ሕጋዊ ማድረግን ይመስል

በአጠቃላይ ፍጡራኖች ሕጋዊ የማያደርገውን ነገር አንዳቸው ሴትን ከመንካትና እፍረተ ገላን ከመንካት ዉዱእ ይፈርሳል ተብሎ ይጠየቃል ይላል በሱ አቡ ሐኒፋ ዘንድ ዉዱእ አይፈርስም፡፡ ከቼዝ ጨዋታና የፈረስን ሥጋ ከመብላት ሲጠየቅ ደግሞ ይላል ሻፊዒይ ዘንድ የተፈቀደ ነው፡፡ ተጠርጣሪን ከማሰቃየት ወይም ከሐራም በታች ባሉ ቅጣቶች ድንበሩን ማለፍ ሲጠየቅ ይላል ይህን ማሊክ ፈቅደዋል፡፡

ለአንድ ሰው ወቅፍን በስጦታ የሰጠውን ንብረት በመሸጥ ለመዘየድ የሻ ጊዜ የተበላሸና ጥቅሙ የጠፋ ጊዜ ለተቆጣጣሪው የሚያስተካክልበት የሌለው ጊዜ ይህ በመፈቀዱ ፈትዋ ያደርግለታል፡፡ በአሕመድ መዝሀብ የሙስሊሞች የወቅፍ ንብረቶች እስከሆኑ ድረስ ከወቅፍነት በየዓመታቱ ቡድኖች ሁሉ ወደ ግልጽ ንብረቶች የሚዞሩ እንደዚሁ የሸሪዓው ግቦች የአላህ ፍራቻ በመጥፋቱ ጠፋ፡፡ አጠቃላይ የሆኑ ሕጎቹ ችላ ተባሉ፡፡ ነገሩ የገጣሚዎችን ቂሎችና ጠማማዎች እፍረተ ቢሶችን በአላህ ሕጎች እስከመቀለድ ድረስ አቡ ኑዋስ ማለቱን ይመስል፡፡

ዒራቃዊው ጭማቂንና መጠጣቱን ፈቀደ፡፡ (ነቢዝ) አለም አስካሪ መጠጥና መስከር ነው ክልክሉ፡፡ ሒጃዛዊው ደግሞ ሁለቱም መጠጦች አንድ ናቸው አለ፡፡ ለኛ ደግሞ በሁለቱ ንግግሮቻቸው መካከል ኸምር ተፈቀደችልን፡፡

ከሁለቱ ንግግሮቻቸው ጫፎቻቸውን እይዛለሁ እጠጣታለሁ ወንጀለኛውን ከወንጀሉ ለማላቀቅ፡፡ በእርግጥም እነዚያ የሃይማኖትን ጥብቅ የሚጠብቁት ሰዎች ተዋረዱ፡፡ በሰዎችም ላይ ሃይማኖታቸው ተዋረደ፡፡ ድንበሮችን ማለፍ ሰዎችን በማግራት ስም የሚዞሩበት እስከሆነ ድረስ - ያም የከፊል ሙፍቲዎች አካሄድ ሆነ፡፡ ከነዚያ የግርማ ሞገሱን ግድግዳ ካፈረሱት ለነፍሶች ዝንባሌዎች በሚስማማ መልኩ ፈትዋ ማድረግን የፈቀዱ -

የደረቀና የጠነከረ ቡድን ደግሞ የነሱ ተቃራኒ ሆኗል፡፡ ለሚጠይቀው ሰው ለመመለስ ጠንካራ የሆነውን ንግግር ለመፈለግ ሞከረ፡፡ እሱ በዚህ እስልምናን ያገለገለ መስሎት - ሰዎችን ቁርጥ ውሳኔውን ወደመያዝ ሊመልስ ነገር ግን ጉዳዩ እንዲህ አይደለም፡፡ ውጤቱ ምንጊዜም እንደጠበቁት አልሆነም፡፡ በብዛት ተቃራኒው ነው የሚከሰተው፡፡ ተራው ሕዝብ ከሸሪዓው ይሸሻል፡፤ ለሱ መሳቡን እምቢ ይላል፡፡ በማግራት ፋንታ በሱ መጥናትን ታያለህ፡፡

እንደ ስፔኑ ንጉሥ ታሪክ ያ የማሊኪያውን ሙፍቲ የሕያ ኢብኑ የሕያን የጠየቀው በጾም ቀን ግንኙነት ለመፈጸሙ ሁለት ተከታታይ ወሮችን መጾም አለበት፡፡ ከነሱ ውጭ አያብቃቃውም በማለት መለሰለት፡፡ በመጀመሪያ ባሪያን ነፃ በማድረግ ፈትዋ ማድረግ ነበረበት፡፡ ከዚያ ጉዳይ የተጠየቀ ጊዜ አለ፡- እሱ በሙቶ

የሚቆጠሩ ጫንቃዎችን ነፃ ማድረግ ይችላል፡፡ አስቸጋሪውን መፈጸም አለበት፡፡ እሱም ጾም ነው፡፡

ወደ እስልምና ተጨባጫዊነትና ገርነቱ የሰዎችን ለሕግጋቱ ታዛዥነት ግላዊ ተፈጥሯዊ በነፃ ተነሳሽነት ያለድካምና ያለችግር ተገዥነት ላይ ማድረግን መዳዳቱን ከመሆኑም ጋር ሰዎችን ነፃዎችና የዝንባሌን ፈረሶች እንዲሳፈሩ አይተዋቸውም፡፡ ያንን ብንሠራ ሁለቱም ቡድኖች ስህተት ላይ መሆናቸው ግልጽ ይሆንልናል፡፡ ከነሱ ሁሉም ጥበበኛው የሆነ ሕግ ደንጋጊ ያሰበውን አልፏል፡፡

የምሁሩ (የዓሊሙ) ግዴታ ለሰዎች የአላህን መልዕክት አላህ (ሱ.ወ) በመጽሐፎቹ እንዳወረደው መልዕክተኞችን እንደላከው ማድረስ ነው፡፡ የማክባድና የማቅለል ሥልጣን የለውም፡፡

«አላህን በሃይማኖታችሁ ታስታውቁታላችሁ በላቸው፡፡» (አል-ሑጁራት 49፡16)

«... እናንተ ታውቃላችሁን ወይስ አላህ› በላቸው፡፡» (አል-በቀራህ 2፡140)

የሚታየው መከተሉ ነው፡፡ ያንን ያለፈ በማክባዱም ጎን ሆነ በማቅለሉ ፈጠራ ነው፡፡

ተቅሊድ (በጭፍኑ መከተልና) እና ውጤቶቹ

ባለፈው የኢጅቲሃድ ወደደረሰበት እንዴት እንደደረሰ አይተናል፡፡ በእርግጥም ብዙ ጥሩ ሰዎች ለሱ ብቃት የሌለው በሩ ከመግባት ፈርተዋል፡፡ በእውነቱ ለፈትዋ በባለሥልጣን የተዘጋጁ ሰዎች ተጋፍጠዋል፡፡ የቁርአንና የሐዲሥ ማስረጃዎችን የዝንባሌን ፈረሶች ወደአዘመሙበት አንገቶቻቸውን የሚጠመዝዙ ሆነዋል፡፡ ዑለማኦቹም ደግሞ በአግሪና አጠንካሪ መካከል ተለያይተዋል፡፡ የኡምማው ደጋጎች ደግሞ ለመጨረሻውና ለዲኑ መጨረሻ ሰግተዋል፡፡ ሕክምናውም መፈለግ ጀምረዋል፡፡ የማምለጫ መስኮት አላገኙም፡፡ ኡማምውን በጭፍን እንዲከተል ማስገደድ ካልሆነ በስተቀር፡፡ ምን ዓይነት ከባድ ችግር ነው! ከሱ መውጫ ደግሞ በጭፍን መከተልን ማግኘት ነው (ተቅሊድ)

የፉቀሃኦቹ መወዳደርና በመካከላቸው መጨቃጨቃቸው ተቃራኒነታቸው ተቃዋሚነታቸው መቀጠሉ ብቸኛውን ክርክር መውጫ መንገድ ልዩነት ባሏቸው መስአላዎች ውስጥ ወደ ቀደምቶቹ ዑለማኦች አባባሎች መመለስ - ሰዎችም ከብዙ ዳኞች ላይ እምነታቸውን እንዳጡ ሁሉ - ወደ ባለሥልጣኖች ስለቀረቡና ወደዱንያ ስለዞሩ በብዙ ጉዳዮቹም ላይ ስለበደሉ - በዳኛው ፍርድ የማያምኑት ሆኑ፡፡ ፍርዱ ከአራቱ መሪዎች ከአንዱ ንግግር ጋር የተስማማ ጊዜ እንጅ፡፡ እንደዚሁ ብዙኃኑ ሙስሊሞች አራቱም መሪዎች በጭፍን መከተልና ንግግሮቻቸውንም መያዝ

በተናገሩበት ሁሉ ባልተናሩት ደግሞ ከተናገሩት ማውጣጣት ጠባቂ ዋስትና ተደርጓል፡፡ ካፈነገጡ ምርምሮች ዓላማዎቹን ለማሳካትና ፍላጎቶችን ለማረጋገጥ የሸሪዓው ዕውቀቶችን ከተማሩ አላህን ከማይፈሩ ሊገኙ ከሚችሉት ኢጅቲሃዶች

ኢማሙል ሐረሜይን (470 ዓ.ሂ ሞቱ) ሞግተዋል፡፡ የተመራማሪዎቹ ሙሉ ስምምነት መገኘቱን፡፡ ሰሓባዎችን በተናጠል ጭፍን መከተል በመከልከል ላይ ይልቁንስ የመሪዎችን መዝሀቦች መከተል አለባቸው፡፡ እነዚያ ልምዱ ያላቸው የተመለከቱ ርዕሶችን ያዘጋጁ የጥያቄዎቹን ሁኔታ ያወሱ የቀደምቶችንም መዝሀቦች ያዩ የሆኑትን ሰዎች

ከዚያም ያንን አጠናከሩና ወደዚያ ባዕድ ወደሆነው ድምዳሜው ደረሰ፡፡ እሱም ተራ ሰው ልምድ ያላቸውን ሰዎች መዝሀቦች መከተል አለበት የሚለው ነው፡፡ በዚህ በኢማሙል ሐረሜይን ንግግር ላይ የተመራማሪዎችን ሙሉ ስምምነት በመሞገቱ ላይ ኢብኑ ሰላህ (643 ዓ.ሂ) ገንብቷል፡፡ አራቱም መሪዎች በጭፍኑ መከተል ግዴታ መሆኑን መሞገቱን መዝሀቦቻቸው ሥርዓት ስላላቸውና ስለተመዘገቡ መስፈርቶቻቸውም ስለተጣሩ ይህን ይመስላል፡፡ ከነሱ ውጭ ላሉ መዝሀቦች ያልተገኘውን ከሰሓባና ከታቢዒ ከዚያ በኋላ ከሱ የኋሊኞቹ ተቀባበሉት፡፡ ከዚሁ ነው ሰዎች የተከበረውን ቁርኣንና ትምህርቶቹን ችላ ማለት የጀመሩት፡፡

ከሐዲሥና ከዓይነቶቹም ከዕውቀት አባባሎችና መዝሀቦችን በመቀባበል ሕጎችን ማውጣትና መሠረቶችን ከሷም በመከራከር በመዘርዘር ... የንግግራቸውን ተመሳሳይ በማስገባት ተብቃቁ፡፡ ይኃውም በጥሩ ሁኔታው ነው፡፡ ማስቆልቆሉ ቀጠለ፡፡ ልዩነቱም በረታ፡፡ ጥልቀትም ኖረው፡፡ ከዛ በኋላ ብዙ ትውልዶች ጥርት ባለ ጭፍን መከተል ላይ አደጉ፡፡ የትምህርቱ ዓለም እንቅስቃሴውን አቆመ፡፡ የምርምሩ ዛፍም ደረቀ፡፡ ፈተናዎች ተሰራጩ፡፡ ድንቁርናም አዳረሰ፡፡ በሰዎች ዕይታ ፈቂህ ምሁር ማለት እሱ ያ ከፉቀሃኦች ንግግሮች የተወሰኑት የሸመደደ፣ ከአስተያየቶች ብዙዎችን የሰነቀ ሆነ፡፡

በጠንካራዋና በደካማ መካከል ያለመለየት ሙሐዲስ ደግሞ ከሐዲሦች የተወሰኑትን የሸመደደ ሆነ ትክክለኛ ቢሆንም ባይሆንም -

ጉዳዩ ምነው እዚሁ ድረስ ቢቆም ኖሮ ሁኔታው ከዚህ ከወረደ አዘቅጥ ወረደ፡፡ ከሱ ይበልጥ የወረደ ወደሆነ ነገር ልክ የዕውቀቶች ፀሐይ ከሙስሊሞች ዱንያ የጠለቀች ትመስላለች፡፡ አስተሳሰብ መከነ፡፡ የፈጠራዎች ገበያ በሕዝብ ዘንድ ተሰራጨ፡፡ የማፈንገጥ ሸቀጣ ሸቀጥም አተረፈ፡፡ ተረቶች ተሰራጩና የተለያዩ

ቅርጾችን ያዙ፡፡ ይህ ነገር ከመሪዎች ፊት ለፊት መንገዱን አሰፋ፡፡ ኢስላማዊውን ሥልጣኔ እንዲጠርጉና የኢስልምናን ሀገሮች የተፈቀደ እንዲያደርጉ፡፡

### የኡምማው ሁኔታ በመጨረሻዎቹ ጊዜያቶች

ያ በጭፍን መከተል ጭኖች ውስጥ ያንቀላፋችው በተከበሩት ሀላፊ ምኞቶች ውስጥ የተኛችው ኡምማ ሁኔታ ነበር፡፡ አበሳጭ የሆነው ቁርርጥ በባለሥልጣኖችና በዚህ ኡምማ የሕግ ምንጮች መካከል ከተከሰተ ጀምሮ ሰዎች የዋለሉ ዝንባሌዎች የሚወረውሯቸው ሆነዋል፡፡ የኡምማው ምሁራኖች ደግሞ ከነሱ ዘንግተዋል፡፡ ሁሉም በሚያዘነጋው ነገር ጥሩ ነው በሚያየው የኡማምውን የማይሰሙ እንኳ ይህ ደረቅ ወደ ድንጋይነት የተቀየረ ተከታይ ከዚያ ሕያውና አብሪ ከሆን ቅድመ አያ ተገኘ ማለትን ሊያምን አይቀርብም፡፡ የአሁኑ የአውሮፓ ዕድገት ሲገኝ ጊዜ ኡምማው በዚያ ሁኔታ ላይ ሆኖ

አውሮፓዉያኖቹ ፊት ለፊታቸው ከእውነተኛ አካሏ የሚረባ ነገር ያልቀረውን ኡምማ አገኙ፡፡ እምነት ጠፍቷል፡፡ የብዙዎቹ እምነት ደግሞ የተርበተበተ ነው፡፡ እርግጡ እርግጥ አልሆነም፡፡ ሥነ-ምግባር አፈንግጧል፡፡ ቀጥተኝነት የለም፡፡ አስተሳሰብ ደርቋል፡፡ ምርምር አቅሟል፡፡ ፊቅህ ፍቷል፡፡ ፈጠራዎች ቆመዋል፡፡ ሱንና ተኝታለች፡፡ ንቃት ርቋል፡፡ ልክ ኡምማው እሷ እንዳልሆነች ይመስላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እነዚያን ኡምማውን የሚጠባበቁትን ሰዎች ቀስቅሰዋል፡፡

ምዕራባዉያን ይህንን ዕድል ተጠቀሙና ሀገሮችን ወረሩ፡፡ የሰዎችን ጫንቃዎች ተቆጣጠሩ፡፡ ከኡምማው አካል ሕልውና የቀረውን ቀሪ ጨረሱ፡፡ ሁኔታው ዛሬ እኛ ውስጡ ያለንበተ እስከደረሰ ድረስ ከውርደትና ከማነስ - የነገሮቻችን ቁልፎች በጠላቶቻችን እጆች ሆኑ፡፡ በዕጣ ፋንታዎቻችን ይወስናሉ፡፡ እነሱ ጋ ለችግሮቻችን መፍትሔ እንፈልጋለን፡፡ በነፍሶቻችን ያስገኘናቸው በእጆቻችን የቀረጽናቸው ሆነን ሳለን፡፡

በዚያ መካከል ኡምማው ከሕይወት ቅሪት በቀረለት ከእንቅፋቱ ለመነሳት ከጥፋቱ ለመታርም ሞክሯል፡፡ ሁሉም ሙከራዎቹ መጠነ ሰፊ የሆነ ውድቀት አጋጠመችው፡፡ ኡምማው ወደስኬት የሚያደርሱትን መንገዶች ተሳስቷልና፡፡ የአላህን ልማድ ተቃራኒ ሆኗልና፡፡ እነዚያ ሙከራዎች ባዕድን በጭፍን ከመከተል መነሻ ነውና የቆመችው፡፡ ወራሪንም መከተል - ሁኔታዎቹ ክፋትን እስከጨመሩ ድረስ፡፡

አዲሱ ትውልድ ከኡምማው ጥሩውን መፍትሔ በጉጉት ይጠባበቃል፡፡ አዳኙን መድኃኒት ይፈልጋል፡፡ ከኡመቱ ልጆች ቀላል የማይባሉ ጭፍሮች ማወቅ

ጀመሩ «የዚህ ኡምማ መጨረሻ መጀመሪያው በተስተካከለበት ነገር እንጅ አይስተካከልም፡፡»

ወደ እስልምና ዞሩ፡፡ ከጣፋጭ ምንጩ ሊጠጡ፡፡ አስ-ሰሕዋል ኢስላሚያ ኢስላማዊ ንቃት ተብሎ የተሰየመው ብቅ አለ፡፡ የእስልምና ጠላቶች ከሃይማኖቶቻቸው ልዩነት ጋር መስኩን በዚች በተባረከች ደዕዋ መልቀቅ አልሆነላቸውም፡፡ እኛን ለመዋጋት የሚጠቀሟቸውን መሣሪያዎች ምን እንዲህ አበዛቸው፡፡

ከፊል የኛው ልጆች እነዚያ በመካከላችን የሚኖሩት ከነዚያ ከመሣሪያዎቹ ናቸው፡፡ ከፊሎቹ ምንም አይመስላቸውም፡፡ በኡምማው ጠላቶች እጆች የማፍረሻ መዶሻ መሆኑ ያም በብዙ ባመኑት ሕዝቦች ላይ ተንኮልን የሚሞክሩ ቡድኖች በእርግጥ ገሃድ ወጥተዋል፡፡ ጠላትና ኢስላማዊ ሕይወትን ለመጀመር መንገዱን በማዘጋጀት መካከል የምትጋርድ የተለያዩ መሣሪያዎችን ተጠቅማ በዚህ ንቃት ፊት ለፊት አደገኛ ተቃውሞችን አቁማ - ወዲያው ይህች የተባረከች ንቃት አስቀያሚውን ችግር ትገጥመዋለች፡፡ «ልዩነትን ከሚያጋጥሟት ታላላቅ ችግሮች ጋር ሌሎቹ ችግሮች እውነተኛ ሠሪዎችን ሀይል ለመጨረስ በቂ ነበሩ» «ልዩነት» ተጨምሮ ይቅርና፡፡ ወዲያውኑ ብዙ ሀይሎች በዚህ በተጠላ ቋጥኝ ላይ ተፈረፈሩ፡ ፡ ወደ ቀደምቶቹ እራሳቸውን የሚያስጠጉ ወጣቶችን ማየት ጀመርን፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ወደ ሐዲሥ ሰዎች ወደ መዝሀብ ተከታይነት ራሳቸውን የሚያስጠጉም - ሌሎች ደግሞ መዝሀብ አልባነትን የሚሞግቱ በነዚህና በነዚህ መካከል ውንጀላዎችን አለ፡፡ ከሀዲ ነው አማጺ ነው በማለትና ወደ ፊጠራ ማፈንገጥ በጠላት ሠሪ ስለላና ይህን ወደመሰሉ ነገሮች ማስጠጋት፡፡ በአንድ ሙስሊም ወንድሙን ወደሱ ማስጠጋት በምንም ተአምር የማይገባን ነገር ለሰዎች ማስተዋወቁ ይቅርና ባገኛቸው መንገዶች ሁሉ እስልምና ላይ እየደረሰ ያለው ከመንቀል ሙከራዎች በኡምማው ዘንድ ከነዚያ ልዩነቶች ይበልጥ አደገኛው መሆኑን ዘንግተው ወይም የዘነጉ መስለው ለተመራማሪ መሪዎች (አኢማ) የመለያየታቸውን ምክንያታዊነት የሚገልጹ የልዩነት ምክንያቶች የኖሩ ጊዜ ከሷም የምታቃልል በልዩነት ሕጎች ክበብ ውስጥ ለመኖር የምትረዳ የኖራቸው ጊዜ በጊዜያችን ካሉ ተለያይዎች ከልዩነት ምክንያቶች አንድም ሎጂካዊ ምክንያት የላቸውም፡፡ እነሱ ተመራማሪዎች አይደሉም፡፡ ሁላቸውም በጭፍን ተከታዮች ናቸው፡፡ እነዚያ ጭፍን ተከታይነት ጣሉ በማለትና ከነፍሶቻቸውም በመገፍተር ድምጾቻቸውን ከፍ የሚያደርጉት እንኳ ሳይቀሩ እነሱ ድንጋጌዎች ቀጥታ ከቁርአንና ከሐዲሥ ያለ ጭፍን መከተል እንይዛለን ይላሉ፡፡

በእውነት እነሱ በከፊል የሐዲሥ መጽሐፎች ላይ ይኮላተፋሉ፡፡ ጸሐፊዎቻቸውን ስለሐዲሡ በሚሉት ሁሉ በጭፍን ይከተሏቸዋል፡፡ ሐዲሡ በደረጃውም ሆነ በዘጋቢዎቹ - ከነዚያ መጽሐፎች በሚያውጠነጥኑትም ነገር ሁሉ ወይም ከፉቀሃኦች በሚዘግቡት ሁሉ ይከተሏቸዋል፡፡ ከነሱ ብዙዎቹ ዘጋቢዎችን ማወቅና የጀርሕ ወተዕዲል ደረጃዎችን የዘጋቢዎችን ታሪክም ዕውቀት አውቃለሁ ባይ ነው፡፡ እሱ በዚህ ሁላ በዚህ ርዕስ ወይም በዚያ ከሰዎቹ መጽሐፎች አንድን መጽሐፍ ያጠና ከመሆን የማያልፍ ሆኖ ሳለ ለነፍሱ በምርምር መድረክ ላይ መውጣትን የፈቀደላት በሰዎችም ላይ ከፍ የማለትን መብት ያገኘው፡፡

ከዕውቀት ዕጣ ፋንታ ያገኘ ሰው ዕውቀቱ ከመሀይማኖቹ እንዳይሆን ሊከለክለው ይገባል፡፡ ማዕረጎችን ከማሰራጭትና ሰዎችን ከመወንጀልም ከፍ ሊል ይገባል፡፡ የኡምማው እምነት የሚያጋጥመውን ችግር አውቆ ከሱ የመከላከልን ሥራ መሥራት አለበት፡፡ ልቦችን በማስተካከል ላይ ሊያተኩር ይገባል፡፡ ሁላቸውም ጭፍን መከተል ማድረጋቸው ካልቀረ ከመሪዎቻቸው አባባሎቻቸውን ከማለያየታቸው ጋር መያዛቸው ካልቀረ ከዚህ ውጭ ቢናገሩ እንኳ የልዩነትን ሥርዓቶች እነዚያ ከሰለፎች የተከበሩ መሪዎች በክንፎቻቸው ሥር የኖሩት ሥርዓቶች ያነሰ የለም እነሱን እንኳ ይያዙ፡፡

ቅን አማኞች በእርግጥ ተስፋ ያደርጉ ነበር ይህች የተባረከች ንቃት መነሳቷን የከሀዲዎችና የእምነት የለሽ አስተሳሰቦች ያስገኙትን ለመጠገን ትነሳለች ብለው፡፡ ሐሰተኛ ያፈነገጡ እምነቶችም በጣም ጥልቅ ከሆነ ገደል በዚህ ሰይጣናት ከልጆቻቸው ከብዙዎችን አዕምሮዎችና ልቦናዎችን የማረከ ኡምማ ሕልውና ውስ ልቦቻቸውን ከዚያ ከዝገት ሊያጸዱ በቦታው ትክክለኛው ኢስላማዊ እምነት እንዲሰፍር ከዚያም በዚህ ሰፊ በሆነ ዓለም የአላህን መልዕክት ይዛ እንድትጓዝ የአላህ ቃል በምድር ላይ ከላይ እንድትሆን

ነገር ግን ነፍስን የሚጎዳው ከፊል የሙስሊም ልጆች የንቃቲቱን ክንፎች በማንኮታኮትና ሕግ በሌለው ልዩነት ማሰሪያዎች በሚገባውም በማይገባውም መጠፈራቸው ነው፡፡ ሙስሊሞቹን በራሳቸው ቢዚ አደረገ፡፡ ብዙ ሀይሎቻቸውን አባከነ፡፡ ፊት ለፊታቸው ብዙ ነገሮችን አስገራሚ መዘባረቆችን ዘባረቀ፡፡ በጥቃቅን እንከኖችና በታላላቅ ጉዳዮች መሀከል፣ በቀላልና በከባድ መሀከል ነገራቸው እንዲህ ለሆኑ ሰዎች ጉዳዮቻቸውን እንዳስፈላጊነቷ ማከም ነገሮችን የእስላማዊውን ሕይወት ሂደት ለመጀመር ቻዮች በሚያደርጋቸው ሁኔታ ለማስተካከል እንዴት ይቻላቸዋል

በሙስሊሞች መካከል ልዩነት መቀስቀስ ወይም ምክንያቶቹን ማልማት ለእስልምና ዓላማዎች ታላቅ ክህደት ነው፡፡ ለዚህ ዘመናዊ ንቃትም ይህችንም በልቦናዎች ውስጥ ተስፋን ሕያው ያደረገችውን ዘመናዊ ንቃት መናድ ነው፡፡ የእስልምናን ጉዞም ማሰናከል ነው፡፡ የታማኝ ሥራዎችንም ትግሎች መበታተን ነው፡፡ አላህ ጀል-ለ ሸእኑሁ አይወደውም

ስለዚህም ዛሬ ለመላው ሙስሊሞች ሲበዛና አስፈላጊ ግዴታዎቻቸው በተለይም ለሰባኪዎች በአላሁ ተዓላ ከማመን በኋላ የእስልምናን ተሸካሚ ቡድኖችና ሰባኪዎቹን አንድ በማድረግ ላይ መሥራት በመካከላቸው የልዩነትን ምክንያቶች ሁሉ መጨረስ፡፡

የግድ ከሆነ ደግሞ በጠባብ ክበቦች ውስጥ እንዲሆን በጥሩ ቀደምቶቻችን ሥርዓቶች ውስጥ የሐሳቦች ልዩነት ከልቦች መገናኘት አይከለክልም፡፡ እስላማዊ የተከበረችውን ሕይወት ለመጀመር ኒያ ለአላሁ ተዓላ እስከጠራ ድረስ ያኔ መገጠምና የአላህ ድጋፍ ይከጀልላቸዋል፡፡

**የዛሬ የልዩነት ምክንያቶች**

የልዩነት ምክንያቶች በጊዜያቶች መካከል የሚለያዩ መሆናቸው የማይካድ ነው፡፡ ሁሉም ጊዜ ከበኋላው የሚመጡትን ጊዜያቶች ከፊል ምክንያቶቹን የሚያስወርስ ቢሆን እንኳ ዛሬ በሙስሊሞቹ መካከል ግልጽና ዋነኛ የልዩነት ምክንያቶች እስልምናን አለማወቅ ወይም እሱን የተጓደለ ዕውቀት ማወቅ በሙስሊሞች ሀገሮች ውስጥ ከሀዲው ቅኝ ገዥ ከመግባቱ በፊት የትምህርታዊው ሁኔታ እንደገለጽነው ነበር፡፡

በእስልምና ሀገሮች ከገባ በኋላማ ጉዳዩ ከፋትን ጨመረ፡፡ ወራሪዎች የዚህ ኡምማ ደረጃ የቱ ጋ እንደተደበቀ አወቁ፡፡ ትኩረታቸውን የትምህርት ፕሮግራሞች ወደማኖርና ተቋማቶችን ወደመገንባት አዞሩ፡፡ የሙስሊሞችን አዕምሮችና አስተሳሰባቸውን መቀየር በሚያስችላቸው መንገድ አዲሱን ዓለም አቀፍ ሁኔታና አስተሳሰብ ለመቀበል ዝግጁ እስከሚሆኑ ድረስ፡፡

አብረው ውህደትን ለመሞከር ከሀዲ የሆኑት ቅኝ ገዢዎች ሙስሊሞች አዲሱን ተጨባጭ መቀበል የዕድገትን ደረጃዎች ለመውጣትና ወደፊት ለመቀጠል ይረዳል ብለው በአውሮፓ ሀገሮች በማነፃፀር ያቺ ወደ ሥልጣኔ ደረጃዎች እውነተኛ እርምጃዋን ከሃይማኖት ሕጎች ከመፀችና ከቤተ ክርስቲያን ማሰሪያ ነፃ ከወጣች በኋላ እንጅ ያልተራመደች፡፡

ሃይማኖት - ማንኛውም ሃይማኖት ነው እንደነሱ አስተሳሰብ ወደተጠባቂው ድሎት ከመምጠቅ የሰው ልጆችን የሚጋርድ ማሠሪያ እንጅ አይደለም፡፡

«ከአፎቻቸው የምትወጣውን ቃል ምን አከበዳት ውሸትን እንጅ አይናገሩም፡፡» (አል-ከህፍ 18፡5)

እነኚህ ሙግቶች በተጣመሙት ሃይማኖቶቻቸው ትክክል ብትሆንም በሰው ልጅ ዕድለኛ እንዲሆንበት በአላህ ብርሃን እየተንቀሳቀሰ ሁሉንም ተስፋዎቹን እንዲያረጋግጥበት አላህ የሻ በሆነው እስልምና አንፃር ግን ትክክል መሆኑን ምን እንዲህ አራቀው

ኡምማውን ከመገኘቱ ምክንያቶችና ከእስልምና ሕይወቱ ለመቁረጥ ሲንቀሳቀስ ከሀዲው ቅኝ ገዢ እንቅፋቶችንና አቀበቶችን ሁላ እስላማዊ ትምህርት ፊት ለፊት አስቀምጧል፡፡ እሱንም የሚያስችልን እሱም ዐረብኛ ቋንቋ ማስተማር ነውና፡፡ ይህን ዓላማ ለማረጋገጥም ወደ እስላማዊ ትምህርት የሚያመሩ ተማሪዎች በእርግጥ ችላ ተብለዋል፡፡ የነሱን ደረጃ የሚቀንሱና ጥናቶቻቸውን እሚያዋርዱ አስተሳሰቦች ተሰራጩ፡፡ ጥናቶቹም ለትንሽ ደረጃዎችና ሥልጣኖችም የሚያበቋቸው ናቸው፡፡ በተቃራኒው በዘመናዊ ት/ቤቶች የተካፈሉና በውስጧ የተማሩ ተማሪዎች በእንክብካቤ ይለያሉ፡፡ በፊታቸውም ያበበ ሕይወት ይከፈትላቸዋል፡፡ በኡምማው ውስጥ የአመራር ቦታዎች በነሱ ላይ ብቻ ያጠሩ ሆኑ፡፡ እንደዚሁ በእስላማዊ ትምህርት ባለቤቶችና በዐረብኛ ቋንቋ ባለቤቶች ላይ ኑሮአቸው ተጣበበባቸው፡፡ ወደሱ የሚያደርሱ መንገዶች ሁሉ ተዘጉ፡፡ የሱን መንገድ የሚይዙ ጥቂት ተማሪዎች እንጅ የሉም፡፡ በተለምዶ በጣም ብዙ ለሆኑ ሁከቶች ይዳረጋሉ፡፡ ከመንገዱ እርከኖች በየትኛውም እርከን ለማፈግፈግ ሊያስገድዷቸው የሚችሉ በመቀጠል ላይ ችክ ያለ በፊት ለፊቱ ምንጊዜም

በሱና በሌሎች መካከል የመለየት ዓይነቶች አሉ፡፡ እንደአሳለፍነው በሥራዎች በሥልኖች በደረጃዎች በደልና የችሎታ ማነስ እንዲሰማው የሚያደርጉ ስለዚህም ኢስላማዊ ትምህርት በአብዛኞቹ ሙስሊም ሀገሮች ተማሪዎቹ አንሰዋል፡ ፡ ደረጃውም ወርዷል፡፡ አብዛኛዎቹ ወደሱ የሚዞሩ ሰዎች በምድር ላይ የሚዘራና ፍሬዋን መሰብሰብ እንደማይፈልግ ሰው ነው፡፡ የተወሰኑ ሁኔታዎች እንጅ የዚህን ዓይነት ትምህርት ለመማር የሚገፋፋቸውላይኖር ይችላል፡፡ ከጫናዎቹ ነፃ ለመውጣት ከተመረቁ በኋላ እንኳ አይችሉም፡፡ መንገዱ በፊታቸው ተዘግቷልና፡፡

አንድ ዓሊም በማህበረሰቡ ውስጥ ሊጫወተው የሚገባውን ሚና ለመሥራት የተንጠለጠለበትን ተልዕኮ ለማረጋገጥ አይችሉም፡፡ በተዘጉት በሮች

ፊት ለፊት ነፃነታቸውን ያጣሉ፡፡ ማንነታቸው ይደበዝዛል፡፡ ቋሚ ሃይማኖታዊ ተቋሞች ውስጥ ለመግባት ይገደዳሉ፡፡ ከበፊት የተጻፉ ዓላማዎችን ለማገልገል የተዘጋጁ እሷን ማለፍ የማይችሉና በነሱና በማህበረሱ ውስጥ ሚናቸውን ከመጫወት ይጋረዳል፡፡ ሰዎች በነሱ ያላቸውን እምነት በዚህ ኡምማና በእምነቱ መካከል ክፍተቱን በማስፋት ሙከራ በሸሪዓው የሚቀጥሉትን ሥራ ሥሮች መቁረጥን በማሰብ ከሀዲው ቅኝ ገዥ እስላማዊውን አስተምህሮትና የዐረቢያን ትምህርት በጥላ ውስጥ ማስቀመጥ ሞከረ፡፡ መስኩን ለአስተያየቶችና ለመረጣቸው መርሆች አገለለ፡፡ ለኡምማው ወጣቶች ወደገንዳዎቹ መውረድን ሸላለመ፡፡ እነዚህም ወጣቶች ሾከና ቆሻሻን እንጅ አላገኙም፡፡ የእንድር እንቧይን ምሬት እንጅ አልቀመሱም፡፡ በእርግጥም ሙስሊሙ ወጣት የአስተሳሰቦችን ዓይነቶች ሁሉ ሞከሯል ያን የተቀራበለትን ከኮሚኒስት ሥርዓት ወደ ሶሻሊስት ወደ ራዲካሊዝም ወደ ብሔርተኝነት ወደ ዲሞክራሲና ወደሌሎችም ከተሸለሙለት ቆሻሻ ያ የኢስላሙን ኡምማ በውርደት ላይ ውርደት የጨመረ የነበረችበትን ውርደት የበለጠ ውርደት፡፡ የኡምማውን ችግሮች በማከም ከውድቀቷ ለማንሳት የኋላ ቀርነቷን ምክንያቶች ለማጥፋት የሚችለው እስልምና ብቻ መሆኑን አረጋገጠ፡፡ ወደ እስልምና ፊቱን ለማዞር ወሰነ - መንገዶች ከዋለሉት በኋላ - ወደሱ መንገዱን በሃይማኖቱ ላይና በነፍሱ ላይ ከሚፈራው ጓደኛ ጋር ሳይሆን ወደሱ መንገዱን ሊጀምር፡፡ ስለዲኑ የማወቅና ሕግጋቶቹን የማወቅ ችግር ያጋጠመው ጊዜ ወደ መጽሐፎች ተጠጋ፡፡ በትክክለኛ አረዳድ ላይ ከሚያግዝ ቀዳሚ ስልታዊ ጥናቶች ውጭ ብቃት ያለው መምርም እንዳጣ ሁሉ፡፡ ያንን እጁን የሚይዘውን ከዕውቀት በሱ ላይ ይህን አዲስ ዓይነት በሚሆንበት ጥናት ውጤቱ እነዚህ ወጣቶች እስልምናን ካነበቧቸው መጽሐፎች አኳያ የሚረዱ መሆን ነበር፡፡ ከእስልምና የተወሰኑ ጎኖችን አዩ፡፡ ስለሱ የተሟላ አጠቃላይ ሐሳብ አይሰጣቸውም፡፡ ዓላማዎቹንና መርሆቹን ለማወቅ አያስችላቸውም፡፡ ትክክለኛን ዕይታም አይሰጣቸውም፡፡ ከግቦቹ አኳያ፡፡ እነሱ ከዝሆን አካል በተለያዩ ቦታዎች ላይ እጆቻቸው እንዳረፈ የዓይነስውራኖች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ ሁሉም የነካው ዝሆን ነው ብሎ እንዳሰበው

ዛሬ የሙስሊሞች ሁኔታ ከእስልምና ጋር እንደዚሁ ነው፡፡ ኡምማው ወደ ቡድኖችና ጭፍሮች ተለያይቷል፡፡ አንዷ ጭፍሯ ጀርባዋን ታዞረለች፡፡ የዝንባሌውን መኪና ትሳፈራለች፡፡ በሷም ምስራቁንም ምዕራቡንም ትዞርበታለች፡፡ ልክ ከእስልምና ጋር የወረሰቻቸው ስሞች እንጅ እንደማያስተሳስራት፡፡ የሀፍረት ቅሪት ባልነበረ ከሷም ትጥራራ ነበር፡፡

ሌላዋ ደግሞ ወደ እስልምና ለምለም ዛፍ ለመመለስ ትጓጓለች፡፡ ነገር ግን ወደሷ የተለያዩ መንገዶችን ትይዛለች፡፡ በመካከላቸው ልዩነት ይበታተናል፡፡ ከሷ ጠላቶችን ያመቻቻል፡፡ የባለሥልጣን ብትርም ትከታተላታለች፡፡ በሁሉም ሰማይ ስር ሁሉንም መስኮት ልትዘጋባት ትሞክራለች፡፡ እንጨቷ ሳይስተካከል በፊት ከሥር መሠረቷ ለመንቀል፡፡

**የመዳኛ መንገድ**

አሁን ኡምማው የሚሰቃይበት ሕመም በእርግጥ ታወቀ፡፡ ቀጣይ በሚመጣው ደግሞ የተወሰነ ሕክምና ሊኖረው ይችላል፡፡

አንደኛ፡- በታማኝ ሙስሊሞች ላይ በእስላማዊ ሰበካ መስክ ላይ የሚሠሩ በሆኑት የኡምማው አሳዛኝ ተጨባጭ የሚኖሩት እውነታዋንም ከኡምማው ልጆች ጮሎዎቹን ንቁ ወጣቶቹን መምረጥ አለባቸው፡፡ የሸሪዓን ትምህርቶች ለማጥናት የበለጡ መንገዶችን ማዘጋጀት በነዚህ ጥቂት ቁጥር ባላቸው ቀሪ ቅሪቶች ከሸሪዓ ዑለማኦች በሆኑት ላይ እነዚያ በዕውቀትና በመልካም አርአያነት መካከል የሚሰበሰቡ በተቅዋና በትክክለኛ አስተሳሰብ የእስልምና ግቦችን እና ዓላማዎቹን መርሆቹን በትምህርቶቹ ማወቅን ትክክለኛ አረዳድ የያዘ፡፡

እነዚያን ወጣቶች ሌሎች ጭፍሮች በተለያዩ የዘመናዊ ትምህርቶች የመጠቁ ኢኽላስና የአላህ ፍራቻ ያላቸው ይደግፏቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ እነዚህና እነዚያ ጉዞውን አቅጣጫ ያስይዙታል፡፡ ንቃቱንም ይመሩታል፡፡ እርምጃውንም ያስተካክላሉ፡፡ ኡምማዋ ጤንነቷን ትመልሳለች፡፡ ያንን ቀን ከቀን ወደ አዘቅት የሚቀርበውን በእስልምና ውስጥ መዳን የሌለው፡፡

ሁለተኛ፡- በሙስሊሞች ዘንድ የአስተሳሰብ ሂደትን ማስተካከል፡- ዛሬ ሙስሊሞች የሚኖሩት የአስተሳሰብ ቀውስ እንዲታከም ጥቂቶች እንጅ ጥልቀቷን አያውቁም፡፡ ይህቺ በግልጽ ይፋ የምትሆነው ችግር የኡምማው ተቋማቶች በመናዳቸው ድርጅቶቹ በመጥፋታቸው በልጆቹ ውስጥ የንቃትና የዕውቀት የአስተዳደግ ደረጃ በመውረዱ ግንኙነቷም በመበተኑ፡፡ ከመሪዎቿም አመዛኙ ብዙ ሕዝብ ለማፈንገጡ፡፡ የምርጥ ጥሩ ልጆቿ የተሻሉ ሙከራዎች ለመፍረሱ፡፡ ይህ ሁሉ እስልምና ከኡምማው ሕይወት ስለተራቀ ነው፡፡ ክፍተቱ ጥልቀት ያለው ሆኗል፡፡ በእስልምና ጥሩ ሥነ-ምግባሮችና በሰው ልጆች ስብስቦች መካከል እስልምናን በሰማይ ያለን ዳመና የማያዘንብ ጠፍ የማያቀና ወይም በለስላሳ ቋጥኝ ድንጋይ ላይ ውሃ ዘርንና ሣርን የማያበቅል አድርገው የሚያዩ ልቦች ደረቁ፡፡ ሽፋን አጠለለባቸው፡፡ ዓይኖች አጨነጨኑ፡፡ በበጎና በክፉ መካከል የማይለዩ ሆኑ፡፡

የተለያዩ የትምህርት ተቋማቶች ለኡምማው ትክክለኛ ሙስሊም ሰው ማቅረብ ተስኗታል፡፡ በሙስሊሞቹ ሀገሮች እንደ ምዕራባዉያን ዓይነት የተቋቋሙት ዩኒቨርሲቲዎች ዓላማቸው በአጠቃላይ የዕውቀት ዘርፎች አዋቂ ሙስሊም ማዘጋጀት እምነታቸው አይደለም፡፡ ያን አጠቃላይ ዕውቀቶችንና ሳይንሶችን በጆቹ ላይ እስላማዊ ማድረግ የሚችል፡፡ ይልቁንስ ዓላማዋ አድርጋ ያመነችው በምዕራቡ ሳይንሶችና ጥበቦች የተፈተነን ተማሪ ማዘጋጀት ነው፡፡ ያን ጆርባውን ለኡምማው እምነትና ለዓላማው ለግቦቹ የሚሰጠውን (በሕይወት) እነዚያ ዩኒቨርሲቲዎች በዝምድናቸው ደካማ የሆኑትን ትውልዶች አስመረቁ፡፡ በግንኙነታቸው የተደናገሩ በሐሳባቸው የተምታቱ ዕውቀታቸውን ለኡምማው አገልግሎት ማዋል የተሳናቸው፡፡

የሕጋዊነትን ሽፋን ያገኙት የትምህርት ተቋማትማ እንደ አዝሀርና የሱ ተመሳሳይ ዩኒቨርሲቲዎች ወይም ኮሌጆችና ኢንስቲትዩቶች የሱን ኮሌጆችና ኢንስቲትዩቶች የሚመስሉት እነሱ በተወሰነ መልኩ ስኬታማ ቢሆኑ እንኳ በከፊል የሸሪዓ ዕውቀቶች ጥሩ በአንድ ሞያ የሰለጠኑ ከፊል ሰዎችን ለኡምማው በማቅረብ ነገር ግን እነሱ ሙስሊም ምሁራኖችን መሪዎችን ተመራማሪዎችን አዳኞችን ለኡምማው ኢስላምን ከመርሆቹ ከግቦቹ ከዓላማዎቹ አንፃር ማቅረብ የሚችሉ ዘመናዊውን ተቃውሞ የሚጋፈጡ የሚያሸንፉትም እንዲህ ዓይነቶችን ማቅረብ ተስኗታል፡፡

ስለዚህም ኢስላማዊ አስተሳሰብ ተሰብስቧል፡፡ በሙስሊሞች ሕይወት ላይ በአስተሳሰባቸው ላይ ያጠለለው እሱ አይደለም፡፡ የሙስሊሞች ልቦናዎች ተከፈቱከእስልምና የተቃረነ ለሆነ አስተሳሰብ ሁሉ ሙስሊሞች ጉዳዮቻቸውን በፖለቲካና በኢኮኖሚ በማህበራዊ ሥርዓትና በሌሎቹም መስኮች መፍታት ተስኗቸው ቆመዋል፡፡

በሌሎቹ ዘንድ የሚያዩትን የጎደፈ አወሳሰድ የወሰዱ ሲሆኑ በኡምማው ልጆች ተማሪዎች መካከል የተለያዩ ግጭቶች በሁሉም ሁሉንም አካሎቹን አጥፍቷል፡፡ እነኚህ ግጭቶች አብዛኛውን ጊዜ በምዕራብ ለተቀመጠ ቡድን በሥልጣኔው ለተፈተነው ጥቅም ይቆረጣል፡፡ ግንባር ቀደም አማኞች ሰልፋቸውን አንበ ማድረግና እነዚህን ተቃውሞዎች በመጋፈጥ ላይ በመሥራት ፋንታ በግጭቶችና በልዩነት ጉዳዮች ተወጠረች፡፡ ያም ክፍሎች ከመርሆች ጋር ዓላማዎች ከመሠረቶች ጋር በብዙ የኡምማው ልጆች ውስጥ ስለተቀላቀለ ነው፡፡

ለኛ ጤነኛ ኢስላማዊ አስተሳሰብ በኢስላም ሩሕ ላይ እና በዓላማዎቹ በአጠቃላይ ሕጎቹ የሕግጋቶቹን ደረጃዎች በማወቅ ላይ የቆመ በጣም እንፈልጋለን፡

፡ በሁለት ታላላቅ ምንጮቹ አማካኝነት የተከበረው የአላህ መጽሐፍና የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና የጥሩ ቀደምቶችን መንገዶች ማጥናትም እንደሚያስፈልገን ሁሉ ከነዚህ ምንጮች ጋር በተሻሉት ክ/ዘመናቶች ውስጥ ምን ዓይነት ግንኙነት እንደነበራቸውም፡፡ የአረዳድ መንገዳቸውም የአላህን መጽሐፍ እና የረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ኡምማው ለሚሰቃይበት ችግር ዓላማዎችንና መፍትሔዎችን በድጋሜ ለማቅረብ እንድንችል ኡምማውን በሙሉ እምነት ላይ በሚያደርግ ሁኔታ እስልምና ይህ ኡምማ ለማዳን ብቸኛ መንገድ መሆኑን በውስጡ ለሁሉም ችግሮቿ ጥሩ መፍትሔ መኖሩንም

ይህ ኡምማውን በንቃትና በመረዳት በኢስላማዊ አስተሳሰብ መሠረቶች ዙሪያ እንዲሽከረከር ያስገደደው በነሱና በሰይጣናቶች መካከል እንዳትነዳቸው ይጋርዳል፡፡ ኡምማው ወደቀናው መንገዱ የተመለሰ ጊዜ እጁን በቁስሉ ላይ ያስቀመጠ ጊዜ የበሽታውንም ቦታ ያወቀ ጊዜ ከዚያ በኋላ መሄድ ያለባቸውን እርምጃዎች ማወቅ አለበት፡፡ ወደ መድኃኒቱ እንዲደርስ ዓላማውንም ወደማረጋገጥ ያ ነገር ደግሞ ከሱ የራቀ አይደለም፡፡

**ማጠቃለያ**

ያለፉት ሁለት ዓላማዎች እስከሚረጋገጡ ድረስ ግንባር ቀደም አማኞቹ ከመንሸራተት እንዲድኑ የተወሰኑ ነገሮችን ማወቅ አለባቸው፡፡ ከነዚያም፡-

1/ ነገሩ ፈጣሪ ችሎታው ከፍ ያለ ሲሆን በእርግጥ ቁርኣንን ለማስታወስ ቢያገራውም በሱንና ላይ ከተሟሉ ብዙ መጽሐፎቿ የሰፊ ግንዛቤ መንገዶችን ቢያመቻችልንም ከነዚህ ምንጮች በግለኛ እንቅስቃሴዎች መውሰድ ብዙ ጥንቃቄዎች ያስፈልጉታል፡፡ ቀዳሚ ዝግጅት መኖር አለበት፡፡ ከዚያም የሞያው ባለቤቶች የዘረዘሯቸውን መሣሪያዎች ለዚያ ጉዳይ መሰነቅ የማውጣጣት መስፈርቶችንና ሕጎቹን ከማወቅና ዐረብኛንና የአገላለጽ ስልቶቹን ማረጋገጥ፤ የቁርኣንንና የሱንናን ትምህርቶች ማወቅ፣ ሻሪን እና ተሻሪን፣ አጠቃላዩንና ልዩውን፣ ልዩ የተሻበትን አጠቃላይ፣ ከማስረጃዎች ወሰን የለሽና የተወሰነ በሱ ላይ ከሚመጡ ሌሎች ነገሮችም ማንኛውም ከአንድ ሙስሊም የሚገኝ ንግግር እነዚህን መዳረሻዎች ሳያካትትና ሳያውቅ እሱ በዲን ውስጥ በስሜትና በመላና በግምት መናገር ነው፡፡ ያለ ብርሃን፣ ያለ መመሪያ፣ ያለ ዕውቀት፣ ያን ያደረገ በእርግጥ አስቸጋሪ መርከብ ተሳፈረ፡፡ ራሱንም አጠፋ፤ አላህ ይጠብቀንና፡፡

በእርግት ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ቀጣዩን ተናግረዋል፡- «ስለቁርኣን ያለ ዕውቀት የተናገረ መቀመጫውን ከእሳት ይያዝ»

ይህ የዕውቀት ዓይነት አንድ መጽሐፍ ሁለት መጽሐፍ በማንበብ የሚመጣ አይደለም፡፡ ይልቁንስ በትህትና የተሞላ ፕሮግራማዊ ጥናት መኖር አለበት፡፡ በተማሪው እጅ የነዚያን ትምህርቶች ቁልፎች ዱያስገባ እነዚያ ወደ እስላማዊ አስተሳሰብ እና እስላማዊ ትምህርቶች መስክ የመግቢያን መንገድ የሚያዘጋጁ፡፡ ያቺ ጥናት ደግሞ ፍሬዋን እንድትሰጥ እስከመጨረሻ ድረስ በሚከታተል ጥናት መመካት አለበት፡፡ ያ ትሁትና መሪ አሳማሪ አስተዋይ ተቺ አስተማሪ የሚመራው በአላህ ፍርሃትና ከሱ አጅርን በመፈልግ ጥላ ሥር፡፡

2/ ይህ ሸሪዓ ሰዎችን በሁለቱም ሀገሮች በዱንያም በኣኼራም ዕድለኛ ለማድረግና አላህ በባሮቹ ላይ ያጣቀመበት አዕምሯዊ አቅሞች ጋር በሚጣጣም መልኩ ጥቅሞቻቸውን ለማረጋገጥ የተወረደ መሆኑን መንቃት አለባቸው፡፡ አላህ ጥራት ይገባውና ከሁሉም ፍጡሮች አከበራቸው፡፡ ደጉ ሸሪዓ ሰዎች መሥራት የማይችሉትን ጉዳይ በጭራሽ አላካተተም፡፡ ስለዚህ አላህ እንዲህ ይላል፡-

«በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፡፡» (አል-ሐጅ 22፡78)

አላህ ጥራት ይገባውና በእርግጥ በባሮቹ ላይ ያገራው በዚህ ሃይማኖት በፍቅር ጥላ ሥር እንዲሠሩ ነው በግዳጅ ሳይሆን ችሎታው የላቀው ጌታ በዚህ ጉዳይ ቀጣዩን ይላል፡-

«አላህ በናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፡፡ በናንተም ችግሩን አይሻም፡፡» (አል-በቀራህ 2፡185)

እና

«አላህ ከናንተ ሊያቃልልላችሁ ይሻል፡፡» (አን-ኒሳእ 4፡28)

ድክመታችሁን ስለሚያውቅ

«ሰውም ደካማ ሆኖ ተፈጠረ፡፡» (አን-ኒሳእ 4፡28)

ሁሉም የሸሪዓ ሕጎች የባሮችን ጥቅም አካተዋል፡፡ ለነሱ ጥቅምን ለማረጋገጥም ዳግተዋል፡፡ በውስጧ ጥቅሙ ወደ አላሁ ተዓላ የሚመለስ ምንም ነገር የለም፡፡ ያም የሆነበት አላሁ ተዓላ ሀብታሙና ምስጉኑ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህም ነገሩ የሸሪዓን ክፍልፋዮች ከነዚያ አጠቃላይ መርሆች ነፀብራቅ አኳያ መረዳት አለብን፡፡ ይህንንም የመሰለ ነገር፡፡ የሸሪዓን መርሆች ያላካበበ ዓላማዎቹንም ያልተረዳ ሕጎቹንም ያላወቀ እሱ ዘርፎችን ወደ መሠረቶች ክፍልፋዮችን ወደ መርሆች መመለስ አይችልም፡፡ ኢማሙ ኢብኑ ብርሃን ይላል፡-

« ... ሸሪዓዎች አላህ ባሮቹን የሚያስተናብርበት ማስተናበሪያዎች ናቸው፡፡ ሰዎች በዚያ ጉዳይ የተለያዩ ናቸው፡፡ እንደ ጊዜያቶቹ ልዩነት ለየጊዜው ሁሉ

የማስተናበሪያ ዓይነት አለው፡፡ ከእዝነትና ከጥቅምም በሱ የሚለይ ዕጣ አለው፡፡ ለሁሉም ኡመት የሚያሳምራቸው የማስተናበር ዓይነት እንዳለሁ ሁሉ ያ ነገር ለሌሎቹ ጥፋት ቢሆን እንኳ››

የኡምማው ምህራኖች ቃል የሸሪዓ ሕጎች ሁላቸውም ለባሮች ጥቅሞች የመጡ ናቸው በማለት አንድ ሆናለች፡፡ ለሷም ተደነገገች፡፡ አላህ እሷን ለማወቅ በግልጽ የነገረንም በመጥቀስ የነገረንም እኩል ነው፡፡ ያላወቅነውም ሁሉም አላህ ጀል-ለ ሸእኑሁ ለሚውቀው ጥበብ ነው፡፡ ስለዚህም በርካታ በርካታ የምርምር ሕጎች ጊዜዎች በመለዋወጣቸው ይለዋወጣሉ፡፡ ሰዎቹና አቅሞቻቸውም ችሎታቻቸውም ሁኔታዎቻቸውም በመለያየታቸው ሊለያዩ ይችላሉ፡፡

እንደዚሁ የቁርኣንና የሐዲሥ ማስረጃዎች ከነሱ ከአላህ እና ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) መሆኑ የተረጋገጠ አለ፡፡ እሱም ታላቁ ቁርኣንና ሙተዋቲር ሐዲሥ ነው፡፡ ከሐዲሥ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በመምጣቱ አጠራጣሪ አለ፡፡ ከአንዳንድ ሰዎች የተዘገበን ይመስል (አኽባረል አሓድ)

የሐተታው ትርጉም ትርጣሪያዊ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚሁ ጥርጣሪያዊም ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን ሁሉ ማወቅ በማውጣጣቱና በምርምሩ ከሐተታውም ለመረዳት ተጽዕኖ አለው፡፡ ማንም ሰው በሌሎቹ ላይ ከሐተታው የሚረዱትን ከሱ አረዳድ በተለየ መልኩ ሊጠላ አይችልም፡፡ ቃሉ የሚያስመቸው እስከሆነ ድረስ ማስረጃውም እስከሰፋለት ድረስ፡፡ ሌሎቹ የሸሪዓ ማስረጃዎች እስካልተቃረኑትና እስካልተቃወሙት ድረስ፡፡

አብዛኞቹ ከቅርንጫፎች ጋር የሚያያዙ ሕጎች ተግባራዊ ጎኖችን የሚዳስሱት እነሱ በጥርጣሪያዊ መንገዶች ከሚመጡት ዓይነቶች ናቸው፡፡ አላህ ለባሮቹ አዝኖ ነው ይህን ያደረገው፡፡ ለሰዎች በሷ ላይ የምርምሩ ሜዳ እንዲሰፋ ነው ጥበበኛው ሻሪዕ ለባሮቹ የማግራትን በር እስከፈተ ድረስ፡፡ የሰዎችን ጥቅም ታሳቢ እስካደረሰ ድረስ፡፡ ለአንድም ሰው ከነዚህ ነገሮች በአንዱ ከሱ የተለየን ወደ ክህደት ወይም ወደ አመጽ ወይም ወደ ፈጠራ ማስጠጋት አይገባውም፡፡ ይልቁንስ ለተፃራሪው ምክንያቶችን መፈለግ አለበት፡፡ በመካከላቸው የፍቅርን ገመድ የተቀጠለ የሚያደርግበትን የሱን ፍቅርና ክብር እንዲያገኝ ወንድምነቱንና ፍቅሩን እንዲጠብቅ፡፡

3/ ከግዴታዎቹ ሁሉ ይበልጥ አስፈላጊው ሁሉም ሰው የእስልምና ወንድማማችነትና የውነተኞች ሙስሊሞች ሰልፎች እሷንም መጠበቅ ለሷ የሚከፋውን ሁላ መጣል ወይም ከዘለበቷ የሚያደክመውን ይበልጥ አስፈላጊ ግዴታዎችና አደገኛው መሆኑን መረዳት ነው፡፡ እንደዚሁም ከአስፈላጊ አምልኮዎች

አንዷ ከበላጭ መቃረቢያዎች አንዷ መሆኗንም ምክንያቱም እኛ በዚህ ወንድማማችነት አላህንና ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) በሚያስደስት መልኩ እስላማዊ ሕይወት መጀመርን የሚያሰናክሉ አቀበቶችን ሁሉ መጋፈጥ እንችላለን እና ነው፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አንድነትን የሚበታትንን ሰው ደም ደመከልብ በማድረግ ልዩነትን እንዲንጠላ ማድረጋቸው ብቻ ይበቃል፡፡ ስለዚህ እስላማዊን ወንድማማችነት ችላ ማለት ወይም እሱን መንካት ለአስተሳሰብ ልዩነት ብቻ ለአንድ ሙስሊም ማድረጉ የማይፈቀድ ጉዳይ ነው፡፡ ወይም በሱ ጫማ ሥር መውደቅ፡፡

በተለይ በዚህ ኡምማዎች በኛ ላይ በተጠራሩበት ሁኔታዎች በልቦች ውስጥ መንቀልቀል የጀመረችውን የእምነት ችቦ ለማጥፋትና ጥሩዋን ዘር ለማጥፋት በምትሻበት ያቺን አፈርን መቅደድ የጀመረችውን የሚወርዱባት ቀላጅ እጆች መንቀል የሚሞክሩ ቢኖሩ እንኳ፡፡ ለአላህ ብሎ ወንድማማችነትና በሙስሊሞች መካከል የልቦች አንድነት ለግዴታዎች የመጀመሪያዎቹን እርከኖች ይሰፍራሉ፡፡ እንዳውም እሷ የመጀመሪያ ነች እሷ የተዊሒድ ስንጣቂና ጓደኛው ስለሆነች፡፡ ለክልክሎችም እርከኖች እንዳሉ ሁሉ ወንድማማችነትን መንካት እንደዚሁ ከመጀመሪያው እንደሚገኝ

ስለዚህም የቀደምት ዑለማኦች ብዙውን ጊዜ ተበላጩን ሠርተው በላጩን ይተው ነበር አንድነትን ለመጠበቅና ከልዩነት ለመውጣት እንደነሱ አስተያየት የተወደደውን ሊተው ይችላሉ፡፡ የተፈቀደውን ይሠራሉ ያንኑ ለማረጋገጥ፡፡

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ አሉ፡-

ከፊላቸው ከከፊላቸው በኋላ መስገድ መፈቀዱ ላይ ተስማምተዋል፡፡ ሰሓባዎችና ተከታዮቻቸውም ከነሱ በኋላ ያሉትም ከአራቱ መሪዎች ከፊላቸው ከከፊላቸው በኋላ ይሰግዱ እንደነበረው ይህን የጠላ ሰው እሱ የፈጠራ ሰው ነው የጠመመ ቁርኣንንና ሱንናን የሙስሊሞቹን ስምምነት የተቃረነ ነው፡፡ በሰሓባዎችና በታቢዒዮች ውስጥ ከነሱ በኋላም በስመላን የሚያነብ ነበረ፡፡ ከነሱም ውስጥ የማያነብ ነበረ፡፡ ከዚሁም ጋር ከፊላቸው ከከፊላቸው ጋር ይሰግድ ነበረ፡፡ አቡ ሐኒፋና ባልደረቦቻቸው ሻፊዒና ሌሎችም በመዲና አሰጋጆች ኋላ ይሰግዱ እንደነበረው ማሊኪያ ከመሆናቸው ጋር በስመላን የማያነቡ ቢሆኑ እንኳ በድብቅም በግልጽም አቡ ዩሱፍ ከረሺድ ኋላ ሰግዷል፡፡ ታሞ ሳለ ማሊክ ዉዱእ ማድረግ ግዴታ ባለመሆኑ ፈትዋ አደረገለት ከኋላው አቡ ዩሱፍ ሰገደ ሶላቱን አልመለሰም፡፡ አሕመድ ከሒጃማና ከነስር ዉዱእ ማድረግን ያምን ነበረ፡፡ ተጠየቀ

አሰጋጁ ደም ወጥቶት ከሆነ ዉዱእ አላደረገም ከኋላው እሰግዳለሁ አለም ከሰዒድ ኢብኑል ሙሰይብና ከማሊክ በኋላ እንዴት አትሰግድም በአንድም ሰው አስተሳሰብ ውስጥ እንዳይፈስ በእስላማዊ ወንድማማችነት ትኩረታችን የሙስሊሞቹ ሰልፍ አንድነት ላይም ማተኮራችን መሠረታዊ የዐቂዳ ጉዳዮች ላይ ማግራራትን ይሻል ማለት

እዚነያ ትችትን የማያስሙቹ በዐቂዳ በተረጋጉ ሕጎች ድንበሮች ውስጥ ያም የኡምማውን ጠላቶች መጋፈጥ ላይ ማትኮር እጆቻችንን በነዚያ በእስልምና ሰዎችን እንጅ ምንም ዕድል የሌላቸው ላይ ወደማኖር አይገፋንም ለወንድምነት በመጓጓት ማስረጃ ሊለዩን የማይፈቀድ የልዩነት ጉዳዮች ከሰለፍ ከሰለፍ መሪዎች የተከበሩት ዑለማኦች ያመኑባቸው ከሷ ጋር ከተከበሩ ሥርዓቶች አካያ አብረዋት የተስማሙት እነሱ ጋር ከማስረጃ ካንድ መንገድ በላይ የሚያስፈቅድ እያላቸው

4/ ፈጣሪ ጥራት ይገባውና ለሰዎች በብዙ ጉዳዮች አምልኮዎችን በተለያዩ ደረጃዎች መፈጸምን መደነገጉ ከታወቁ ጉዳዮች እንደሆነ ሁሉ በበላጭና በተመራጭ በመፈቀድ መካከል ይከፋፈላሉ፡፡ እነዚህ ያለፉት ደረጃዎች ሁላቸውም በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ከመሆን አኳያ የሚገናኙ ቢሆኑም ነገር ግን በደረጃዎች ይተላለፋሉ፡፡ ብዙ ግዴታዎችና ዋጂቦች ብዙ ቅርፆች አሏቸው፡፡ እነዚህ ሦስት ደረጃዎች ውስጥ ይካተታሉ፡፡ አንድ አምልኮ በበላጭ ሐጋዊ ቅርጹ ሊሠራ ይችላል፡፡ ከትርፍ ምንዳ ጋር ተቀባይነት ያገኛል፡፡ በህብረት በሰዓቱ መጀመሪያ ላይ እንደሚሰግድ ሰው ለሶላት ተፈላጊ የሆኑትን ሱንናዎች ሁሉ ይፈጽማል፡፡

ምርጫም አለ እሱ ያንኑ ሥራ መተግበር ነው፡፡ ከበላጭ ደረጃ በታች በሰዓቱ ውስጥ እንደሚሰግድ ሰው፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያው አይደለም ይልቁንስ ከሱ በምርጫ ሰዓት ከዚያ ሦስተኛ ደረጃ የፍቃድ ደረጃ ነው፡፡ እሱ ያ አንድ ባሪያ ለራሱ ከሱ ያነሰው ደረጃ ከተቀበለ በችላ ባዮቹ ውስጥ የሚገባበት ነው በአሰር ውስጥ ቀጣዩ መጥቷል፡- «የውነተኞቹ መልካም ሥራዎች የባለሟሎቹ ኃጢአቶች ናቸው» ከሁሉም ሰው ሁኔታዎቻቸው ከመለያየቱ ጋር ለእስልምና ሐሳባዊ ቅርጽን ለማረጋገጥ የጠበቀ ሰው በእርግጥም ማግኘቱ ቀላል ያልሆነን ጉዳይ ይሻል

የአምልኮዎችና የታዛዥነቶች ደረጃዎች መተላለፍ ባልነበረ በጀነት ውስጥ የአማኞች ደረጃዎችም ባልተላለፉ ነበር፡፡ የሰዎች አቅሞች የተለያዩ ናቸው፡፡ ችሎታዎቻቸውም የተፈራረቁ ናቸው፡፡ ሁሉም ለተፈጠረለት ጉዳይ የተገራ ነው፡፡

ኢብኑ ጀሪር አጠበሪ በተፍሲራቸው ዘግበዋል፡- የሆኑ ሰዎች ዐብደላህ ኢብኑ ዑመርን በግብፅ አገኙትና አሉ፡- በአላህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲሠራባቸው

ያዘዘ የማይሥራባቸው ነገሮችን እናያለን፡፡ በዚህ ጉዳይ የአማኞቹን አዛዥ ማግኘት ሽቶን መጣ እነሱም አብረውት መጡ፡፡ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁ አገኘውና መቼ መጣህ አለው እንዲህ እንዲህ ነው አለው፡፡ በፍቃድ ነው የመጣህው አለው ሐሰን አለ (ሐዲሡን ዘጋቢው)፡- (እንዴት እንደመለሰለት አላውቅም) አለም፡- አንተ የአማኞች አዛዥ የሆኑ ሰዎች በግብጽ አገኙንና አለ፡- እኛ በአላህ ተባረከ ወተዓላ መጽሐፍ ውስጥ እንዲሥራባቸው ያዘዘና የማይሠሩባቸው ነገሮች እናያለን፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊያገኙህ ፈለጉ፡፡ ሰብስብልኝ አለ፡፡ ሰበሰብኩለት፡፡ አለ ወደሱ የቀረበን አንድ ሰው ያዘና አለ፡- በአላህ እይዘሀለሁ እስልምና ባንተ ላይ ባለውም ሙብት ቁርአንን ሁሉንም አንብብሃል አዎ አለ፡፡ ሁሉንም በራስህ በሁሉም ሥርተህበታል አልሠራሁበትም አለ፡፡ (አዎ ቢል ኖሮ ይከራከረው ነበር) በዓይንህስ አዳርሰህዋል አለ በአንደበትህስ አዳርሰህዋል ልጆችህን አስተምረሃል አለ ከዚያ በመጨረሻቸው ላይ እስከመጣ ድረስ ተከታተላቸው አለም ዑመርን እናቱ ትጣው ሰዎችን በአላህ መጽሐፍ ላይ እንዲያቆም ታስገድዱታላችሁ ጌታችን በእርግጥ ኃጢአቶች እንደሚኖሩን አውቋል አለ የአላሁ ተዓላን አባባል አነበበ፡-

«ከርሱ ከተከለከላችሁት ታላላቆቹብ ብትርቁ (ትናንሾቹን) ኃጢአቶቻችሁን ከናንተ እናብሳለን፡፡ የተከበረንም ስፍራ (ገነትን) እናገባችኋለን፡፡» (አን-ኒሳእ 4፡31)

ከዚያም አለ የመዲና ሰዎች አውቀዋል ወይም አለ አንድም ሰው የመጣችሁበትን አውቋል አሉ አላወቀም፡፡ አለ ቢያውቁ ኖሮ በናንተ እመክር ነበር፡ ፡ መቀጣጫ ያደርጋቸው ነበር ማለት ነው ለሌሎቹ ማስተዋያና መገሰጫ ሊያደርቸው፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ ድካ የደረሰ ትምህርት አለበት፡፡ ሰዒዲና ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁ ለሙስሊም ታላቁ ቁርአን የግድ ያደረጋት ታላቋ ምሳሌ እሷ ናሙናዊ ቅርጽ ነች አንድ ሙስሊም እውን ሊያደርጋት መሞከሩ የሚገባ ማለትን የሚገልጽበት ነገር ግን እሷ ላይ መድረስ ካልቻለ የአላህ እዝነት ሰፊ መሆኑን መረዳት አለበት፡፡ ነገሩኮ ታላላቅ ወንጀሎች ሲራቁ አንድ ሙስሊም አላህ ከሻ በብዙ በጎ ሥራ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ምንጊዜም ወደታላቋ ምሳሌ መቋመጥ አለበት፡፡ በታናሹ ተደንቆ በሱ ድንበሮች ላይ መቆም የለበትም፡፡

5/ በአሁኑ ጊዜ የልዩነትን ምክንያቶች ለመቀነስ ከሚረዱ ነገሮችና በሥርዓቶቹ በመሸለም ላይ የሚቀሰቅሱት ከቀደምት ፉቀሃኦች ሪድዋኑሏሂ ዐለይሂም የልዩነትን ምክንያቶች ማወቅና እነዚያን ምክንያቶች መረዳት የግላዊነታቸውንም መጠን ያ የልዩነትን ሥርዓት ለመያዝ ከቀስቃሾቹ እንዲሆን

እነሱ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩት ባልተዛቡ ምክንያቶች ነው ሁላቸውም ትጉዎች ነበሩ፡፡ ከነሱ እያንዳንዱ ሐቅን በመፈለግ የጠፋን ነገር እንደሚፈልግ ነበሩ፡፡ ከሱ ጋ ምንም ልዩነት የለም፡፡ ያቺ የጠፋች ነገር በጁ ከመገኘቷና በሌላ እጅ ከመገኘቷ መካከል

6/ ሙስሊሞችን የልዩነት ሥርዓቶችን ለመያዝ ለመገፋፋት የሚጠቅሙ ጉዳዮች አስፈሪ የሆኑ አደጋዎችንና አደገኛ የሆኑ ሙከራዎችን ተንኮለኛ የሆኑ ፕላኖችን የእስልምና ጠላቶች የዚህን ሰበካ ባንዲራ የምትሸከመውን አማኝ ግንባር ቀደም ቡድን ለመጨረስ የሚያዘጋጁቸውን ማወቅ ምንጊዜም በጠላቶቹ ሒሳብ ከቻሉ ሌላዋ ስትቀር አንዷ ጭፍራ ከእጃቸው ማምለጥ የለም፡፡ ዋናው ለእስልምና ሠሪዎቹን ከመዝሀቦቻቸው ልዩነት ጋር አስተያየታቸው ከመለያየቱ ጋር መጨረስ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሙስሊሞች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት መቀስቀስ ወይም ምክንያቶቹን ማልማት ወይም ሥርዓቶቹን መተላለፍ ለኡምማው ዓላማዎች ታላቅ ክዳት ያደርጋል በጎ ማድረጉ የማይቻል ወይም በምንም ተአምር ይቅር የማይባል በኡምማው ሙብት ታላቅ ወንጀል ያደርገዋል፡፡

7/ ከዚህ በፊትና ከዚህም በኋላ በድብቅም ሆነ በግልጽ የአላህን ፍርሃት ከመያዝ ቅሮት የለም፡፡ በስምሙነትም ጊዜ ሆበ በልዩነት የሱን ውዴታ ከመፈለግም የአላህን ሃይማኖት በመረዳት ላይና ከዝንባሌ መጽዳት ከሰይጣን ማበላሸቶችም መራቅ ላይ ከመጓጓት ጋር የኢብሊስን መንገዶች ማወቅ እና ከወጥመዱ መጠንቀቅ ኡምማው ያጋጠመውና የተሰቃየበት ይበቃዋል ወደ ቀጥታው መንገድ እንዲመለስ ጊዜው በእርግጥ ቀረበ፡፡ በጌታው መጽሐፍ እንዲመራ የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሥ በመንጋጋዎች ነክሰው እንዲይዙ አላህ የዚህን ኡምማ መዳን በዚህ ትውልድ በጎ አድራጊ ልጆቹ እጅ ሊጽፈው ይከጀላልና ከአላህ ጋር ውሳኔ እውነተኛ የሆነች ጊዜ ከመንገዶች ቅፍለቶቹን ወደሰላም ዳርቻ ለመውሰድ አስተማማኙን የያዘች ጊዜ፡፡ የመንከራተትና የጥመት ሌሊት ከረዘመ በኋላ ከኡምማው ደጋጎቹ ለአማኝ ቡድኖች መስተካከልንና መገጠም ዱዓቸውን አይንፈጉ አላሁ ተዓላን የሚጠቅመንን እንዲያስተምረን እንለምነዋለን

ባሳወቅንም ይጥቀመን ዕውቀትንም ይጨምረን ቃላችንን በሐቅ ላይ ይሰብስበው በነገሮቻችን ሁሉ ቅኑንና ትክክለኛውን ያሳውቀወን የነፍሶቻችንን ተንኮሎችና የሥራዎቻችንን ኃጢአቶች ይጠብቀን እንደዚያች ፈትልዋን ከጠነከረ በኋላ ትርትሮች አድርጋ እንዳፈረሰችው ሴት እንዳያደርገንም እሱ ጥራት ይገባውና የዚያ ጌታ ነው በሱም ላይ ቻይ ነው፡፡ የመጨረሻ ጸሎታችንም ምስጋና ለዓለማት ጌታ ይህን (ማለት) ነው፡፡

ተፈጸመ

ማውጫ

ርዕስ ገጽ
መግቢያ
ክፍል አንድ
የልዩነትን ሕልውናና ከሱ ጋር የሚያያዙትን ስለመግለጽ
ልዩነትና ንትርክ የልዩነት ሳይንስ ክርክርና የክርክር ሳይንስ ግጭት
ከልዩነት ተቀባይነት ያለውና ተቀባይነት የሌለው
ከፊል ተቀባይነት ያለው ልዩነት ጥቅሞች
የልዩነት ዓይነት ከአነሳሾች አኳያ
ዝንባሌ ያመነጨው ልዩነት
በማሞገስና በማውገዝ መካከል የሚመላለስ ልዩነት
የዑለማኦች አስተያየት በልዩነት
ክፍል ሁለት
የልዩነት ታሪክና ዕድገቱ
በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ የሰሓባዎች ልዩነት
ትችትና ዓይነቶቹ (ቅርብ-እሩቅ-ሩቅ የተደረገ)
የትችት መስፈርቶች (ትችት ከፍቺ ጋር ያለው ልዩነት)
የትችት መስፈርቶች የተበላሹና ተመላሽ ትችቶች

ከሰሓባ የጥረት (ኢጅቲሃድ) ባለቤቶች
ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦቻቸውን ከልዩነት ማስጠንቀቃቸው
በነብይነት ጊዜ የልዩነት ሥርዓት ገጽታዎች
ልዩነት በሰሓባዎች ጊዜና ሥርዓቶቹ
(በነብዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ሞትና በመቅበሩም ከዚያም በምትክነቱ)
ዘካን የከለከሉትን መዋጋቱ ሌሎች ከፊል የፊቅህ መስአላዎች
በሁሉም ሁኔታ የልዩነትን ሥርዓት መያዛቸው)
በቅን አስተዳዳሪዎች ጊዜ የልዩነት ሥርዓት ገጽታዎች
ልዩነት በታቢዒዮች ጊዜና ሥርዓቶቹ
የፖለቲካዊ ልዩነት ተጽዕኖ በእምነታዊና በፊቅሃዊ ልዩነቶች
ኢብኑ ዐብ-ባስ ከኸዋሪጆች ጋር ያደረጉት ክርክር
ክፍል ሦስት
የመሪዎች ስልቶች ልዩነት በማውጣጣት
የፊቅህ መዝሀቦች
በጣም የታወቁ መሪዎች ስልቶች
(የኢማሙ አቡ ሐኒፋ ስልት - የኢማሙ ማሊክ ስልት - የኢማሙ ሻፊዒ ስልት - የኢማሙ አሕመድ ስልት - የዛሂሪያ መዝሀብ ስልት)
ለኛን ሐሳብ አለን
ክፍል አራት
የልዩነት ምክንያቶችና ዕድገታቸው
የልዩነት ምክንያቶች በነብይነት ጊዜ እስከ ኹለፋኦች ጊዜ
የፊቅህ ልዩነቶች ምክንያቶች በፉቀሃኦቹ ጊዜ
(ወደ ቋንቋ የሚመለሱ ምክንያቶች - ወደ ሱንናዎች ዘገባ የሚመለሱ ምክንያቶች - ወደ ኡሱል ሕጎችና ወደማውጣጣት መስፈርቶች የሚመለሱ ምክንያቶች)
ክፍል አምስት
በመሪዎች መካከል የልዩነት ገጽታዎችና ሥርዓቶቹ
የለይስ ኢብኑ ሰዕድ መልዕክት ወደ ኢማሙ ማሊክ
በተከበሪ መሪዎች መካከል የልዩነት ሥርዓት ናሙናዎች ከጥሩ ሰለፎች የሆኑ

(አቡ ሐኒፋና ማሊክ - ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰንና ማሊክ - ሻፊዒና ሙሐመድ ኢብኑል ሐሰን - ማሊክና ኢብኑ ዑየይና - ማሊክና ሻፊዒ - አሕመድ ኢብኑ ሐንበል እና ማሊክ)
ከፊል የዑለማኦች አስተያየት በአቡ ሐኒፋ
የከፊል ዑለማኦች አስተያየት በሻፊዒ
በኢማሙ አሕመድና በሻፊዒ መካከል
ክፍል ስድስት
ልዩነትና ሥርዓቶቹ ከተበላሹት ክ/ዘመናት በኋላ
በሂጅራ አራተኛው ክ/ዘመን
ከአራተኛው ክ/ዘመን በኋላ የነበረው ሁኔታ
የጭፍን መከተልና መጨረሻዎቹ
የኡምማው ሁኔታ በመጨረሻዎቹ ዘመናት
የዛሬው የልዩነት ምክንያቶች
የመድን መንገድ
ማጠቃለያ
ማውጫ